# በበረሐው ጉያ ውስጥ

የቀደምት አበው እና እማት መንፈሳዊ ኑሮና ምክር

፪ኛ እትም

በ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

[illegible] እና አከፋፋይ
[illegible] ንትመትና ጠቅላላ ንግድ ስራ ሐላ.የተ.የግ.ማኅበር

1998 ዓ.ም
አ.አ

0.0
200
በበ

ደብረ ሲና

የገረፏቸው፣ የዘበቱባቸው፣ ያሰሯቸውም፣ ወኅኒ ያገቧቸውም አሉ። በመጋዝ የሰነጠቋቸው፣ በድንጋይ የወገሯቸው፣ በሰይፍ ስለት የገደሏቸው አሉ፤ ማቅ፣ ምንጣፍ፣ የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ ተጨነቁ፤ ተቸገሩ፤ መከራ ተቀበሉ፤ ተራቡ፤ ተጠሙ። ዓለም የማይገባቸው እነዚህ ናቸው፤ ዱር ለዱር፣ ተራራ ለተራራ፣ ዋሻ ለዋሻ፣ ፍርኩታ ለፍርኩታ ዞሩ።

ዕብ.11፥36-38

Mega Printing Plc

ዋጋ ብር 25.00

[illegible] ለቤተመፅሐፍት የተበረከተ

# በበረሓው ጉያ ውስጥ

የላፍቶ ደ/ት/ቅ/ሚካኤል
እና ቅ/ጊዮርጊስ
ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት ቤ/መጻሕፍት

## የቀደምት አበው እና እማት

## መንፈሳዊ ኑሮና ምክር

አርተር፦ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

*አሳታሚ እና አከፋፋይ፦*

*አግዮስ ንትመት እና ጠቅላላ ንግድ ሐላ / የተ / የግ / ማኅበር*

1998 ዓ.ም.

© ዳንኤል ክብረት

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

All Rights Reserved

የመጀመሪያ እትም 1998 ዓ.ም.

ሁለተኛ እትም 2003 ዓ.ም.

ሦስተኛ እትም 2004 ዓ.ም.

አራተኛ እትም 2009 ዓ.ም.



አሳታሚ እና አከፋፋይ

አግዮስ ኅትመት እና ጠቅላላ ንግድ ሐላ / የተ/ የግ/ ማኅበር

**አድራሻ:-** መገናኛ፣ ለም ሆቴል ባቡር ጣቢያ ፊት ለፊት
ማትያስ ሕንፃ፣ ቢሮ ቁ 404
አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

ስልክ 251-911-474503
ኢሜይል:- danielk@agyos.com
ገጸ ድር:- www.agyos.com
www.danielkibret.com

# መታሰቢያነቱ



በአሶሳና በአካባቢው ከ40 ዓመታት በላይ በስብከተ ወንጌል፣ አብያተ ክርስቲያናትን በማነፅ፣ ሕዝቡን ለልማት በማስተባበር ላገለገሉት፣ በሙስሊሙም በክርስቲያኑም ዘንድ ለሚወደዱት፣ የእርጅና ድካም ሳይበግራቸው፣ የቦታ አለመመቻቸት ሳያግዳቸው ሐዋርያዊ ተልዕኳቸውን ለፈጸሙት፣ የአሶሳ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ለነበሩት ለነፍስ ኄር መልአከ ኃይል አባ እንየው ውቤ ይሁን::

## ማውጫ


ርዕስ ገጽ

መቅድም ........ 6
መግቢያ ........ 8
አርሳንዮስ ........ 12
አባ አጋቶን ........ 16
አባ አብርሃም ........ 19
አባ ገላስዮስ ........ 20
አባ ኤጲፋንዮስ ........ 21
አባ ኤፍሬም ሶርያዊ ........ 22
ኤቫግሪዮስ ........ 24
10. አባ ኤልያስ ........ 25
11. አባ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት ........ 25
12. ዮሐንስ ሐዊር ........ 26
13. አባ መቃርዮስ ........ 30
14. አባ እንጦንስ ........ 42
15. አባ ሙሴ ጸሊም ........ 49
16. አባ መጣዕ ........ 54
17. አባ ማርቆስ /የአባ ስልዋኖስ ደቀ መዝሙር/ ........ 55
18. አባ ሜላስዮስ ........ 55
19. አባ ማርቆስ ግብፃዊ ........ 56
20. አባ ኔለስ ........ 56
21. አባ ኔጥራስ ........ 57
22. አባ ኔቅጣስ ........ 57
23. አባ ዞዮስ ........ 58





24. አባ ዛንትያስ ........ 58
25. አባ አሊምፐስ ........ 58
26. አባ አርሲሲየስ ........ 59
27. አባ ጴሜን ........ 59
28. አባ ፓምቦ ........ 67
29. ጲስጦስ ........ 67
30. ጲዮር ........ 68
31. አባ ጳውሊ መፍቀሬ ትሕትና ........ 69
32. አባ ሩፎስ ........ 71
33. አባ ሲዞስ ........ 71
34. አባ ስልዋኖስ ........ 73
35. አባ ስምዖን ........ 74
36. አባ ሳርማታስ ........ 75
37. አባ ሰራፕዮን ........ 75
38. እማሆይ ሣራ ........ 76
39. እማሆይ ሲንቅሌጢቃ ........ 76
40. አባ ጥጦስ ........ 79
41. አባ ጢሞቴዎስ ........ 80
42. አባ አውር ........ 80


*«አርተር» ማለት አርታኢ እና ተርጓሚ ማለት ነው።*

*በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የካርቱን ሥዕሎች የሳለው*
*ዘሪሁን ገብረ ወልድ ለማ ነው።*

# መቅድም

ገዳማዊ ሕይወት በግብፅ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በየበረሓው ለሚገኙ አበው ሁለት የመንፈሳዊ ሕይወት መመሪያዎች ነበሯቸው:: የመጀመሪያው ቅዱሳት መጻሕፍት ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ ከቀደሙ አበው የሚገኘው መንፈሳዊ ጥበብ ነው::

ይህ መንፈሳዊ ጥበብ ከኑሯቸውና ከንግግራቸው የሚገኝ ነበር:: በየ ገዳማቱ ለመንፈሳዊ ተጋድሎ የተሰለፉ የእነዚህን አበው ሕይወትና ንግግር ለማሰባሰብ ብዙ ሊቃውንት በየበረሓው ተጉዘው ነበር:: አባ ሄሮኒመስ፣ ታሪክ ጸሐፊው ሩፊኖስ፣ ጳላድዮን፣ ኤቫግሪዮስ እና ዮሐንስ ካስያን ተጠቃሽ ናቸው::

ከገዳማውያን አበው የተገኙት ብሂሎች በተለያዩ ደረጃዎች አልፈው ለዚህ ዘመን መድረሳቸው ይታመናል:: የመጀመሪያው ደረጃ እነዚያን መንፈሳውያን አርበኞች የሆኑ ገዳማውያን አበው ለሚቀርቡ፣ ለሚጠይቁና በረድእነት ለሚያገለግሉ በየዘመኑ በቃል የተነገሩበት ደረጃ ነው:: ወደ ግብፅና ፍልስጥኤም በረሓዎች እነዚህን አበው ለማየት በመጡ ክርስቲያኖች አማካኝነት ለ300 ዘመናት ቃል በቃል ሲተላለፉ ቆይተዋል::

ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ እነዚህ በቃል የተላለፉ የአበው ብሂሎች ወደ ጽሑፍ የተሸጋገሩበት ዘመን ነው:: ይህም በአራተኛው መ/ክ/ዘ መጨረሻ እና በአምስተኛው መ/ክ/ዘ መጀመርያ አካባቢ መከናወኑ ይታመናል::

ሦስተኛው ደረጃ ደግሞ የአርትዖት ሥራ ተሠርቶላቸው በተናገሯቸው አበው የፊደል ተራ ቅደም ተከተል ወይም በጉዳያቸው መሠረት የተቀመጠበት ደረጃ ነው:: በዚህ መልኩ የተለያዩ ጥራዞች በአምስተኛው መ/ክ/ዘ አጋማሽ መውጣት ጀምረዋል:: ከፊደል ቅደም ተከተል በተጨማሪም ጸሎት፣ ትኅትና፣ ታዛዥነት፣ ወዘተ በሚሉ ንዑሳን





ርዕሶች ተከፋፍለው ተዘጋጅተውም ነበር::

በመካከለኛው ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት መጻሕፍት መካከል የሚቆጠሩት መጻሕፍተ መነኮሳት (ፊልክስዮስ በዐፄ ድል ነዐድ፣ አረጋዊ መንፈሳዊ በዐፄ ልብነ ድንግል፣ ማር ይስሐቅ በዐፄ ገላውዴዎስ ዘመን ተተርጉመዋል):: ይዘታቸው ከእነዚህ የአባቶች ብሂል የተቀዳ ነው:: መጽሐፈ መነኮሳት እየደጋገመ የሚጠቅሰው ጳላድዮን (palladius) የተባለ ጸሐፊ በግብፅና ፍልስጥኤም በረሓዎች ተዘዋውረው የእነዚህን አበው ሕይወትና ብሂል ካሰባሰቡት የአራተኛው መ/ክ/ዘ ሰዎች አንዱ ነው::

የእነዚህን አበው ብሂል ማንበብ በቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዘንድ የተለመደ ነው:: አውግስጢኖስ እና ዞሲማስ ብሂሎቹን ያነቧቸው እንደነበር ተዘግቧል:: አባ ዞሲማስን በተመለከተ አንድ የታሪክ መዝገብ «ይህ ብፁዕ ዞሲማስ የእነዚህን የተቀደሱ አበው ብሂሎች አዘውትሮ ማንበብን ይወድድ ነበር:: እነርሱ ለእርሱ እንደሚተነፍሰው አየር የሚቆጠሩ ነበሩና:: የሁሉንም ዓይነት መንፈሳዊ ሕይወት ፍሬዎችን የለቀመው ከእነዚህ ብሂሎች ነው» ይላል::

በልዩ ልዩ ዘጋቢዎች የተሰበሰው ብሂል 127 አበው እና እማት የተናገሯቸውን 1202 ብሂሎች የያዘ ነው:: ከእነዚህ መካከል የተወሰኑትን ብቻ በዚህ መጽሐፍ አቅርበናቸዋል::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከመጽሐፈ መነኩሳት በተጨማሪ የሚከተሉትን መጻሕፍት በምንጭነት ተጠቅመናል:: (In the Heart of The desert Fathers (John chryssavigs: 2003), The Sayings of the Desert Fathers (Benedicta word, 1997)

## መግቢያ

ከሦስተኛው እስከ አምስተኛው መ/ክ/ዘ ያለው ጊዜ ምናኔ፣ ምንኩስናና ገዳማዊ ኑሮ በግብፅ በሶርያ፣ በፍልስጥኤምና በሊባኖስ በረሓዎች የተስፋፋበት ዘመን ነበር:: የምንኩስና ዋና ማዕከል ግብፅ ነበረች:: በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካና በረሓዎች የተስፋፋውን መልአካዊ ሕይወት ለመሳተፍ ከምዕራብና ከምሥራቅ ብዙዎች የነገሥታቱን ቤት፣ የተሰጣቸውን መዓርግና ሥልጣን፣ ያካበቱትን ሀብትና ንብረት እንዲሁም የደከሙበትን የዘመኑን ዕውቀት ትተው ወደ ግብፅ ይወርዱ ነበር::

ግብፅ በዚያ ጊዜ ሥርዓተ ምንኩስና እና የምናኔ ሕይወት የተስፋፋባቸው ሦስት ዋና ዋና ቦታዎች ነበሯት::

*1. ታሕታይ ግብፅ - የተባሕትዎ ምንኩስና ኑሮ፡-* የዚህ ሕይወት መሥራቹ ቅዱስ እንጦንስ ነው:: አባ እንጦንስ የሀብታም ገበሬ ልጅ ሲሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን መሔድን ያዘወትር ነበር:: አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያለ «ሒድና ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድኾች ስጥና ተከተለኝ» የሚለውን የወንጌል ትእዛዝ ሰማ:: ወዲያው የዚህን ዓለም ኑሮ ትቶ በ270/71 ዓ.ም መነነ:: ይህቺን ቀን በተመለከተ ዮሐንስ ክሪስቫጊስ የተባለ ግሪካዊ ፕሮፌሰር «ክርስቲያናዊ ገዳማዊ ኑሮ 270/71 ዓ.ም. በአንድ እሑድ ጠዋት በአንዲት ትንሽ የግብፅ መንደር ተወጠነ» ብሏል::(In the Heart of the Desert.2003 p.15) ቀስ በቀስ ወደ በረሓው እየራቀ ገባ:: በአንድ ተራራ ውስጥም በብሕትውና ከቆየ በኋላ በ365 ዓ.ም. በ105 ዓመት ዕድሜው ዐረፈ:: «አበ መነኰሳት» የተባለው አባ እንጦንስ ብዙ አርድእትንና መንገዱን የተከተሉ ብዙ ትውልድ አፍርቷል::

*2. ላዕላይ ግብፅ - የመነኮሳት አንድነት ገዳም፡-* የዚህ ዓይነቱ ሕይወት መሥራቹ አባ ጳኩሚስ (292-346) ዓም ነው:: አስቀድሞ በሮም ሠራዊት ውስጥ ያገለግል የነበረው ጳኩሚስ ታስሮ በነበረ ጊዜ ክርስቲያኖች ያደረጉለትን የልግሥና ሥራ ተመልክቶ ልቡ ተነካ:: ከዚያ በኋላ ባለው ነገር ሁሉ የሰውን ዘር ሊያገለግል ቃል ገባ:: ከውትድርና ሲሰናበት ክርስትናን ተቀብሎ ተጠመቀና ለሦስት ዓመታት ማኅበራዊ አገልግሎት ሰጠ:: በኋላም ከሼኔሴት ከተማ ራቅ ብሎ በምናኔ ይኖር የነበረው የአባ ጳልሞን ደቀ መዝሙር ሆነ:: ከእርሱ ጋር ሰባት ዓመት







ገዳመ አስቄጥስ አሁን ባለበት ይዞታ

ከኖረና ሥርዓተ ምናኔን ከተማረ በኋላ ታቤኔህ ወደ ምትባል ቦታ በምናኔ ተጓዘ:: በዚያ የምናኔን ኑሮ በመኖር ላይ እያለ ብዙ ወንዶችና ሴቶች መናንያን በዙሪያው ተሰባሰቡ:: እርሱም የጋራ ሥራ፣ የጋራ ማዕድ፣ የጋራ ጸሎት ሕግጋትን አወጣ::

*3. ንጥራ እና አስቄጥስ - ማኅበረ መናንያን፡- በግብፅ* ከዓባይ ወንዝ በስተ ምዕራብ እና በንጥራ በስተደቡብ 40 ማይልስ ርቀት ላይ በሚገኘው አስቄጥስ ሦስተኛው ዓይነት የምናኔ ሕይወት ተስፋፍቶ ነበር:: መነኰሳት በማኅበር እየሆኑ በአንድ አበ ምኔት ሥር ይተዳደሩ ነበር:: ንጥራ ከእስክንድርያ ከተማ አጠገብ ስለነበር ለአስቄስጥስ የመገናኛ ድልድይ ነበር:: የውጭው ዓለምና የገዳመ አስቄስጥስ የመገናኛ በሩ ንጥራ ነበር:: ዮሐንስ ናስያንን የመሰለ ጐብኝዎች መጀመሪያ የመጡት ወደ ንጥራ ነበር::

ከግብፅ በተጨማሪ በመካከለኛው ምሥራቅ ሦስት ቦታዎች ሥርዓተ



በግብፅ በረሓ የዓባይን ወንዝ ተከትለው የተተከሉ ገዳማት ካርታ





ምንኩስና ተስፋፍቶባቸው ነበር።

*ሶርያ፦* በኤዴሳ እና በአንጾኪያ ዙርያ በተለይም በቱር አብዲን ተራራ ላይ ልዩ የሆነ የምናኔ ሕይወት ተስፋፍቶ ነበር፡ ሶርያውያን መነኮስት በየግል መኖርንና ከባድ የሆነ ቀንበር በራሳቸው ላይ መጫንን ያዘወትሩ ነበር። ራቁታቸውን ሆነው በሠንሠለት ታስረው መዘዋወር፣ በጫካ ውስጥ ያገኙትን መመገብ፣ ልማዳቸው ነበር። የሚኖሩት ሰው ሊቀበለው የሚችለውን የመጨረሻውን ከባድ ኑሮ ነበር። ለአራዊት፣ ለቅዱሳን መላእክትና ለፀብአ አጋንንት ቅርብ ነበሩ። በተለይም በአምስተኛው መ/ክ/ዘ ታዋቂ የሆኑትና «ዓምደኞች» ተብለው የሚታወቁት ለዚህ ማሳያ ናቸው። እነዚህ መናንያን በአንድ ዓምድ ጫፍ ላይ ለረዥም ዘመን ጸንተው ይኖሩ ነበር። የዚህ ዓይነቱ ምናኔ ጀማሪ «ስምዖን ዘዓምድ» ይባላል። ስምዖን ዘዓምድ ከአንጾኪያ ወጣ ብሎ በአንድ ዓምድ ላይ 40 ዓመት ኖሮአል። ከእነዚህ የምንኩስና ማዕከላት የተወሰኑ ታሪኮች ብቻ ተዘግበዋል።

*ታናሽ እስያ፦* በቀጰዶቅያ አካባቢ ትምህርትን መሠረት ያደረገ ሥርዓተ ምንኩስና ተመሥርቶ ነበር። በዚህ አካባቢ በከተሞች ውስጥና ከከተሞች ውጭ ገዳማት ነበሩ። ለቀጰዶቅያ ሥርዓተ ምንኩስና ዋና ፈር ቀዳጁ ታላቁ ባስልዮስ (330-379)ዓ.ም. ነው።

*ፍልስጥኤም፦* በአምስተኛው መ/ክ/ዘ ዋነኛው ገዳማዊ ሕይወት የተስፋፋው በፍልስጥኤም በረሓዎች ነበር። በዮርዳኖስ በረሓ በተለይም በጋዛ በረሓ የግብፅን ሥርዓት ተከትለው የሚኖሩ አያሌ መናንያን ነበሩ። የእነዚህ ገዳማት አበው ታሪኮችና ንግግሮች በስፋት ተዘግበዋል።

ከእነዚህ አበው ሕይወት የተገኘው ትምህርት የምንኩስና ጉዞ ለጀመሩም ሆነ በዓለም ውስጥ ሆነው ከሰይጣን ጋር ለሚጋደሉ ክርስቲያኖች ትምህርት ሰጭ፣ የድኅነት መንገድ አመልካችና ራስን የመፈተሻ መሣሪያም ነው። ከአጋንንት ጋር ያላቸው ውጊያ፣ ለኃጢአት እጅ ላለመስጠት የሚያደርጉት ተጋድሎ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ቀረቤታ የሚያስቀናና ምነው አብሬያቸው በሆንኩ የሚያሰኝ ነው። ምድራውያን መላእክት ሆነው፣ የዚህን ዓለም ጣጣ ፍጹም ትተው፣ የሥጋ ፈቃድን ድል ነሥተው ያሳዩን የኑሮ መሥመር እስከ ዓለም ፍጻሜ ሕያው ትምህርት ነው።

# አርሳንዮስ[1]

1. አባ አርሳንዮስ በቤተ መንግሥት በነበረበት ሰዓት «ጌታ ሆይ በድኅነት ጐዳና ምራኝ» እያለ ይጸልይ ነበር። እናም «አርሳንዮስ» ሆይ ከሰዎች ተለይ ያን ጊዜ ድኅነትን ታገኛለህ» የሚል ድምጽ ሰማ። ወዲያውም ቤተ መንግሥቱን ትቶ ወደ ገዳም ገባ።

2. ወደ ምናኔ ሕይወት ከገባም በኋላ ከቀድሞው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጸሎት ይጸልይ ነበር። ያን ጊዜም ከሰማይ የመጣ ድምጽ «አርሳንዮስ ሆይ ሽሽና በአርምሞ ኑር፤ ዘወትር ጸልይ፤ እነዚህ የንጽሕና መገኛዎች ናቸውና» ሲል ተናገረው።

3. አባ አርሳንዮስ በበኣቱ እያለ አጋንንት መጥተው ያውኩት ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ከሔዱበት ተመልሰው ከበአቱ ደጅ ሲደርሱ እንዲህ እያለ ሲጸልይ ሰሙት፤ «እግዚአብሔር ሆይ አትተወኝ፤ በፊትህ መልካም የሚሆን ምንም ምግባር የለኝም። ነገር ግን ስለ ቸርነትህ ስትል መልካምን ነገር እንዴት እንደምጀምረው ግለጥልኝ»።

4. አንድ ጊዜ አባ አርሳንዮስ በኀሊናው እየተመላለሱ ስለሚያስቸግሩት ክፉ ሐሳቦች አንድን አረጋዊ የግብፅ መነኩሴ ሲያማክረው አንድ ሌላ ወጣኒ መነኩሴ ተመለከተው። ያም መነኩሴ በጣም ተደንቆ «አባ አርሳንዮስ ሆይ በላቲንና በግሪክ ትምህርት የበሰልክ አንተን የመሰልክ ሊቅ ይህንን ማይም ገበሬ እንዴት ስለ ፈተናህ ትጠይቀዋለህ?» አለው። አባ አርሳንዮስም «በርግጥ ላቲንና ግሪክ በሚገባ ተምሬያለሁ፤ ነገር ግን የዚህን ገበሬ መንፈሳዊ የፊደል ገበታ ገና አላወቅሁትም» ሲል መለሰለት።

5. አባ አርሳንዮስ እንዲህ ብሎ ነበር፤«እግዚአብሔርን ከፈለግነው ራሱን ይገልጥልናል፤አጥብቀን ከያዝነውም ከእኛ ጋር አብሮ ይኖራል።።»

6. አባ ማርቆስ አባ አርሳንዮስን «ለምን ከኛ ትርቃለህ? ሲል ጠየቀው። አባ አርሳንዮስም፤ «እንደምወዳችሁ እግዚአብሔር ያውቃል፤ ነገር ግን ከሰዎችም ከእግዚአብሔርም ጋር በአንድ ላይ መኖር አልችልም። እልፍ አእላፋት መላእክት በአንድ ቦታ ቢኖሩም ሐሳባቸው ግን አንድ ነው። ሰዎች ግን ሐሳባቸው በቁጥራቸው ልክ ብዙ ነው። ስለሆነም ከሰው

1 አባ አርሳንዮስ በ360 ዓ.ም በሮም ተወለደ። በዘመኑ ትምህርት በሚገባ የተማረና ለሴናተርነትም መዓርግ የደረሰ ሰው ነበር። የሮሙ ንጉሥ ቴዎዶስየስ ለልዕልት አርቃድዮስ እና ለልዕልት አኖሬዎስ መምህር አድርጎ መድቦት ነበር። በ394 ዓ.ም የሮምን ቤተ መንግሥት ንቆ ትቶ በድብቅ ወደ እስክንድርያ መጣ። በመቀጠልም ወደ ገዳመ አስቄጥስ ገብቶ የአባ ዮሐንስ ሐጺር ደቀ መዝሙር ሆነ። በገዳመ አስቄጥስ አጠገብ በሚገኘው በጴጥራ በምናኔ ይኖር ጀመር። የታወቁ ሦስት ደቀ መዛሙርት ነበሩት፡- እስክንድር፣ ዞይለስ እና ዳንኤል። ድሎት የለሽ ኑሮን በመኖር እና በአርምሞው የታወቀ አባት ነው። በ434 ዓ.ም ገዳመ አስቄጥስ ለሁለተኛ ጊዜ ከጠፋ በኋላ ወደ ትሮኤ ተራራ ወጣ፤ እዚያም በ449 ዓ.ም ዐረፈ።








አባ አርሳንዮስ ታላቁ ቦስተን- ከሚገኘው የደብረ ታቦር ( Hloy Transfiguration Monastry ) ገዳም የተገኘ ሥዕል

አባ አርሳንዮስ ታላቁ፤ ቦስተን ከሚገኘው የደብረ ታቦር ገዳም የተገኘ

ጋር ለመኖር ስል እግዚአብሔርን መተው አልሻም» አለው።

7. አባ አርሳንዮስ «በተጋድሎ ውስጥ ለሚገኝ መነኩሴ የአንድ ሰዓት ዕንቅልፍ በቂ ነው» ይል ነበር።

8. በዕለተ ዓርብ ምሽት፣ ለታላቁ ሰንበት ለመዘጋጀት ሲል፣ ጀርባውን ለፀሐይዋ ሰጥቶ እጆቹን በመዘርጋት ወደ ሰማያት ያለ ማቋረጥ ይጸልያል። የሚያርፈው ፀሐይ በፊት ለፊት በኩል ብርሃንዋን መር ጨት ስትጀምር በቀጣዩ ቀን ነው።

9. አባ ዳዊት አንድ ጊዜ አርሳንዮስ የነገራቸውን ታሪክ እንዲህ ያወጉናል። «እርግጥ አባ አርሳንዮስ ይህንን ታሪክ የተናገረው ሌላ ሰው አደረገው ብሎ ነው። በርግጥ ግን የታሪኩ ባለቤት እርሱ ራሱ ነው። አንድ አረጋዊ መነኩሴ ከበአቱ ወጥቶ ሳለ «የሰው ልጆችን ሥራ አሳይህ ዘንድ ና» የሚል ድምፅ ሰማ። እርሱም ከበአቱ ወጥቶ የጠራውን ድምፅ ተከትሎ ተጓዘ። ያ ድምፅ ወደ አንድ ቦታ አደረሰውና አንድ አትዮጵያዊ እንጨት እየፈለጠ ሲከምር አሳየው። ያ እንጨት የሚፈልጥ ኢትዮጵያዊ ሊሸከመው ሞከረና አቃተው፤ ይሁን እንጂ በመቀነስ ፋንታ አሁንም እየቆረጠ መከመር ቀጠለ። ጥቂት አለፍ ብሎ ደግሞ አንድ ሰው በሐይቅ አጠገብ ቆሞ በተሰበረ ማሠሮ ውኃ ሲቀዳ ተመለከተ። ማሠሮው የተሰበረ በመሆኑ ውኃው እንደገና ወደ ሐይቁ ይመለስ ነበር። ያ ድምጽ በድጋሚ «ና ሌላ ነገር ደግሞ አሳይሃለሁ» ብሎ ወሰደው።

በአንድ ሥፍራ ላይ መቅደስ አሳየው። ሁለት ሰዎች በፈረስ ጐን ለጐን ሆነው መጡ። በትከሻቸውም በትራቸውን ጫፍና ጫፍ ላይ አጋድመው ይዘውት ነበር። በበሩ ወደ ውስጥ ሊያልፉ ቢፈልጉም በትራቸውን አግድም ስለያዙት ያግዳቸው ነበር። አንዳቸውም ከሌላኛው ኋላ በመሆን በትሩን ፊትና ኋላ አድርገው ሊገቡ አልፈለጉም። ስለዚህም በፉክክር ከውጭ ቀሩ። ያ ድምጽ ለዚያ አረጋዊ አባት እንዲህ አለው።«እነዚህ ሰዎች የጽድቅን ቀንበር በትዕቢት ተሸክመውታል፣ ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ አላደረጉም፤ ራሳቸውን ለማረምና በክርስቶስ የትኅትና ጉዞ ለመጓዝ አልፈለጉም፣ ስለዚህም ከመንግሥተ ሰማያት በአፍአ ይቀራሉ። እንጨት የሚቆርጠው ሰውም በኃጢአት ላይ ኃጢአት የሚጨምርን ሰው ይመስ ላል። ንስሐ ከመግባት ይልቅ ሌሎች ኃጢአቶችን እንደገና ይጨምራል። ውኃ የሚቀዳውም ሰው መልካም ሥራን የሚሠራ ሰውን ይመስላል፣ ነገር ግን መልካም ሥራው ከክፉ ሥራው ጋር የተቀላቀለ በመሆኑ ጥቂቱ መልካም ሥራው ይበላሽበታል፣ ስለሆነም እያንዳንዱ ለሚሠራው ነገር ሊጠነቀቅና በከንቱ እንዳይደክም ሊያስብበት ይገባል» አለው።







በትከሻቸውም በትራቸውን ጫፍና ጫፍ ላይ አጋድመው ይዘውት ነበር። በበሩ ወደ ውስጥ ሊያልፉ ቢፈልጉም በትራቸውን አግድም ስለያዙት ያግዳቸው ነበር።

# አባ አጋቶን[2]

1. የአባ ሎጥ ደቀ መዝሙር አባ ጴጥሮስ ስለ አባ አጋቶን እንዲህ ብሏል:: «አንድ ጊዜ በአባ አጋቶን በአት እያለሁ አንድ ወንድም መጣና አባ አጋቶንን «ከወንድሞች ጋር መኖር እሻ ነበር፤ እስቲ እንዴት አብሬያቸው መኖር እንዳለብኝ ምከረኝ?» ሲል ጠየቀው:: አባ አጋቶንም «በኑሮህ ሁሉ የእንግዳ ሰው ዓይነት ልቡና ይኑርህ፤ ልክ በመጀመሪያ ያገኘሃቸው ቀን የምትሆነውን ዓይነት:: በጣምም አትቅረባቸው፣ በጣምም አት ራቃቸው::» አለው:: በዚህ ጊዜ አባ መቃርዮስ «ይህ መቀራረብ ምን ያስ ከትላል?» ሲል ጠየቀው:: አባ አጋቶንም «ያማ እንደ ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ ያለ ነው፤ ሊንሳፈፍ የሚችለውን ሁሉ እያነሣ የዛፎችን ፍሬ ያበላሽ ባቸዋል»:: አባ መቃርዮስም «ያለ መጠን መናገር ይህን ያህል ይጐዳል እንዴ?» ብሎ ጠየቀ:: አባ አጋቶንም «የማይቆጣጠሩትን ምላስ ያህል መጥፎ ፆር የለም፤ እርሷ የፈተና ሁሉ እናት ናት:: ስለሆነም እውነተኛ የሥራ ሰው አይጠቀምባትም፤ አንዲት ትንሽ አልጋ የነበረችው አንድ ወንድም አውቃለሁ፤እርሱ በበአቱ ለረዥም ዘመናት ከኖረ በኋላ «ያችን ትንሽ አልጋ ሳልጠቀምባት ከበአቴ ወጣሁ፣ምክንያቱም እዚያ መኖርዋን የነገረኝ ሰው አልነበረምና» ይል ነበር:: ጠንካራ መነኩሴ ማለት ተዋጊ ነው::

2. እኔ ማንንም አሳዝኜ ወደ መኝታዬ ገብቼ አላውቅም፣ ማንንም ቢሆን አሳዝኖኝ ወደ መኝታው እንዲሔድም አልተወውም::

3. አንድ ጊዜ ስለ አባ አጋቶን ትኅትና የሰሙ መነኰሳት ሊያዩት መጡ:: የቁጣ ስሜቱን መተውንና አለመተውን ለማረጋገጥ ብለው «አመንዝራውና ትዕቢተኛው አጋቶን ማለት አንተ ነህ?» አሉት:: አባ አጋቶንም «አዎ ትክክል ነው» አላቸው:: ቀጥለውም «ፍሬ የሌለው ነገር ዘወትር የምታወራ አጋቶን ማለት አንተ ነህን?» አሉት «አዎ ነኝ» አላቸው:: «መናፍቅ አጋቶን ማለት አንተ አይደለህምን?» ሲሉ ጠየቁት፤ ያን ጊዜ ግን «መናፍቅስ አይደለሁም» ሲል መለሰላቸው:: በዚህ ጊዜ «እስካሁን የተናገርንብህን ሁሉ ተቀብለህ የመጨረሻውን ለምን ተቃወምክ?» አሉት:: አባ አጋቶንም «የመጀመሪያዎቹን

2 አጋቶን ወደ ቲቢያድ ገዳም ሲመጣ ገና ሕፃን ነበር:: ያሳደገውና ያስተማረው አባ ጴሜን ነው:: በመቀጠልም ወደ አስቄጥስ ተጉዞ ከአባ እስክንድር እና ዞይለስ ጋር ለጥቂት ጊዜ ኖሯል:: ገዳመ አስቄጥስ ለመጀመርያ ጊዜ ሲጠፋ አባ አጋቶን ከደቀ መዝሙሩ ከአባ አብርሃም ጋር በመሆን ከደብረ ትሮኤ ሳይርቅ ከዓባይ ወንዝ አጠገብ መኖር ጀመረ::





ወቀሳዎች ለነፍሴ ተስማሚዎች ናቸውና ተቀበልኳቸው:: ኑፋቄ ግን ከእግ ዚአብሔር መለየት ነው፤ እናም እኔ ከፈጣሪዬ መለየት አልፈልግም አላቸው::»በዚህ የተነሣም የርሱ ሕይወት አስደነቃቸው::

4. አንድ ጊዜ አባ አጋቶንን «በአፍአ የሚታይ ምናኔ ይሻላል ወይስ በውስጥ የሚገኝ የነቃ ልቡና ይሻላል» ብለው ጠየቁት:: እርሱም «ሰው ማለት ዛፍ ነው:: አፍአዊ ምናኔ ቅጠል፣ የልቡና ንቃት ግን ፍሬ ነው:: ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል /ማቴ.3÷10/ ተብሎ እንደተገለጠው ድካማችን ሁሉ ውሳጣዊውን ፍሬ ለማፍራት መሆን አለበት:: ያም ነፍስን መጠበቅ ነው:: ይህ ግን የቅጠልን ከለላና ጌጥ ይፈልጋል:: ያም አፍአዊ ምናኔ ነው» ሲል መለሰላቸው::»

5. አባ አጋቶንን በሌሎች ላይ እንዲፈርድ የሚያነሣሣ ሐሳብ ሲመጣበት «አጋቶን ሆይ ይህ ያንተ ተግባር አይደለም» እያለ ራሱን ይገስፀው ነበር::

6. «ቁጡ ሰው ምንም እንኳን ሙት የማስነሣት ችሎታ ቢኖረው በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ተቀባይነት የለውም» ይል ነበር::

7. አንድ ሰው ለእኔ በጣም ወዳጄ ቢሆን፣ ነገር ግን እምብዛም ወደ ማይረባ ተግባር እየመራኝ ከሆነ እርሱን ከኔ አርቀዋለሁ::

8. አንድ ቀን አባ አጋቶን በእጁ የሠራቸውን ነገሮች ለመሸጥ ወደ ገበያ ሲወጣ በመንገድ ዳር አንድ ሽባ ሰው አገኘ:: ሽባውም የት እንደ ሚሔድ አባ አጋቶንን ጠየቀው:: «አንዳንድ ነገሮች ለመሸጥ ወደ ገበያ እሔዳለሁ» አለው:: ሽባው ሰውም «እባክህ ተሸክመህ ወደዚያ ውሰደኝ» ሲል ለመነው:: አባ አጋቶንም ያንን ሰው ተሸክሞ ወደ ከተማ ወሰደው:: ሽባው ሰውዬ «ዕቃዎችህን ከምትሸጥበት ቦታ አጠገብ አኑረኝ» አለው:: አባ አጋቶንም እንደዚያው አደረገው::

አባ አጋቶን የመጀመሪያውን ዕቃ ሲሸጥ «ምን ያህል ሸጥከው?» ብሎ ሽባው ሰው ጠየቀው:: እርሱም ዋጋውን ነገረው:: ያም ሽባ ሰው «እባክህ ዳቦ ግዛልኝ» ሲል ለመነውና ገዛለት:: አባ አጋቶን ሁለተኛውን ዕቃ ሲሸጥ «ምን ያህል ሸጥከው» ሲል ያ ሰው ጠየቀው:: እርሱም ዋጋውን ነገረው:: «እባክህ ይህን ነገር ግዛልኝ» ሲል ለመነው:: አባ አጋቶንም ገዛለት:: በዚህ መልኩ ሁሉንም ዕቃዎች ሸጦ በጨረሰ ጊዜ ያ ሽባ ሰው «ወደ በአትህ ትመለሳለህን?» ሲል ጠየቀው «አዎ»:: «እንግዲያው እባክህ ቀድሞ ወዳገኘኸኝ ሥፍራ አዝለህ መልሰኝ» አለው:: አባ አጋቶንም ያን



አባ አጋቶንም ያንን ሰው ተሸክሞ ወደ ከተማ ወሰደው:: ሽባው ሰውዩ <<ዕቃዎችህን ከምትሸጥበት ቦታ አጠገብ አኑረኝ>> አለው:: አባ አጋቶንም እንደዚያው አደረገው::





ሽባ ሰው ተሸክሞ ወደ ቀድሞ ቦታው መለሰው:: በዚህ ጊዜ ሽባው ሰው «አባ አጋቶን በሰማይና በምድር በረከት ተሞላህ» ብሎ ተናገረው:: ወዲያው አባ አጋቶን ዓይኑን አንሥቶ ሽባውን ቢያየው በቦታው የለም:: ሊፈትነው ይህን ያደረገው መልአከ እግዚአብሔር ነበር::

9. «ጠባቡና ከባዱ በር የትኛው ነው»ማቴ.7÷14 ተብሎ በተጠየቀ ጊዜ አባ አጋቶን እንዲህ አለ «ልቡናን መቆጣጠር፣ ራስንም ለእግዚአብሔር ሲሉ ከመሻቱ ማራቅት ነው:: እኛ ሁሉን ትተን ተከተልን» የተባለው ትርጉም ይህ ነው /ማቴ.19÷27/::

# አባ አብርሃም

1. ለ15 ዓመታት ጳቦ ተመግቦ ወይን ጠጥቶ የማያውቅ አንድ ተሐራሚ አረጋዊ ነበር:: እርሱም «ፈተናውን አጥፍቼዋለሁ፣ ስስትና ከንቱ ውዳሴም በኔ ውስጥ የሉም» ይል ነበር:: ይህንን የሰማው አባ አብርሃም ወደ አረጋዊው መጣና «በእውነት እንዲህ ብለሃልን?» ሲል ጠየቀው:: «አዎን» አለ:: «ለመሆኑ አንዲት ሴት በበአትህ ውስጥ በምንጣፍህ ላይ ተኝታ ብታገኛት ልክ ሴት እንዳልሆነች አድርገህ ማሰብ ትችላለህን?» ሲል ጠየቀው:: «አልችልም ነገር ግን እርሷን ላለመንካት ከልቡናዬ ጋር እታገላለሁ» አለው::

አባ አብርሃምም «ምንም እንኳን ልትቆጣጠረው ብትችል ፈቲው ግን ባንተ ውስጥ አልጠፋልህም፤ አሁንም አለ ማለት ነው» አለው:: ቀጥሎም «በመንገድህ ላይ ከድንጋይ መካከል ወርቅ ብትመለከት ወርቁን የድንጋዩን ያህል ቆጥረህ ሳታየው ታልፋለህን» ሲል ጠየቀው:: ያም አረጋዊ «አላልፈውም፣ ነገር ግን ወርቁን ላለመንካት ከራሴ ጋር እጋደላለሁ» አለው:: «አየህ መንፈስ ስስት አልጠፋልህም ማለት ነው፤ ተቆጣጠርከው እንጂ» ሲል መለሰለት:: ከዚያም «ከሁለት ወንድሞች መካከል አንዱ እንደሚወድህ፣ ሌላው ግን እንደሚጠላህና ስላንተም ክፉ ነገር እንደሚናገር ዐወቅክ እንበል፤ ሁለቱም አንተን ለመጎብኘት ቢመጡ በእኩል ዓይን ትቀበላቸዋለህን?» ሲል አባ አብርሃም አረጋዊውን ጠየቀው:: አረጋዊውም «አልቀበላቸውም፤ ነገር ግን የሚጠላኝን ሰው ላለማሳዘንና ለእርሱም መልካም እሆንለት ዘንድ ከልቡናዬ ጋር እታገላለሁ» አለው:: «በዚህ መንገድ» አለ አባ አብርሃም «ፆር አልጠፋልህም፤ ነገር ግን ቅዱሳን ያንን ፆር መቆጣጠር ስለሚችሉ ነው» ሲል ተናገረ::

# አባ ገላስዮስ[3]

አባ ገላስዮስ አንድ የብራና መጽሐፍ ቅዱስ ነበረው:: ዋጋውም 18 ብር ነበር:: የሚፈልግ ሁሉ ያነብበው ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቀምጦት ነበር:: አንድ ጊዜ አንድ ሰው አባ ገላስዮስን ሊጠይቅ መጣና መጽሐፍ ቅዱሱን ተመለከተው:: ሲመለስም መጽሐፍ ቅዱሱን ሰርቆ ሔደ:: አባ ገላስዮስ የሆነውን ነገር ቢያውቅም ሊያስመልሰው ግን አልወደደም:: ያም ሰው ወደ ከተማ ወጣና ሊሸጠው ወደደ:: አንድ ገዥ አግኝቶም በ13 ብር ዋጋ ተስማማ::

«ያ ገዥም መጀመርያ ስጠኝ በትክክል የተጻፈ መሆኑን መር ምሬ ነገ ዋጋህን እከፍልሃለሁ» ሲል አሰናበተው:: ገዥውም መጽሐፍ ቅዱሱን ይዞ ወደ አባ ገላስዮስ መጣና «አንድ ሰው በ13 ብር ይህን መጽሐፍ ሊሸጥለኝ ተስማማ፤ ልግዛውን?» ሲል ጠየቀው አባ ገላስዮስም «አዎ ርካሽ ነው፤ መጽሐፉም ጥሩ ነው ግዛው» አለው:: ወደ ሻጩ መጣና «መጽሐፉን ለአባ ገላስዮስ አሳየሁት፤ እርሱም ዋጋው ውድ ነው:: መጽሐፉ ያንን ያህል አያወጣም አለኝ» ብሎ ተናገረው::

በዚህ ጊዜ ሻጩ «ሌላ ምንም አላለህም» ሲል ጠየቀው:: «ምንም አላለኝም» ሲል መለሰለት:: በዚህ ጊዜ ሻጩ «ልሸጠው አልፈልግም» አለና ልቡ ተነክቶ በፀፀት ወደ አባ ገላስዮስ አመራ:: አባ ገላስዮስንም «እባክህን መጽሐፍህን እንደ ገና ተቀበለኝ፤ ኃጢአቴንም ይቅር በለኝ» ብሎ ለመነው:: አባ ግን እሺ አላለውም:: ያም ሰው «መጽሐፍህን ካልወሰድክ በሰላም መኖር አይቻለኝም» አለው:: አባ ገላስዮስም «ሰላ ምን ካገኘህስ መልሼ እወስደ ዋለሁ» ብሎ ተቀበለው:: ያም ሰው ገስሐ ገብቶ እስከ ዕለተ ሞቱ አባ ገላስዮስን አገለገለው::

3 አባ ገላስዮስ የምናኔን ኑሮ የጀመረው ግብፅ ውስጥ ነው:: በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የናይሎፖሊስ ገዳም አበ ምኔት ሆኖ ነበር::





# አባ ኤጲፋንዮስ[4]

1. «ከነዓናዊቷ ሴት ጮኸች፤ ጩኸቷም ተሰማ(ማቴ.15)፤ ደም ይፈስሳት የነበረችው ሴት ምንም ቃል አልተነፈሰችም ነበር፤ ነገር ግን ብፅዕት ተባለች (ሉቃ.8÷43)፤ ፈሪሳዊው ብዙ ተናገረ፤ ነገር ግን ተወቀሰ (ማቴ.9÷10)፤ ቀራጩ ግን አፉን አልከፈተም፤ ነገር ግን ጸሎቱ ተሰማ (ሉቃ.18÷9)::

2. ነቢዩ ዳዊት በምሽት፣በእኩለ ሌሊት፣በነግህ፣በሠርክ፣በእግዚአ ብሔር ፊት ይቆም ነበር:: በጠዋት በእኩለ ቀንም እንዲሁ:: «በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ»(መዝ.118÷164)በማለት የተናገረው ለዚህ ነው::

3. ለሚጠቀሙባቸው ሰዎች የክርስትና መጻሕፍትን ገንዘብ ማድረግ መልካም ነው:: እነዚህን መጻሕፍት አብዝተን በተመለከትን ቁጥር ወደ ኃጢአት ማዘንበላችን ይቀንሳል:: በእምነት ጸንተን ጽድቅንም የበለጠ እንፈጽም ዘንድ ያነቃቁናል::

4. ሐዲሳት መጻሕፍትን ማንበብ ከኃጢአት ፍላጻ የመደበቂያ ጽኑ መከላከያ ነው::

5. ቅዱሳት መጻሕፍትን አለማወቅ በዘቀትና በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ መኖር ነው::

6. የጻድቃን በደል በአንደበታቸው ነው፤ የኃጥአን በደል ግን በመላ ሰውነታቸው ነው:: ልበ አምላክ ዳዊት «ለአፌ ጠባቂ አኑር» ያለው ለዚህ ነው መዝ.141÷3 እንዲሁም «በአንደበቴ መንገዴን እጠብቃለሁ» ብሏል::

7. አንድ ሰው ኤጲፋንዮስን የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማብረድ አንድ ጻድቅ ብቻ በቂ ነውን? ሲል ጠየቀው:: ኤጲፋንዮስም «ርግጥ ነው፤ እርሱ ራሱ ፍርድን የሚያደርግ እውነትንም የሚሻውን ሰው ታገኙ እንደሆነ ይቅር እላታለሁ» (ኤር.5÷1) ብሏል ሲል መለሰ::

8. እግዚአብሔር ጽድቅን ሊገዙ ለሚፈልጉ ሁሉ በርካሽ ዋጋ ሸጠ ው:: በቁራሽ እንጀራ፤ በእራፊ ጨርቅ፤ በአንዲት ኩባያ ቀዝቃዛ ውኃ፤ እንዲሁም በድቃቂ ሳንቲም::

*4 የቆጵሮስ ሊቀ ጳጳስ አባ ኤጲፋንዮስ (315- 403 ዓ.ም) የተወለደው በፍልስጥኤም ሲሆን ገዳማዊ ሕይወትን የተማረው ደግሞ ግብፅ ውስጥ የአባ ሂላርዮን ደቀ መዝሙር ሆኖ ነው:: እርሱ የመሠረተው ገዳም በጋዛና በኢየሩሳሌም መካከል በኤሌትሮፖሊስ ይገኝ የነበረው ገዳም ነው:: አባ ኤጲፋንዮስ የአርጌንስን ኑፋቄ በብርቱ ከተቃወሙት አበው አንዱ ነው:: ብዙ ዘመኑን በንባብ እና በጽሑፍ አሳልፏል::*

# አባ ኤፍሬም ሶርያዊ[5]

1. አባ ኤፍሬም ሕፃን እያለ እንዲህ የሚል ራእይ አየ። የወይን ቅርንጫፍ ከአፉ ወጥቶ እጅግ ታላቅ ሆነ፣ ከሰማይ በታች ያለውንም ሸፈነው። ውብ የሆነ ፍሬም አፈራ። የሰማይ ወፎች ሁሉ ከዚያ ፍሬ ለመብላት ይመጡ ነበር። በተመገቡት ቁጥርም ፍሬው ይበልጥ እየተ ንዠረገገ ይሔድ ነበር።

2. በሌላ ጊዜ ደግሞ ቅዱሳን አንድ ራእይ ተመለከቱ። በእግዚ አብሔር ታዝዘው ብዙ መላእክት ወደ ምድር ወረዱ። በእጃቸውም በብራና ላይ የተጻፈ ጽሑፍ ይዘው ነበር። «ይህን ለማን እንስጠው?» በማለት ተናገሩ። አንዱ ለእገሌ ሌላውም ለእገሌ አለ። በመካከል ግን «በርግጥ ሁሉም ቅዱሳን ናቸው፣ ከአባ ኤፍሬም በላይ ግን ይህንን ሊቀበል የሚችል የለም» የሚል ድምፅ መጣ። አንድ አረጋዊ ቅዱስም ያ ፓፒረስ ለአባ ኤፍሬም ሲሰጥ ተመለከተ። ከአባ ኤፍሬም አንደ በትም እንደ ፏፏቴ ሆኖ ሲወርድ አየ። በዚህም ከአባ ኤፍሬም አንደ በት የሚወጣው ነገር ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ መሆኑን ተረዳ።

3. አንዲት ዘማ አባ ኤፍሬምን ከመንገድ ጠብቃ በዝሙት ቃላት ተናግራ ታሳፍረው ዘንድ ጀመረች። ምንም እንኳን አባ ኤፍሬምን በዝሙት ለመጣል ቢያቅታት ሲቆጣ ለማየት ግን ጓጓች። እርሱ በሕ ይወቱ ሲቆጣ ያየው አንድም ሰው አልነበረምና። አባ ኤፍሬምም «ተከተይኝ» አላት። ብዙ ሕዝብ ወደ ተሰበሰበበት ሥፍራ በደረሱ ጊ ዜም «በይ በዚህ ቦታ የምትፈልጊውን ነገር እንፈጽም» አላት። ዘማ ዋም «በዚህ ሁሉ ሕዝብ መካከል ይህን ነገር ስንፈጽም አናፍርምን?» ስትል ጠየቀችው። እርሱም «በሰው ፊት ከፈራን በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል ማፈር ይኖርብን ይሆን፣ እርሱ በጨለማ የተወሰረውን ሁሉ ያውቃልና» አላት። በዚህ ጊዜ በሃፍረት ተሸማቀቀች፣ ተገርማም ትታው ሔደች።

5 የተወለደው በሶርያ ንጽቢስ በምትባል ከተማ ነው። አባ ኤፍሬም የአባ ያዕቆብ ደቀ መዝሙር ሲሆን ዲቁናን የተቀበለው ከአባ ያዕቆብ ነው። እርሱንም ተከትሎ በኒቂያ ጉባኤ ተካፍሏል። ከዚያ በኋላ አባ ኤፍሬም ከአባ ባስልዮስ ጋር ተገናኝቷል። በትሕትናው፣ በድርሰቶቹ እና በመንፈሳዊ ሕይወቱ የታወቀ አባት ነው። ከ3000 በላይ መንፈሳዊ ድርሰት መድረሱ ይነገራል። ያረፈው በ69 ዓመቱ ሐምሌ 15 ቀን 375 ዓ.ም ነው።







አባ ኤፍሬም ሶርያዊ በኢትዮጵያዊው ሠዓሊ ዓይን

# ኤቫግሪዮስ[6]

4. በበአትህ ተቀመጥ፣ ልብህን ሰብስብ፣ ዕለተ ሞትህን አዘክር፣ አሚሚትህ ምን ሊሆን እንደሚችል አስብ፤ መንፈስህ ጽኑ ይሁን፣ሕማማትን ተቀበል፣ የዓለምን ከንቱ ነገር ናቀው፣ ያን ጊዜ ያለ ድካም በሰላም መኖር ትችላለህ:: በሲዖል ምን እንዳለ አስብ፣ በዚያ ያሉ ነፍሳትን ሁኔታ አስብ፣ አስቃቂ የሆነውን ዝምታ፣ መሪር የሆነውን ጩኸት፣ ፍርሐታቸውን፣ ሁከታቸውን፣ በዚያ የሚኖሩበት ዘመን ማለቂያ እንደሌለው አስበው:: ፍጻሜ የሌለውን ሐዘናቸውንና ዘለዓለማዊውን የነፍሳቸውን ልቅሶ አስብ:: በሌላ በኩል ደግሞ የትንሣኤን ዕለት አስበው፤በእግዚአብሔር ፊት መቆምንም አትርሳ:: አስፈሪውንና አስደንጋጩን ፍርድ አስብ፣ ለኃጥኣን የተጠበቀላቸውን መከራ፣ በፈጣሪ ፊት በሊቃነ መላእክት፣ በመላእክትና በጻድቃን ሁሉ ፊት የሚከናነቡትን ሃፍረት አስብ፣ ያም ቅጣቱ፣ ዘለዓለማዊው እሳት፣ የማያንቀላፋው ትል፣ ጨለማው፣ ጥርስ ማፋጨቱ፣ ፍርሐቱና ሰቀቀኑ ናቸው:: ለጻድቃን የታሰበላቸውን መልካም ነገርም አስብ፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ፊት፣ በሊቃነ መላእክት በመላእክትና በሰዎች ሁሉ ፊት የሚኖራቸውን ክብር አስብ፤ መንግሥተ ሰማያትን በዚያ ያለውን ጸጋ፣ ደስታና ብፅዕና አትርሳ::

5. እነዚህን ሁለት እውነታዎች በልቡናህ አኑር:- በኃጥኣን ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ስትል አልቅስ፣ ምናልባት አንተም እነዚያን ስቃዮች እንደምትቀበል አድርገህ ለራስህ እዘን:: በጻድቃን ዕጣ ፈንታ ደግሞ ደስ ይበልህ:: እነዚያን ጸጋዎች ለማግኘት ተጋደል:: ነገር ግን ለእነዚያ ስቃያት እንግዳ ሁን:: በበአትህ ውስጥም ሆነ ከበአትህ ውጭ እነዚህን ነገሮች ማሰብ ከአንተ እንዳይለይ ተጠንቀቅ:: ያን ጊዜ ክፉውንና አሳፋሪውን ሐሳብ ከአንተ ታርቀዋለህና::

6 የተወለደው ጳንጦስ ውስጥ በምትገኝ ኢቦራ በተባለች ከተማ ነው:: በ345/6 ዓ.ም አካባቢ አናጉንስጢስ ተብሎ በቅዱስ ባስልዮስ ተሾመ:: በመቀጠልም ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ዲቁና ሾመው:: ጎርጎርዮስን ተከትሎ በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ተካፍሏል:: በ382 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ተሻግሮ አስከፊ የሆነ የሕመም ጊዜን አሳለፈ:: በ383 ወደ ግብፅ በመውረድ በንጥራ ገዳም መነከሰ:: በሴልያ የመቃርዮስ ዘእስክንድርያ ደቀ መዝሙር ሆኖ ዐሥር ዓመት ተቀምጧል:: በትምህርቱ እና ምቾት አልባ ኑሮን በመውደዱ የታወቀ ነበር:: ያረፈው በ400 ዓ.ም ነው::





# አባ ኤልያስ

1. ፀፀት ባለችበት ኃጢአት ምን ትሠራለች፤ ትዕቢት ባለችበትስ ፍቅር ምን ትጠቅማለች::

2. የሰው ኅሊና ከሦስት ነገሮች ወደ አንዱ ያጋደለ ነው:- ወደ ኃጢአት፣ ወደ ሰዎች ወይም ወደ ክርስቶስ::

3. መንፈሳችን ከአካላችን ጋር አብሮ ካልዘመረ ድካማችን ሁሉ ከንቱ ነው:: መከራን የሚቀበል ሁሉ በመጨረሻ ደስታና ሰላም ማግኘቱ አይቀሬ ነው::

4. አንድ መነኩሴ አባ ኤልያስን «እባክህ ለሕይወቴ የሚጠቅመኝን ምክር ስጠኝ» አለው:: አባ ኤልያስም «በአባቶቻችን ዘመን ለእነዚህ ለሦስቱ ነገሮች ልዩ ቦታ ይሰጡ ነበር:- በፈቃድ ለሚሆን ድህነት፣ ለመታዘዝና ለጾም:: በአሁኑ ዘመን መነኮሳት ዘንድ ግን ስስት፣ በራስ መኩራራትና ስግብግብነት ቦታ አላቸው:: ከእነዚህ ከሁለቱ መንገዶች መልካሙን ምረጥ» አለው::

# አባ ቴዎፍሎስ ሊቀ ጳጳሳት[7]

ነፍሳችን ከሥጋችን በምትለይባት በዚያች ሰዓት እንዴት ያለ ፍርሐት፣ እንዴት ያለ ጭንቀት፣ እንዴት ያለ ችግር ይገጥመን ይሆን:: የጠላት ኃይላት ሁሉ ይህን ለመቃወም ይመጣሉ:: የጨለማም አበጋዞች፣ የክፉው ዓለም ገዥዎች፣ አለቆች፣ ኃይላት፣ የክፉው መናፍስት ሁሉ በሙግቱ ሥፍራ ከልጅነት እስከ ሽበት፣ በማወቅም ባለማወቅም የሠራችውን በደል ሁሉ በማቅረብ ነፍሳችንን ይከሷታል:: ለፈጸመችው ሁሉ ጥፋተኛ ናት ብለው ይሞግቷታል:: በዚያች ሰዓት ነፍስ ምን ዓይነት ስሜት ይኖራታል ብላችሁ ታስባላችሁ? ፍርድ ተሰጥቷት ነጻ መሆንዋ እስኪታወጅ ድረስ:: የሚመጣውን ቁርጥ ነገር እስከ ታውቅ ድረስ ያለው ሰዓት ለነፍስ ምንኛ የሚያስጨንቅ ሰዓት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር ወገኖች ጥብቅና ይቆሙላታል:: ነፍስ የፈጸመቻቸውን መልካም ምግባራት ሁሉ ዘርዝረው ያቀርባሉ:: ነፍስ በእነዚህ በሁለቱ ኃይላት መካከል ቆማ እውነተኛው ርቱዕ ፍርድ እስኪሰጣት ድረስ የሚኖራትን ፍርሐትና መንቀጥቀጥ አስቡት::

7 የእስክንድርያው ፓትርያርክ (385-412 ዓ.ም) የቅዱስ ቄርሎስ አጎት ሲሆን መንበሩን ከርሱ በኋላ ተረክቧል:: በ301 ዓ.ም. በሰራፒስ የነበረውን ዋና ቤተ ጣዖት አፈረሰ:: የአርጌንስን ኑፋቄ በዋናነት ይቃወም ነበር::

«ንዑ ኀቤየ ብሩካኑ ለአቡየ» የሚለው ፍርድ ከተላለፈላት ያን ጊዜ አጋንንት ይፈረድባቸዋል፤ መላእክትም ያሳድዷቸዋል። በዚያ ሰዓት ያለ ፍርሓት ትቆማላችሁ፤ ወይም ደግሞ «በአንቺ የሚኖሩ ሁሉ ደስ እንደሚላቸው ይነግራቸዋል»(መዝ.86÷7) እንደ ተባለው የደስታ ሕይወት ይኖራችኋል። በነቢዩ መጽሐፍ «ኀዘንና ትካዜም ይሸሻሉ» የተባለው ቃል ይፈጸማል /ኢሳ.35÷10/።

እናም ነፃ የወጣችው ነፍሳችሁ ወደዚያ ደስታ ትገባለች። የማይጠፋ ክብርም ተቀዳጅላለች። ነገር ግን በግድየለሽነት የኖረች ነፍስ ከሆነች ያንን አስጨናቂ ድምጽ «ኃጢአተኛውን ውሰደው፤ የእግዚአብሔርን ግርማ አያይም»(ኢሳ.2÷10) የሚለውን ትሰማለች። ስለዚህም የቁጣ ቀን፣ የመከራ ቀን፣ የጨለማና የድንግዝግዝ ቀን ይወርሳታል። በውጭ ወዳለው ጨለማ ትወረወራለች፤ ለማይጠፋው እሳት ተላልፋ ትሰጣ ለች፤ በዚያም ፍጻሜ ለሌለው ዘመን ትቀጣለች።

ታድያ ያ የዓለም ከንቱ ነገር የት አለ? ከንቱ ውዳሴ የት አለ? ሥጋዊ ሕይወትስ ወዴት ነው? መዝናናትስ ወዴት አለ? ክብር፣ አባት፣ እናት፣ወንድም? ማን ነው ነፍስን ከዚህ መከራ በዚያ ጊዜ ሊያወጣት የሚችል? በእሳት ስትቃጠል፣ ከመራራው ሥቃይስ ሊታደጋት የሚችል ማን ነው?

ይህ ከሆነ ታድያ ለመልካምና ለተቀደሰ ምግባር የማንተጋው በምን ምክንያት ነው? የትኛው ዓይነት ፍቅር ነው ገንዘባችን ሊሆን የሚገባው? በምን ዓይነት የኑሮ መንገድስ ነው መጓዝ ያለብን? ምን ዓይነት ምግባር? በምን ዓይነት ፍጥነት? እንዴት ባለ ትጋት? በምን ዓይነት ጸሎት? እንዴት ባለ ጽናት? መጽሐፍ «ጌታችንን ስንጠባበቅ ሁሉንም ነገር ያለ ነቀፋና ያለ ወቀሳ በሰላም ይሁን» ይለናል(1ቆሮ.1÷7-8)። በዚህ መንገድ ከተጓዝን «የአባቴ ቡሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ» የሚለውን ድምጽ እንሰማለን (ማቴ.25÷34/) አሜን።

## ዮሐንስ ሐፂር[8]

1. የጠላቱን ከተማ ለመቆጣጠር የዘመተ ንጉሥ አስቀድሞ የውኃውን መንገድ ይዘጋል፤ የእህሉንም መግቢያ ይይዛል። ያን ጊዜ ጠላቶቹ ይራባሉ፣ ይጠማሉ። በመጨረሻም እጃቸውን ይሰጣሉ። የነፍስን ፆር ለማሸነፍም በተመሳሳይ መንገድ መጠቀም ይገባል። አንድ ሰው

8 በላይኛው ግብፅ ቴባን በምትባል መንደር በ339 ዓ.ም ተወለደ። ወደ ገዳመ አስቄጥስ የገባው በልጅነቱ ሲሆን ያን ጊዜ አበ ምኔቱ አባ ባሞይ ይባል ነበር። አባ ዮሐንስ በተመሥጦው እና በታዛዥነቱ የታወቀ አባት ነበር። በመጀመርያው የአስቄጥስ ጥፋት ጊዜ ገዳሙን ትቶ ወደ ቁልዝም ተጓዘ፤ ያረፈውም በዚያ ነው።







አባ ዮሐንስ ሐፂር (ከገዳመ አስቄጥስ የተወሰደ)

በጾምና በረኃብ ከጸና የነፍሱ ጠላቶች ይዳከማሉ።

2. እኔ በትልቅ ዋርካ ሥር የተቀመጠንና አራዊት ሊባሉት የመጣን ሰው እመስላለሁ። ሊቋቋማቸው እንደማይችል ከተረዳ ሸሽቶ ወደ ዛፉ በመውጣት ነፍሱን ያድናል። በእኔም የተፈጸመው ይኸው ነው። በበአቴ ተቀምጬ ክፉ ሐሳቦች ሊቃወሙኝ ሲመጡ፣ ልቋቋማ ቸው እንደማልችል ባወቅኩ ጊዜ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሸሽቼ እመሸጋለሁ። በዚያም ከጠላ ቶቼ ፍላፃ እድናለሁ።

3. መለወጥ የምትፈልግን ነፍስ በተመለከተ አባ ዮሐንስ እንዲህ አለ፡- በአንዲት ከተማ ውስጥ ብዙ ወዳጆች የነበሯት አንዲት አመንዝራ ሴት ነበረች። ከገዥዎቹ አንዱ ቀረባትና «መልካም ሴት ለመሆን ቃል ግቢልኝና አገባሻለሁ» አላት። እርሷም ቃል ገባችለትና ተጋቡ። ወደ ቤቱም ወሰዳት። የቀድሞ አፍቃሪዎቿ ያቺን ሴት ፈለጓት፣ እርስ በርሳቸውም «ያ ልዑል ወደ ቤቱ ወስዷታል፤ ወደ ቤቱ

ብንሔድ ይቀጣናል፡፡ ነገር ግን በጓሮ በኩል እንሒድ፣ ለርሷም እና ፏጭላት፣ የፉጨቱን ድምጽ ስትሰማ ከደርቡ ወርዳ ወደኛ ትመጣለች፣ በዚህም ያለ ችግር እናገኛታለን» ተባባሉ፡፡ ወደ ቤቷም ጓሮ ተጉዘው ያፏጩ ጀመር፡፡ እርሷ ግን የፉጨቱን ድምፅ ስትሰማ ጆሮዋን ደፈነች፡፡ ወደ ውሳጣዊው እልፍኝም ገባች፡፡ በሩንም ጥርቅም አድርጋ ዘጋች፡፡ ይህቺ ሴት የኛ ነፍስ ምሳሌ ናት፤ ወዳጆቿ የተባለም ፈተናዎቿ ናቸው፤ ገዥ የተባለውም ክርስቶስ ነው፡፡ እልፍኝ የተባለውም ዘለዓለማዊው ቤት ነው፡፡ እነዚያ የሚያፏጩት ክፉዎች አጋንንት ናቸው፤ ነገር ግን ነፍስ ሁልጊዜም በክርስቶስ አምባነት ትሸሸጋቸዋለች፡፡

4. አባ ዮሐንስ ልቡናው ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበረ ምድራዊ ነገሮችን ይዘነጋ ነበር፡፡ አንድ ቀን አንድ ወንድም ቅርጫት ሊወስድ ወደ አባ ዮሐንስ በኣት መጣ፡፡ አባ ዮሐንስም ምን ፈልጐ እንደሆነ ጠየቀው፡፡ ያም ወንድም «ቅርጫት ፈልጌ ነው» አለው፡፡ አባ ዮሐንስ ወደ በኣቱ ተመለሰና ዘንግቶት ወደ ሽመና ሥራው አመራ፡፡ ጥቂት ቆይቶ ያ ወንድም አንኳኳ፣ አባ ዮሐንስም ወጥቶ «ምን ፈልገህ ነው» አለው «ቅርጫት ስጠኝ ብየህ ነበር» ሲል መለሰለት፡፡ ተመልሶ ወደ በኣቱ ሲገባ ልቡናው በሰማያዊ ነገር ስለተመሰጠ ዘንግቶት ወደ ሽመናው ሥራ እንደገና ገባ፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ያ ወንድም ሲያንኳኳ አባ ዮሐንስ ተመልሶ ወጣና «ምን ፈልገህ ነው?» አለው፡፡ «ቅርጫት ስጠኝ ብዬህ ነበር» አለና መለሰለት፡፡ አባ ዮሐንስም እጁን ይዞ እየጐተተ ወደ በኣቱ አስገባውና «ቅርጫት ከፈለግህ ያዝና ሒድ፣ በእውነቱ እንዲህ ላሉት ነገሮች እኔ ጊዜ የለኝም» አለው፡፡

5. አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ አባ ዮሐንስ ሐቂር በኣት መጣና ሥራውን እያየ ያመሰግነው ጀመር፡፡ አባ ዮሐንስ ዝም አለውና ገመድ መሥራቱን ቀጠለ፡፡ እንግዳውም እንደገና ወሬውን ቀጠለ፤ አባ ዮሐንስም ጸጥ አለው፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ እንግዳው ወሬ ሲያበዛ፡፡ «አንተ ወደ በኣቴ በመግባትህ እግዚአብሔር ወጥቶ ሔደ» ብሎ ተናገረው፡፡

6. አባ ዮሐንስ እንዲህ አለ፡- «የብሕትውናን ኑሮ በከተማ ውስጥ የሚኖር አንድ ሽማግሌ ነበረ፡፡ ያ ሰው በከተማው ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠውና ባለዝናም ነበር፡፡ አንድ አረጋዊ አባት ከማረፉ በፊት ያንን ሰው ሊያየው እንደሚፈልግ ለዚያ ሰው ጥሪ ደረሰው፡፡ ያም ሰው በቀን ከተጓዙ ሰዎች ስለሚከተሉኝ ለኔ የተለየ ክብር ይሰጠኛል ብሎ አሰበ፡፡ ስለዚህም በሌሊት ሰው ሳያየው ለመጓዝ ወሰነ፡፡ በመሸ ጊዜም







አባ መቃርዮስ፣ በገዳመ አስቄጥስ የአባ መቃርዮስ ገዳም የሚገኝ

አሁን ማንም አያየኝም ብሎ ተነሣና ጉዞ ጀመረ:: ነገር ግን ሁለት መላእክት ታዝዘው መብራት ይዘው መንገዱን ይመሩት ነበር:: ይህንን የተመለከቱ የከተማው ሰዎች ወደ እርሱ ተሰባሰቡ፤ መላ ከተማው ያንን የመላእክት ብርሃን እያየ ከኋላ ተከተለው:: ከክብር በሸሸ ቁጥር የበለጠ ክብርን አገኘ:: በዚህም «ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፤ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ከፍ ይላል» የሚለው የወንጌል ቃል ተፈጸመ /ሉቃ.14÷11/::

7. አባ ጴሜን አባ ዮሐንስ እንዲህ ብሎ መናገሩን ገልጧል:: «ቅዱሳን በአንድ ቦታ የበቀለ ዛፎችን ይመስላሉ:: ከአንድ ምንጭ ጠጥተው፣ ልዩ ልዩ ዓይነት ፍሬ ያፈራሉ:: የአንዱ ቅዱስ ሥራ ከሌላው ይለያል፣ ነገር ግን በሁሉም አድሮ የሚሠራው አንድ መንፈስ ቅዱስ ነው::»

## አባ መቃርዮስ[9]

1. በአንድ ወቅት አባ መቃርዮስ ይህንን ታሪክ ተናግሮ ነበር: - ወጣት ሆኜ በአንዲት በአት ውስጥ ስኖር የመንደሩ ጸሐፊ ሊያደርጉኝ ፈለጉ:: ይህንን ክብር መቀበል ስላልፈለግሁ ሸሸቼ ወደ ሌላ መንደር ገባሁ:: ሸሸቼ ስሔድም አንድ ሰው አብሮኝ ነበረ:: ያም ሰው እኔ በእጄ የምሠራውን እየሸጠልኝ ያገለግለኝ ነበር:: በዚህ መሐል በዚያ መንደር የነበረች አንዲት ድንግል ሕጋዊ ባልሆነ መልኩ አረገዘች:: ማርገዟ በታወቀ ጊዜ ያስረገዛት ማን እንደሆነ ቤተሰቦቿ ጠየቋት:: እርሷም «ያስረገዘኝ ያ መናኝ ነው» ብላ ተናገረች:: መንደርተኞቹም ይህንን ሲሰሙ መጥተው ያዙኝ:: ጥቀርሻ የመሰለ ማሠሮና ሌሎችንም የወዳደቁ ነገሮች በአንገቴ ዙሪያ አደረጉብኝና በመንደር መሐል እያዳፉ ወሰዱኝ:: እየደበደቡኝም «ይህ መነኩሴ ልጃችንን አበላሸ፣ ያዙት፣ ያዙት» ይሉ ነበር::

እስክሞት ድረስ ደበደቡኝ:: ከሽማግሌዎች አንዱን ወደ እኔ ቀረበና ሕዝቡን «ምን መሥራታችሁ ነው? ይህን እንግዳ መነኩሴ እስኪሞት መደብደባችሁ ለምንድን ነው?» ሲል ተቆጣቸው:: ያ ያገለግለኝ የነበረ ሰው ሃፍረት ተከናንቦ ከኋላዬ ይጓዝ ነበር:: እርሱንም ይሰድቡት ነበር:: «ተመልከት ይህንን የምታገለግለውን መነኩሴ፤ ምን

9 አባ መቃርዮስ ታላቁ የተወለደው በ300 ዓ.ም ሲሆን በንጥራን አካባቢ በግመል ይነግድ የነበረ ነጋዴ ነው:: በገዳመ አስቄጥስ ምንኩስናዊ ሕይወትን ካደራጁ አበው አንዱ ነው:: መጀመርያ በዲቁና ተሹሞ በአንዲት መንደር ውስጥ የምናኔን ሕይወት ይኖር ነበር:: በኋላ ግን ወደ ገዳመ አስቄጥስ በመምጣት በዚያ ገዳማዊ ሕይወትን አስፋፍቷል:: ያረፈው በ390 ዓ.ም ነው::





እንደ ሠራ አየህ?» ይሉት ነበር:: የልጃገረዲቱ ወላጆች «እርሷን ለመከባከብ ቃል እስኪገባ ድረስ አትልቀቁት» ይላሉ:: (ልጅቱን ለመከባከብ ቃል ገብቼ ሲለቁኝ ወደ በኣቴ ተመለስኩ::) ከዚያም የሚያገለግለኝን ሰው «ያሉኝን ቅርጫቶች ሁሉ ሽጥና ለዚያች ሴት ስጥልኝ» አልኩት:: እር ሱም እንዳልኩት አደረገ:: ለራሴም «መቃርዮስ ሆይ፣ ለራስህ ሚስት አግኝተሃል፣ እርሷን መከባከብ ትችል ዘንድ ካለፈው የተሻለ ሥራ መሥራት አለብህ» ብዬ ነገርኩት:: ሌትና ቀን እየሠራሁ የማገኘውን ሁሉ ለእርስዋ እልክላት ነበር:: የዚያች ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ:: ነገር ግን ለብዙ ቀናት ብታምጥም መውለድ አልቻለችም:: መንደርተኞቹም «ምንድን ነው ችግሩ?» ብለው ጠየቋት:: እርሷም «ምክንያቱን ዐውቄዋለሁ፣ ያንን መናኝ ባላደረገው ኃጢአት ስለ ወነጀልኩት ነው፤ ያስረገዘኝ እርሱ አልነበረም፤ ያስረገዘኝስ እገሌ ነው» ብላ እውነቱን ተናገረች:: በዚህ ጊዜ ያገለግለኝ የነበረው ሰው ተደስቶ ወደ እኔ እየሮጠ መጣና የሆነውን ሁሉ ነገረኝ:: «ያች ሴት ያስረገዘኝ መነኩሴው አይደለም እስክትልና እውነቱን እስክትናገር ድረስ መው ለድ አልቻለችም፤ መንደርተኞቹ ሁሉ መጥተው ይቅርታ ሊጠይቁህ በዝግጅት ላይ ናቸው» አለኝ:: ነገር ግን ይህንን ስሰማ ሕዝቡ ስለ እኔ መልካም በማውራት ነፍሴን በውዳሴ ያዝሏታል ብዬ በመፍራት ሸሽሁ፤ ወደዚህ ገዳምም መጣሁ::

2. አንድ ጊዜ አባ መቃርዮስ ከገዳመ አስቄጥስ ወደ ንጥራ ተራራ አባ ፓምቦን ለማግኘት ወጣ:: በዚያ ያሉ መነኩሳት ትክክለኛ መነኩሴ ማን እንደሆነ ጠየቁት:: አባ መቃርዮስም «እኔ ገና መነኩሴ መሆን አልጀመርኩም፤ ነገር ግን የመነኮሱ መነኮሳትን አይቻለሁ» አለና ቀጥሎ ያለውን ታሪክ ነገራቸው::

«አንድ ጊዜ በበኣቴ ውስጥ ተቀምጬ እያለሁ፤ ሐሳቦቼ ያስቸግሩኝ ነበር:: ተነሣና ወደ በረሓ ሒድ፣ በዚያም የማሳይህን ተመልከት የሚለኝ መንፈስ መጣ:: ነገር ግን ምናልባት ከአጋንንት የመጣ ሊሆን ይችላል ብዬ ከበኣቴ ሳልወጣ ለአምስት ዓመታት ይህን ሐሳብ ስጋደለው ኖርኩ:: ይሁን እንጂ ያ ሐሳብ አሁንም ሊጠፋ ስላልቻለ ወደ በረሓ ተጓዝኩ:: በዚያም የተንጣለለ ባሕርና በመካከሉም ደሴት አገኘሁ:: የደሴቲቱም እንስሳት ውኃውን ለመጠጣት መጡ:: በእነዚህ እንስሳት መካከል ሁለት ራቁታቸውን የሆኑ ሰዎችን ተመለከትኩ:: መናፍስት ናቸው ብዬ ስላሰብኩ ሰውነቴ ራደ:: ወደ እኔ ሲመለከቱም በጣም ተንቀጠቀጥኩ:: ያን ጊዜ «እኛ ሰዎች ነን፤ አትፍራ» አሉኝ::

እኔም «ከየት መጣችሁ፣ እዚህ በረሓ ውስጥስ እንዴት መጣችሁ» ስል ጠየቅኳቸው:: «የመጣነው ከገዳም ነው፣ እዚህ በረሓ ውስጥ በአንድነት ለመኖር ተስማማን፤ ወደዚህ የመጣነው ከአርባ ዓመታት በፊት ነው፤ አንዳችን ግብፃዊ አንዳችንም ሊቢያዊ ነን» ብለው መለሱልኝ::

ከዚያም እንዲህ ሲሉ ይጠይቁኝ ጀመር፣ «ዓለም እንዴት ናት?» በዘመን ብዛት የውኃው መጠን ጨምሯልን? ዓለም በብልጽግና ተሞልታለችን?» እኔም «አዎን» ብዬ መለስኩላቸው:: «እንዴት ነው መነኩሴ መሆን የምችለው?» ብዬ ጠየቅኳቸው:: «በዓለም ያለውን ሁሉ በፈቃድህ መተው ካልቻልክ መነኩሴ መሆን አትችልም» ሲሉ መለሱልኝ:: «እኔ ደካማ ነኝ፣ እናንተ የምታደርጉትን ማድረግ አልችልም» አልኳቸው:: «እንደ እኛ መሆን ካልቻልክማ በበኣትህ ውስጥ ተቀመጥና አልቅስ» አሉኝ:: እኔም መልሼ «የብርዱ ወራት ሲመጣ አይበርዳችሁምን?» ብዬ ጠየቅኳቸው:: እነርሱም መልሰው «ይህን መሰሉን ሕይወት ለኛ የሰጠ እግዚአብሔር ነው፤ በቀዝቃዛው ጊዜ አይበርደንም፣ በሙቀቱም ጊዜ አያቃጥለንም» ሲሉ መለሱልኝ:: ለዚህ ነው ገና መነኩሴ አልሆንኩም ያልኳችሁ::

3. አባ መቃርዮስ በምድረ በዳ እያለ በአካባቢው በብሕትውና የሚኖር እርሱ ብቻ ነበር:: ከእርሱ በኣት ራቅ ብሎ በሌላ በረሓ ውስጥ ብዙ መናንያን ነበሩ:: አንድ ጊዜ አባ መቃርዮስ ሰይጣንን በሰው ተመስሎ፣ የተቀዳደደ ልብስ ለብሶ፣ በእያንዳንዱ ቀዳዳ የተለያዩ የምግብ ዕቃዎች አንጠልጥሎ ሲጓዝ አየው:: አባ መቃርዮስም ሰይጣኑን «ወዴት እየተጓዝክ ነው?» ሲል ጠየቀው:: ሰይጣንም «የወንድሞችን ልቡና ለማወክ እየሔድኩ ነው» ሲል መለሰ:: «ታድያ የእነዚህ ትናንሽ የምግብ ዕቃዎች ጥቅም ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው:: «ወንድሞች ይቀምሱት ዘንድ ምግብ ይዤላቸው እየሔድኩ ነው» አለው:: አባ መቃርዮስም «ይህ ሁሉ ዓይነት ምግብ ምን ያደርግልሃል?» ብሎ ጠየቀው:: «አንዱ ወንድም አንድን ዓይነት ምግብ ባይወደው ሌላውን እሰጠዋለሁ፣ ያንንም ካልወደደው ሦስተኛውን አቀርብለታለሁ፤ እንዲህ እያደረግኩ ቢያንስ አንድ የሚወደው ምግብ አገኝለታለሁ» ብሎ ነግሮት ከርሱ ተለየ::

አባ መቃርዮስ ያ ሰይጣን የተጓዘበትን መንገድ እያየ እስኪመለስ ድረስ ጠበቀው:: በመጨረሻ ሰይጣኑ ተመልሶ ሲመጣ አየውና «ጤና ይስጥልኝ» አለው:: «እንዴት አድርጌ በጤና እሆናለሁ» ሲል መለሰ ሰይጣኑ:: አባ መቃርዮስም ምን ማለቱ እንደሆነ እንዲነግረው





ጠየቀው::«ማንም አልተቀበለኝም፤ ሁሉም ተቃወሙኝ»ሲል መለሰለት:: «ላንተ የሚሆን ምንም ሰው ከዚያኛው በረሓ አላገኘህምን?» ሲል መቃርዮስ ጠየቀው:: በርግጥ በዚያ የሚኖር አንድ መነኩሴ አግኝቻለሁ፤ ባይሆን እርሱ እሺ ብሎኛል:: ባየኝ ጊዜ እንደ ነፋስ ሆኖ ተቀየረ» አለ ሰይጣኑ:: «ስሙ ማን ይባላል?» በማለት መቃርዮስ ጠየቀው፤ «ቴዎዲምጦስ ይባላል» ብሎ ሰይጣኑ በሓዘን መንገዱን ቀጠለ::

አባ መቃርዮስ ይህን እንደሰማ ተነሥቶ ወደዚያኛው ምድረ በዳ ወረደ:: የርሱን መምጣት እንደሰሙ በበረሓው የነበሩ ወንድሞች ሁሉ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡ:: እያንዳንዱ መናኒ አባ መቃርዮስ የመጣው እኔን ሊጎሥጽ ነው እያለ ልቡናውን ዝግጁ አደረገ:: አባ መቃርዮስ ግን ሁሉንም ትቶ ቴዎዲምጦስ የተባለው መናኒ የቱ እንደሆነ ይጠይቅ ጀምር:: መነኩሳቱ የዚያን መናኒ በኣት አሳዩትና ወደዚያ አመራ:: ቴዎዲምጦስም አባ መቃርዮስን ተቀበለው:: ሁሉም ሔደው አባ መቃርዮስና ቴዎዲምጦስ ብቻቸውን በቀሩ ጊዜ አባ መቃርዮስ «ሕይወት እንዴት ነው?» ሲል ጠየቀው:: ቴዎዲምጦስም «በጸሎትህ የተነሣ ሁሉም ነገር ደኅና ነው» ሲል መለሰ: «ክፉ ሐሳብ በልቡናህ እየመጣ አይፈታተንህምን?» ሲል ጠየቀው:: ቴዎዲምጦስ አባ መቃርዮስን ስለ ፈራው «አይ ሰላም ነኝ» ብሎ መለሰለት:: አባ መቃርዮስም «ታድለሃል! ተመልከት እኔ ለብዙ ዘመናት በምናኔ ኑሬያለሁ፤ ሁሉም ያመሰግኑኛል:: ምንም እንኳን አረጋዊ ብሆን መንፈሰ ዝሙት ግን አሁንም ይፈታተነኛል» ብሎ ነገረው:: ቴዎዲምጦስም «አባቴ ሆይ÷ ይህማ እኔንም ይፈትነኛል» አለው:: አባ መቃርዮስም ያ ወንድም ሌሎችም ፍትወታት እየተዋጉት መሆኑን እስኪያምን ድረስ በሁኔታው ገፋበት:: በመጨረሻም «የምትጸመው እንዴት ነው?» አለና ጠየቀው:: «እስከ ዘጠኝ ሰዓት ነው» ብሎ መለሰ:: «ትንሽ ጨምረህ ጹም፤ ወንጌልና ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበብክ በልቡናህ ዘወትር አስባቸው፣ተቃዋሚ ሲነሣብህ ስለዚያ ነገር ማሰብ ትተህ ስለ ሰማያዊ ነገር አስብ፤ ጌታ አንተን ሊረዳህ ይመጣልና» ሲል መከረው:: ከዚያም አባ መቃርዮስ ወደ በኣቱ ተመለሰ::

በሌላ ጊዜ ከበኣቱ በር አጠገብ ተቀምጦ ሰይጣንን በዚያ መንገድ እስኪያልፍ ይጠባበቀው ነበር:: ሰይጣንም በዚያ መንገድ ወደዚያኛው ገዳም ለመሔድ መጣ:: አባ መቃርዮስም «የት ትጓዛለህ?» ሲል ጠየቀው:: «የወንድሞችን ልቡና ለማወክ እሔዳለሁ» አለውና ሔደ:: ተመልሶ ሲመጣ «ወንድሞች እንዴት ናቸው?» ሲል ጠየቀው:: ካለፈው

የከፋ እንደሆነበትና ምንም እንዳልተሳካለት ነገረው:: አባ መቃርዮስም ለምን እንደሆነ ጠየቀው:: «ሁሉም ጽኑዐን ሆኑብኝ፤ በተለይ የገረመኝ ያ ያልኩትን ይቀበለኝ የነበረው መናኒ፤ ምን እንደ ለወጠው አሳው ቅም ሊቀበለኝ በፍጹም አልወደደም:: በዚህም ምክንያት ለቀጣዮቹ ዘመናት ተመልሼ ወደዚያ ላለመሔድ ለራሴ ቃል ገብቻለሁ» አለው:: ይህን ብሎ መንገዱን በሓዘን ቀጠለ:: መቃርዮስም ወደ በአቱ ገባ::

4. አንድ ጊዜ አባ መቃርዮስ አባ እንጦንስ ወደሚኖርበት ተራራ ወጣ:: ወደ አባ እንጦንስ በአት ቀርቦ እጁን ጻፋ:: አባ እንጦንስ ከበአቱ ወጥቶ መጣና «አንተ ማን ነህ?» ሲል ጠየቀው:: አባ መቃርዮስም «እኔ መቃርዮስ ነኝ» ብሎ መለሰ:: አባ እንጦንስም ወደ በአቱ ተመልሶ ገባና በሩን ዘጋው:: አባ እንጦንስ የአባ መቃርዮስን በትዕግሥት ጸንቶ መቆየት ተመለከተና በሩን ከፈተለት:: መቃርዮስንም በደስታ ተቀበለው:: አባ እንጦንስም «አንተን ለማየት ለረዥም ዘመን እናፍቅ ነበር:: ስለ አንተ ብዙ እሰማ ነበርና» አለው:: ለአንድ እንግዳ የሚገባውን ሁሉ አደረገለት:: ደክሞት ነበርና ያርፍ ዘንድ አነጠፈለት:: ሲመሽም አባ እንጦንስ ለራሱ ጥቂት የዘንባባ ፍሬዎች ሸመጠጠ:: አባ መቃርዮስም «እባክህ እኔም ለራሴ ፍሬዎችን አሸመጥጥ ዘንድ ፍቀድልኝ» አለው:: አባ እንጦንስም «ባል በርታ» አለው:: ብዙ የዘንባባ ቅርንጫፍ ሰበሰበና ፍሬዎቹን ሸመጠጣቸው:: ከዚያም ምሽቱን ሰሌን እየታቱ ስለ ነፍሳቸው ድኅነት ይነጋገሩ ጀመር:: አባ መቃርዮስ የሠራው ገመድ በበአቱ መስኮት በኩል ተንጠልጠሎ ነበር:: በነጋታው የገመዱን ርዝመት የተመለከተው አባ እንጦንስ «ከእነዚህ ደካማ እጆች እንዴት ያለ ጉልበት ተገኘ!» ሲል ተደነቀ::

5. አባ ሲሳስ ስለ አባ መቃርዮስ የሚከተለውን ተናግሮ ነበር:: ከአባ መቃርዮስ ጋር ሰባት ሆነን ለመከር ሥራ ወጥተን ነበር:: በዚያ ጊዜ አንዲት ባልዋ የሞተባት ሴት ከኋላችን እያለቀሰች ትከተለን ጀመር:: አባ መቃርዮስ የእርሻውን ባለቤት ጠርቶ ሴትዮዋ ምን እንደ ሆነች ጠየቀው:: «ባልዋ ከሰው ገንዘብ ወስዶ የት እንዳስቀመጠው ሳያሳያት ሞተ:: አበዳሪው አሁን መጥቶ ገንዘቡን ካላመጣሽ ልጆችሽን ወስጄ ባሪያዎች አደርጋቸዋለሁ አላት» ሲል ነገረው:: «በዕረፍት ሰዓታችን እንድትመጣ ንገራት» አለው ለእርሻው ባለቤት::

ሴትየዋ በዕረፍት ሰዓታችን መጣች:: አባ መቃርዮስም «እንደዚህ ሆነሽ የምታለቅሽው ለምንድን ነው?» ብሎ ጠየቃት:: «ባሌ በወለድ ገንዘብ ከሰው ወሰደ:: ነገር ግን የት እንዳስቀመጠው ሳይነግረኝ





በድንገት ሞተ» ስትል ነገረችው:: «ባልሽ የት እንደተቀበረ አሳይኝ» አላት:: አባ መቃርዮስ እኛን አስከትሎ በሴትየዋ መሪነት ወደ መቃብሩ ተጓዘ:: ሴትየዋ ቦታውን ካሳየችን በኋላ ወደ ቤትሽ ሒጂ አላት:: ከዚያም ወንድሞችን ጸልዩ ብሎ «አንቴ ሆይ - ገንዘቡን የት ነው ያስቀመጥከው?» ሲል መቃብሩን ጠየቀው:: ዐፅሙም «በቤት ውስጥ ከአልጋው እግር ሥር ነው» ሲል መለሰላት:: አባ መቃርዮስም «በል እስከ ዕለተ ትንሣኤ ባለህበት ዕረፍ» ሲል ተናገረው:: ይህንን የሰሙ ወንድሞች ሁሉ በፍርሐት ተዋጡ:: በእግሩ ሥርም ወደቁ:: አባ መቃርዮስ ግን «ይህ ሁሉ የሆነው ስለ እኔ ሲባል አይደለም፤ እኔ ምንም ነኝና:: እግዚአብሔር ይህንን ተአምር የሠራው ስለ ሴትየዋና ስለ ልጆቿ ሲባል ነው:: ይህም ነፍስ ያለ ኃጢአት ብትኖር እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደሚሰጣት የሚያመለክት ነው» አለ:: ከዚያ በኋላ ባልዋ ለሞተባት ሴት ገንዘቡ የት እንዳለ ነገራት:: እርሷም ወስዳ ለአበዳሪው ሰጠችው:: ልጆቿም ነጻ ወጡ:: ይህን ታሪክ የሰሙ ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ::

6. አባ ጴጥሮስ የተባለው አባት ስለ አባ መቃርዮስ ይህን ተናገረ:: «አንድ ጊዜ አባ መቃርዮስ ወደ አንድ የታመመ ባሕታዊ ዘንድ መጣ:: ቀርቦም አንዳች የሚበላ ነገር አግኝቶ እንደሆነ ጠየቀው:: በበአቱ ውስጥ ግን ምንም ነገር አልነበረም:: ታማሚው ባሕታዊም «ጥቂት ፓፓያ ብቻ አለኝ» ሲል መለሰ:: አባ መቃርዮስም ማንም ሳያየው ተነሥቶ በእርጅና ጉልበቱ እስክንድርያ ከተማ ድረስ በመጓዝ ለሕመምተኛው የሚሆን ነገር ይዞለት መጣ::

7. አንድ ቀን አባ መቃርዮስ የሰሌን ዛፍ ቆርጦ ወደ በአቱ ሲመለስ በመንገድ ላይ ሰይጣንን ረዥም፣ ጠማማና ስለታም ማጭድ ይዞ አገኘው:: ሰይጣንም በያዘው ማጭድ በኃይል ሠንዝሮ መቃርዮስን መታው:: ነገር ግን ምንም አልጐዳውም:: በዚህ የተገረመው ሰይጣን «መቃርዮስ ሆይ ምን ዓይነት ኃይል ነው ያለህ? እንዴት ባንተ ላይ ዐቅመ ቢስ ሆንኩ? የምታደርገውን ሁሉ አደርገዋለሁ፤ ትጾማለህ እኔም አልበላም፤ ሌት ያለ ዕንቅልፍ ታነጋለህ፤ እኔም ዕንቅልፍ የለብኝም፤ አንተ እኔን ድል ያደረግከኝ በአንድ ነገር ብቻ ነው:: ያም ፍጹም የሆነ ትሕትናህ ነው:: በርሱ የተነሣ በአንተ ላይ አንዳች ሥልጣን አጣሁ» ብሎት ሔደ::

8. ከወንድሞች አንዱ ወደ አባ መቃርዮስ መጥቶ «እባክህ ለሕይወቴ የሚሆን መመርያ ስጠኝ?» አለው:: አባ መቃርዮስም ያንን

ወንድም «ወደ መቃብር ሒድና በሙታን ላይ ክፉ ነገር አድርግባቸው» ብሎ ላከው:: ሰውየውም በሙታን ላይ ድንጋይ በመወርወርና በመ ሳደብ የተላከውን ፈጽሞ መጣ:: አባ መቃርዮስም «ምን አሉህ?» ሲል ጠየቀው:: ያም ወንድም «ምንም አላሉኝም» ብሎ መለሰ:: «በነጋታው ተመልሰህ ናና አመስግናቸው» አለው:: በነጋታው ያ ወንድም ወደ መቃብሩ ሥፍራ ተጉዞ ሙታኑን «ሐዋርያት፣ ቅዱሳን፣ ጻድቃን» እያለ አመሰገናቸውና ተመለሰ:: መቃርዮስም «ምን መለሱልህ?» አለው:: «ምንም» አለ:: መቃርዮስም ስትሰድባቸውና በድንጋይ ስት መታቸው፣ ስታመሰግናቸውና ስታወድሳቸው ምንም አልመለሱም፤ አን ተም ለነፍስህ ድኅነትን ከፈለግክ እንደ ሞተ ሰው ሆነህ ኑር:: ሰዎች ክፉ ቢያደርጉብህም ቢያመሰግኑህም ምንም አይሰማህ አለው::

9. አንድ ጊዜ አባ መቃርዮስ ከወንድሞች ጋር ወደ ግብፅ ሲሔድ አንድ ልጅ ለእናቱ «አንድ ሀብታም አለ እርሱ ይወደኛል እኔ እጠላዋለሁ፤ አንድ ምስኪን አለ እርሱ ይጠላኛል እኔ እወደዋለሁ» ብሎ ሲነግራት ሰማ:: ይህን ጊዜ አባ መቃርዮስ እጅግ ተደነቀ:: አብረውት የነበሩት ወንድሞችም ምን እንዳስደነቀው ጠየቁት:: እርሱም «በእውነት ባዕለ ጸጋ የተባለ ጌታችን ነው:: ነገር ግን እኛ አንወ ደውም፤ ምስኪን የተባለው ዲያብሎስ ግን እኛን ይጠላናል፤ እኛ ግን ክፋቱን እንወድለታለን::» ብሎ ነገራቸው::

10. አባ ቢጥሞስ የሚከተለውን ታሪክ ከአባ መቃርዮስ እንደሰማ መቃርዮስ ተናገረ:: «በገዳመ አስቄጥስ በነበርኩ ጊዜ ሁለት እንግዶች መጡ:: አንዱ ጢሙ የተንዠረገገ ሲሆን ሌላው ገና ጢም በማውጣት ላይ ነበር:: ወደ እኔ መጥተው «አባ መቃርዮስ የት ነው?» ብለው ጠየቁኝ:: «ከእርሱ ዘንድ ምን አላችሁ?» ስል ጠየቅኋቸው:: «ስለ እርሱና ስለ ገዳመ አስቄጥስ ሰማን፤ ስለዚህም ልናየው መጣን» ሲሉ መለሱልኝ:: «እኔ ነኝ» አልኳቸው:: እጅ ነሱኝና «እዚህ መኖር እንፈልጋለን» አሉኝ:: ገና መከራ ያልቀመሱና በቅንጦት ያደጉ መሆናቸውን ተመልክቼ «እዚህማ ለመኖር ይከብዳችኋል» አልኳቸው:: ታላቅየው እዚህ መኖር ካልቻልን ሌላ ቦታ እንሔዳለን አለኝ:: ወዲያው ለራሴ «ለምን አባርራቸዋለሁ? ለምንስ የመሰናከያ ድንጋይ እሆንባቸዋለሁ? በቦታው ያለው መከራ ራሱ በፈቃዳቸው እንዲሔዱ ያደርጋቸው የለምን?» ብዬ አሰብኩ:: ከዚያም መልሼ «ኑ ለራሳችሁም በኣት ሥሩ» አልኳቸው:: «ቦታውን አሳየንና አንዲት በኣት





እንሠራለን» አሉኝ:: እኔም መጥረቢያ፣ ዳቦ የሞላበት ቅርጫትና ጨው ሰጠኋቸው፤ ድንጋይ የማውጫውንም ቦታ አሳየኋቸው፤ «ከዚህ ጥቂት ድንጋይ ውሰዱ፣ ከዚያ ረግረግ ሥፍራ ጥቂት እንጨት አምጡ፣ ከዚያም ጣራ ሥሩለትና እዚህ ቦታ ኑሩ» አልኳቸው::

ይህን ስላቸው መከራውን ተሰቅቀው ይሔዳሉ ብዬ ነበር:: ይባስ ብለው ግን ምን ምን ዓይነት ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ጠየቁኝ:: እኔም «ገመድ መሥራት ነው» አልኳቸው:: ከረግረጉ ሥፍራ ጥቂት ሰሌን አመጣሁና እንዴት እንደሚሠሩ አሳየኋቸው:: «በዚህ ሰሌን ቅርጫት ሥሩ፤ ለጠባቂዎቹም ስጧቸው፣ ለእናንተም ዳቤ ያመጡላችኋል» አልኳቸው:: ከዚያም ትቻቸው ሔድኩ:: የሚገርመው ግን ባለማመንታትና ባለመሰልቸት ያዘዝኳቸውን ሁሉ መፈጸም ጀመሩ:: ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ወደ እኔ ዘንድ አልመጡም:: በዚህ የተነሣ በሐሳቤ «ምን ዓይነት ሕይወት እየኖሩ ይሆን? ስለገጠማቸው ያር ለማማከር ለምን እኔ ዘንድ አልመጡም? ሩቅ ያሉት ሊያማክሩኝ ሲመጡ እዚህ ከአጠገቤ ያሉት ለምን ዝም አሉ? ወደ የትም ቦታ ሔደው አያውቁም፤ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል በአርምሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ይሔዳሉ» እያልኩ አወጣ አወርድ ጀመር: ስለ ሁኔታው ወደ እግዚአብሔር ጸለይኩኝ:: የእነዚህን ወንድሞች ሕይወት ይገልጥልኝ ዘንድ ሳምንቱን በሙሉ ጾምኩ:: በሳምንቱ መጨረሻ ተነሣሁና ልጐበኛቸው ወደ በኣታቸው አመራሁ:: በሩን ሳንኳኳ ከፈቱልኝና በአርምሞ ሰላምታ ሰጡኝ:: ጸሎት ካደረግን በኋላ ዐረፍ አልኩ:: ታላቅየው ለታናሹ ምልክት ሲሰጠው ታናሹ ወጥቶ ሔደ:: ታላቁም ቁጭ ብሎ ገመድ መጐንጐን ቀጠለ:: ምንም ቃል አልተነፈሰም::

ልክ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ታናሽ አንኳኩቶ ገባና በታላቅየው ምልክት ሰጭነት ገበታ አዘጋጀ:: ቀጥሎም ከፊታችን በአርምሞ ቆመ:: እኔም «ተነሥተን በገበታው እንሠየም» አልኩና አብረን ቀረብን:: ምሽቱ ሲቃረብ «አባ ትሔዳለህን?» ብለው ጠየቁኝ:: አይ እዚሁ ነው የማድረው አልኳቸው:: በአንድ ጥግ ለእኔ ሰሌን አነጠፉልኝ፤ በሌላው ጥግ ደግሞ ለራሳቸው አነጠፉ:: መታጠቂያቸውንና አጽፋቸውን አውልቀው አንድ ላይ ተኙ:: ልክ እንደተኙ የሕይወታቸውን መንገድ ይገልጥልኝ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለይኩ:: በዚህ ጊዜ ጣራው ተከፈተ፣ ብርሃኑም እንደ ቀን ብርሃን ሆነ:: እነርሱ ግን ያንን ብርሃን አላዩትም ነበር:: ልክ የተኛሁ በመሰላቸው ሰዓት ታላቅየው ጐኑን ነካ ነካ አድርጐ ታናሹን ቀሰቀሰውና ተነሡ:: መታጠቂያቸውን አስረው እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ዘረጉ:: እኔ አያቸዋለሁ፤ እነርሱ ግን አያዩኝም

ነበር። በታናሽየው ላይ አጋንንት ዝምቦችን መስለው ሲመጡበት አየሁ። ጥቂቶቹ በአፉ ላይ ጥቂቶቹም በዐይኑ ላይ ዐረፉ። የእግዚአብሔር መልአክ ዙርያውን ከብቦ በነበልባላዊ ሰይፍ ሲያባርራቸው ተመለከትኩ። ወደ ታላቅየው ግን ፈጽሞ አይቀርቡም ነበር። ሲነጋጋ ሲል ተመልሰው ተኙ።

እኔ መንጋቱን አይቼ ከዕንቅልፍ እንደነቃ ሰው ተነሣሁ፤ እነርሱም እንደ እኔ አደረጉ። ታላቅየውም «ዐሥራ ሁለቱን መዝሙራት እናዚማቸውን?» ሲል ጠየቀኝ። «መልካም ነው» አልኩት። ታናሽየው ስድስት ስድስቱን መስመር አንድ እያደረገና ሃሌ ሉያ እያለ አምስት መዝሙራትን አዜመ። በዚህ ጊዜ ከአንደበቱ እሳት እየወጣ ወደ ሰማይ ሲያርግ አየሁ። ታላቅየውም በተመሳሳይ ሁኔታ መዝሙራቱን ሲያዜም የእሳት ዓምድ ተዘርግቶ ወደ ሰማይ ሲወጣ ተመለከትኩ። እኔም በበኩሌ በልቤ የተወሰኑትን መዝሙራት አዜምኩ። ከዚያም «ጸልዩልኝ» ብያቸው ወጣሁ። እነርሱ ግን ቃል ሳይወጣቸው እጅ ነሥተውኝ ተሰናበቱኝ። ታላቅየው ከፍጹምነት ደረጃ መድረሱን ታናሹን ግን ገና አጋንንት እየተዋጉት መሆኑን ተረዳሁ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ታላቁ ዐረፈ። ከሦስት ቀን በኋላ ደግሞ ታናሹ ተከተለው። አበው አባ መቃርዮስን ሲጐበኙ በመጡ ቁጥር ወደ እነዚያ ወንድሞች በኣት ይወስዳቸውና «ኑ! የወጣት እንግዶችን የሰማዕትነት ሥፍራ እዩ» ይላቸው ነበር።

11. አንድ ጊዜ በተራራው ላይ የሚገኙ አረጋውያን አበው ወደ ገዳመ አስቄጥስ ከአባ መቃርዮስ ዘንድ እንዲህ ብለው መልእክት ላኩ፤ «እባክህ ወደ ጌታ ከመሔድህ በፊት እኛን ለማየት ውጣ፤ ያለበለዚያ ሁሉም ሰው ሲያዝን ይኖራል።» አባ መቃርዮስም ተነሥቶ ወደ ተራራው ወጣ። እዚያ በደረሰ ጊዜ ሁሉም ተሰበሰቡና «አንድ ምክር ንገረን» አሉት። «ወንድሞቼ ኑ÷ እናልቅስ ዕንባዎቻችንም ከዐይኖቻችን እንደ ጐርፍ ይውረዱ፤ ዕንባዎቻችን የገዛ ሰውነታችንን ወደ ሚያቃጥሉበት ሥፍራ ከመሔዳችን በፊት» አላቸው። ሁሉም ወደ ምድር ተደፍተው አለቀሱ፤ ከዚያም «አባ ሆይ÷ ጸልይልን» አሉት።

12. ሰዎች የፈጸሙብንን ክፉ ነገር የምናስብ ከሆነ፣እግዚአብሔርን ለማሰብ የምንችልበትን ኃይል እናጣለን። ነገር ግን የአጋንንትን ክፉ ሥራ ዘወትር የምናስብ ከሆነ ጽኑዐን እንሆናለን።

13. አባ መቃርዮስ አንድ ጊዜ የሚከተለውን ታሪክ ተናገር





ነበር። አንድ ቀን በበረሓ ውስጥ ስጓዝ የሞተ ሰው የራስ ቅል አገኘሁ። በበትሬ ነካ ሳደርገው ያ የራስ ቅል አፍ አውጥቶ መናገር ጀመረ። እኔም «አንተ ማን ነህ?» አልኩት። «እኔማ በዚህ አካባቢ የሚኖሩ አረማውያን የቤተ ጣዖታቸው ሊቀ ካህን ነኝ፤ አንተ በጸጋ የተሞላህ መቃርዮስ ሆይ÷ በመከራ ውስጥ በመሠቃየት ላይ ላሉት /በሲዖል/ ወገኖች ጥቂት እንኳ በጸለይክላቸው ጊዜ ፋታ ያገኛሉ» አለኝ። እኔም «ይህ መከራ ምንድን ነው? ይህ ፋታስ ምንድን ነው?» ብየ ጠየቅሁት። ያም የራስ ቅል «ሰማይ ከምድር የሚርቀውን ያህል የሞላ እሳት ከሥራችን አለ። ሁላችንም በእሳቱ ባሕር ውስጥ ቆመናል፤ ከእግር ጥፍራችን እስከ ራስ ፀጉራችን በእሳቱ ተውጠናል። እያንዳንዱ ሰው ፊት ለፊት ለመተያየት አይችልም፤ የአንዱ ሰው ፊት ከሌላው ሰው ጀርባ ጋር የተጣበቀ ነው። ነገር ግን አንተ ስትጸልይልን እያንዳንዳችን በመጠኑም ቢሆን ፊት ለፊት እንተያያለን። ለኛ ፋታ ማለት ያ ነው» አለኝ። እኔም በዕንባ ተዋጥሁ። ይህ ሰው የተወለደባት ቀን ምንኛ የተረገመች ትሆን አልሁ። ለራስ ቅሉም «ከዚህ የባሰ ሌላ ቅጣትስ እዚያ አለ» ብዬ ጠየቅሁት። «እኛ እግዚአብሔርን ለማወቅ ዕድል ስላልነበረን የተወሰነ ምሕረት እናገኛለን፤ እነዚያ ዐውቀው የካዱት ግን ከኛ በታች ባለው ከፍተኛው የመከራ ቦታ ይገኛሉ» አለኝ።

14. አንድ ጊዜ አባ መቃርዮስ ረድእን አስከትሎ ወደ ናጥራን ተራራ ወጣ። በመንገድ እያለ ደቀ መዝሙሩን ከእኔ ቀድመህ ሒድ ብሎ ላከው። ያም ረድእ በመንገድ እያለ የአረማውያን የቤተ ጣዖታቸው ካህን ሲወርድ አገኘውና ድምፁን ከፍ አድርጐ «አ! ሰይጣን ከየት ትመጣለህ?» አለው። ያም የአረማውያን ካህን ተመልሶ መጣና ያንን ረድእ እስኪሞት ድረስ ደበደበው፤ በትሩንም ቀምቶት መንገዱን ቀጠለ። ጥቂት እንደ ተጓዘ አባ መቃርዮስ ያንን የጣዖት ካህን አገኘውና ወደ ርሱ ሮጥ ብሎ፤ «አንተ በመንገድ የደከምክ ሰው እንዴት ነህ?» ሲል ሰላምታ ሰጠው። ያም የአረማውያን ካህን በጣም ተደንቆ «በዚህ መልክ ሰላም ትለኝ ዘንድ ከእኔ ምን መልካም ነገር አገኘህ?» ሲል ጠየቀው። አባ መቃርዮስም «አንተማ ራስህን በራስህ ማድከምህ ሳይታወቅህ ራስህን በራስህ ታደክመዋለህ» አለው።

ያም የአረማውያን ካህን «በሰላምታህ ልቤ ተነካቷል። ከሰላምታህም የእግዚአብሔር ሰው መሆንህን ዐውቄአለሁ፤ የሚገርመው ግን አንድ የማይረባ መነኩሴ መንገድ ላይ አግኝቶ ሰደበኝ፤ እኔም ለመሞት የሚያበቃውን ዱላ አቀመስኩት» ብሎ ለመቃርዮስ መለሰለት።

አባ መቃርዮስም ተደበደበ የተባለው የእርሱ ረድእ መሆኑን ዐወቀ:: ያም ካህን በመቃርዮስ እግር ሥር ተደፋና «መነኩሴ ካላደረግከኝ በቀር አልተውህም» አለው:: ከዚያም ያ ረድእ ተደብድቦ ወደ ተጣለበት ሥፍራ መጡ:: በትከሻቸው ተሸክመውም በተራራው ላይ ወዳለው ቤተ ክርስቲያን ወሰዱት:: በዚያ ተራራ የሚገኙ አበው መቃርዮስና የአረማውያኑ ካህን በአንድነት ሲመጡ ባዩ ጊዜ ተደነቁ:: ያንንም ሰው አመነኰሱት፤ በርሱም ምክንያት ብዙ አረማውያን ተጠመቁ:: መቃርዮስም «አንዲት ክፉ ቃል መልካሙን ሰው እንኳ ክፉ ታደርገዋለች፤ አንዲት መልካም ቃል ግን ክፉውን ሰው መልካም ታደርገዋለች» ይል ነበር::

15. አንድ ጊዜ አባ መቃርዮስ ከበኣቱ ውጭ እያለ ሌባ መጣና ያለውን ንብረት ሁሉ በግመል ላይ ይጭን ጀመር:: አባ መቃርዮስ ሲመጣ የቀረውን ንብረት በመጫን ሌባውን ረዳው:: ሌባው ዕቃውን ሁሉ ጭኖ ሲያበቃ ግመሏን ሊያስነሣት ሞከረ:: ነገር ግን እምቢ አለችው:: አባ መቃርዮስም ወደ በኣቱ ገብቶ አንዲት የተረሳች መኰትኰቻ አመጣና «ወንድሜ ግመሏ ይህንንም መውሰድ ፈልጋ ይሆናል» ብሎ ጫነለት:: ከዚያም ግመሏን እንድትንሣ አዘዛት:: ግመሏም ትእዛዙን አክብራ በመነሣት ጥቂት ከተራመደች በኋላ መልሳ ተቀመጠች:: ከዚያ በኋላ ግን ዕቃው ሁሉ እስኪወርድ ድረስ አልነሣም አለች::

16. ልጄ ሆይ ጌታን ለማገልገል ስትነሣ ነፍስህን ለተጋድሎ አዘጋጃት:: ልብህን አጽናው:: ማንኛውንም ነገር በትዕግሥት ተቀበለው:: በየቦታው ማንኛውንም ነገር በመልካም ተቀበለው:: ማንኛውም ነገር ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር አይፈጸምምና:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የምትሻ ነፍስ ከሁሉም በላይ ትዕግሥትን፣ጽናትንና ተስፋን ገንዘብ ለማድረግ መጋደል አለባት:: ከዲያብሎስ ዘዴዎች አንዱ በመከራችን ሰዓት እንድንፈዝ ማድረግ ነው:: በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን ተስፋ እናሚጥጣለን:: እግዚአብሔር በርሱ ተስፋ የምታደርግን ነፍስ እግዚአብሔር አይረዳኝም እስከትል ድረስ በመከራ እንድትንገላታ አይተዋትም:: ቅዱስ ጳውሎስ «ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው:: ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል::» (1ኛቆሮ.10፥13):: ብሏልና፤ ሰይጣን ነፍስን የሚፈትናት በሚፈልገው መጠን ሳይሆን እግዚአብሔር በፈቀደለት መጠን ነው:: በበቅሎ ላይ፣ በአህያ ላይ፣ በግመል ላይ ምን ያህል ሸክም መጫን





እንዳለበት ባለቤታቸው ያውቃል:: ሸክላ ሠሪውም በእሳት ውስጥ ረዥም ጊዜ ማቃጠል እንዳለበት ያውቃል:: በሌላም በኩል በሚገባ ከመጠንከራቸው በፊት ከእሳት እንዳይወጡም ያደርጋል:: ሰው ስለ ገንዘቡ ይህን ያህል ካወቀ እግዚአብሔርማ ምን ያህል ያውቅ፥ በርግጥም በእያንዳንዷ ነፍስ ላይ መጫን ያለበትን የፈተና መጠን ያውቃል፤ ስለዚህም እያንዳንዱን ለመንግሥት ሰማያት ብቁ ያደርገዋል::

17. አባ መቃርዮስ በሚያስተዳድረው በገዳመ አስቄጥስ ታዖሚጦስ የተባለ መነኩሴ ነበረ:: ታዖሚጦስ ከገዳሙ እየወጣ መንደር ይውል ነበር:: ጉዳዩን ሌሎች መነኰሳት ለአባ መቃርዮስ መጥተው ነገሩት:: አባ መቃርዮስ ግን «ልጄ ንጹሕ ነውና ስሙን በከንቱ አታጥፉ» ብሎ መለሳቸው:: አባ መቃርዮስ ዝም ሲለው ጊዜ አንድ ቀን ታዖሚጦስ በመንደር ያለች ወዳጁን አስከትሏት ወደ ገዳሙ መጣ:: መነኰሳቱም ለአባ መቃርዮስ ነገሩት:: አባ መቃርዮስ የመነኩሴው ድፍረት ለመሸፈን የሚያስቸግር በመሆኑና ለሌሎችም ክፉ አርአያ ስለሚሆን ብዙ መነኩሳትን አስከትሎ ድምፅ እያሰማ ወደ ታዖሚጦስ በኣት ሔደ::

ታዖሚጦስ አባ መቃርዮስ ወደ እርሱ እንደ መጣ ሲያውቅ በልጅቱ ላይ ቅርጫት ደፋባት:: መቃርዮስ ግን የተሰወረውን ይመለከት ነበርና የሆነውን ዐወቀ:: ስለዚህም በቅርጫቱ ላይ ተቀምጦ «ፈልጓት» አላቸው:: ተከትለውት የመጡት መነኮሳት ቢፈልጉ አጧት:: አባ መቃርዮስም «ንጹሑን ልጄን ለምን ታሙታላችሁ? በሉ ውጡ፣ የማጫውተው ነገር አለኝ» አላቸውና ወጡ:: መነኩሳቱ ከወጡ በኋላ «ልጄ እንዴት ሆነህ ትኖራለህ?» አለው:: «በአንተ ጸሎት ጾር ጠፍቶልኛል» ሲል ታዖሚጦስ መለሰ:: አባ መቃርዮስም «እኔ በሰማንያ ዘመኔ አልጠፋልኝም» አለው::

ወዲያውም «ልጄ ሆይ፥ ፈጣሪህ ባንተ ላይ ከመፍረዱ በፊት በራስህ ላይ ፍረድ» አለው:: ታዖሚጦስም «ብፈራህ ነው እንጂ በልጂቱ ላይስ ቅርጫት ደፍቼባታለሁ:: በቅርጫቱም ተቀምጠህበታል» አለው:: አባ መቃርዮስም ልጅቱን ከቅርጫቱ ውስጥ አውጥቶ «ለምን ይህን አደረግሽ?» አላት:: «እርሳቸው አመጡኝ፤ ምን ላድርግ?» አለችው:: ታዖሚጦስንም «ካሁን በኋላ ውለህ ተመገብ፣ የዮሐንስ ወንጌልን አታስታጉል» ብሎት መክሮት ሔደ:: አባ መቃርዮስ ከበኣቱ ወጥቶ ሲሔድ ድንጋዮች እየተከተሉት «መቃርዮስ በምድር ላይ እንደ አምላክ ሆነ» ብለው አመሰገኑት::

# አባ እንጦንስ

1. አባ እንጦንስ በበረሓ እያለ በትካዜ ይዋጥ በብዙ ፆርም ይፈተን ነበር። በዚህም የተነሣ «እግዚአብሔር ሆይ÷ ለመዳን ብዬ ወደዚህ መጣሁ፤ ነገር ግን እነዚህ ክፉ ሐሳቦች ሊተውኝ አልቻሉም። ምን ባደርግ ይሻለኛል? እንዴትስ መላቀቅ እችላለሁ?» ሲል ጸለየ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከበኣቱ ወጣ ሲል አንድ እርሱን የመሰለ ሰው በሥራ ተጠምዶ ተመለከተ። ከዚያም ደግሞ ያ ሰው ተነሥቶ ሲጸልይ አየ፤ እንደገና ተመልሶ ተቀመጠና ሰሌን መታታት ጀመረ፤ ቀጥሎ ደግሞ ተነሥቶ ጸለየ። ያ ሰው ለአባ እንጦንስ ሥርዓተ ምንኩስናን ለማስተማር የተላከ መልአክ ነበር። መልአኩ «እንዳሳየሁህ ብታደርግ ትድናለህ» ብሎ ሲናገር አባ እንጦንስ ሰማው። በዚህ ጊዜ አባ እንጦንስ በደስታና በጥብዓት ተሞላ። ከዚያ በኋላ እንደተመለከተው ያደርግ ጀመር።

2. አንድ ጊዜ አባ እንጦንስ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያስብ ጀመር። እግዚአብሔርንም «አንዳንዶች ለምን በወጣትነታቸው ሌሎችስ እጅግ በጣም አርጅተው ይሞታሉ? አንዳንዶች ሀብታም ሌሎችስ ድኾች ለምን ይሆናሉ?» በማለት ጠየቀው። በዚህ ጊዜ «እንጦንስ ሆይ÷ ሐሳብህ ስለ ራስህ ብቻ ይሁን፤ እነዚህ ነገሮች አንተን አይመለከቱህም፤ በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ አትግባ፤ ስለ እነርሱ ማወቅም ላንተ ዋጋ አይጨምርልህም» የሚል ድምፅ ሰማ።

3. ወንድሞች አባ እንጦንስን «እግዚአብሔርን ደስ እናሰኘው ዘንድ ምን እናድርግ?» ብለው ጠየቁት። እርሱም «የምነግራችሁን ነገር ልብ አድርጉ፤ ማንም ሁኑ ማን ዘወትር እግዚአብሔርን በፊታችሁ አድርጉት፤ የምትሠሩትን ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል መሠረት ፈጽሙት፤ የትም ቦታ ኑሩ፤ በቀላሉ ግን ያን ቦታ አትልቀቁት።» እነዚህን ሦስቱን ብታደርጉ መልካም ይሆንላችኋል አላቸው።

4. አባ እንጦንስ አባ ጴሜን የተባለውን አባት እንዲህ አለው፤ «ለሰው ልጅ ታላቁ ነገር በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ስለ በደሉ መውቀስና እስከ መጨረሻዋ ሕቅታ ድረስ ፈተና ሊጠፋ አለመቻሉን ማሰብ ነው።»

5. አባ እንጦንስ «በፈተና ያላለፈ ሰው መንግሥተ ሰማያትን








አባ እንጦንስ እና አባ ጳውሊ

አይወርስም፣ ያለ ፈተናም ማንም አይድንም» ይል ነበር።

6. አባ ፓምቦ የተባለው አባት አባ እንጦንስን «ምን ባደርግ መልካም ነው?» ብሎ ጠየቀው። «በሠራኸው የጽድቅ ሥራ አትተማመን፣ ስላለፈው አትጨነቅ፣ አንደበትህንና ሆድህን ተቆጣጠር።» አለው።

7. አባ እንጦንስ እንዲህ አለ፦ «አንድ ጊዜ ጠላት ዲያብሎስ በዓለም ላይ የዘረጋቸውን ወጥመዶች ሁሉ ተመለከትኩና ከዚህ ሁሉ ወጥመድ በምን ማምለጥ ይቻላል? ብየ ጮህኩ። አንድ ድምፅም «በትኅትና» ሲል መለሰልኝ።

8.አንዳንዶች ሰውነታቸውን በምንኩስና ቀንበር ያሠቃዩታል፤ ነገር ግን ልቡናቸው ከዓለም ስላልተለየ ከእግዚአብሔር ርቀው ይኖራሉ።

9. ከውኃ የወጣ ዓሣ ወዲያው እንደሚሞተው ሁሉ ከበኣታቸው ወጥተው የሚባዝኑ መነኮሳት የነፍሳቸውን ሰላም ያጣሉ። ዓሣ ወደ ውኃው ለመመለስ እንደሚፋጠን መነኮሳትም ወደ በኣታቸው ለመመለስ መፋጠን አለባቸው፤ ከበኣት ወጥተን በቆየን ቁጥር ዐይነ ልቡናችን ይታወራልና።

10. ከሰው ርቀ በብሕትውና የሚኖር ሰው ከሦስት ፈተናዎች መራቅ ይችላል፦ ከማየት፣ ከመናገር፣ ከመስማት። ለርሱ የሚቀረው ፈተና አንድ ነው። ያም የፍትወት ፆር ነው።

11. አንድ ጊዜ አንድ አዳኝ ሰው አባ እንጦንስን ከወንድሞች ጋር ሲጫወት ተመለከተውና ተገረመ። እንዴት እንዲህ ያደርጋል ብሎም በልቡ አሰበ። አባ እንጦንስም ጠራውና «በደጋንህ ላይ ቀስት ወድረህ ሠንዝር» አለው። ሠነዘረ። «ድገም» አለው። ደገመ። «ሠልስ» አለው። ያን ጊዜ አዳኙ ከዚህ በላይ ደጋኔን ከወጠርኩት ይሰበርብኛል ሲል መለሰ። «አየህ፦ - እዚህም ተመሳሳይ ነው። ወንድሞችን ከልክ በላይ ከወጠርናቸው ይሰበሩብናል። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ወደ ታች ወርዶ ፍላጐታቸውን መጠበቅም ተገቢ ነው» አለው።

12. አባ እንጦንስ ድንቅ ተአምራትን ስለሚሠራ አንድ ወጣት መነኩሴ ሰማ። ያ ወጣት መነኩሴ ወደ አባ እንጦንስ ለሚመጡ አረጋውያን የዱር አህያዎችን አዝዞ ይዘዋቸው እንዲሔዱ ማድረጉን የመጡት አበው ነገሩት። እርሱ ግን «እኔስ ይህ ሰው መልካም ነገሮችን የተጫነች መርከብን ይመስለኛል፤ ወደ ወደቡ መድረሱን ግን እንጃ» አላቸው። ከዚያም ፀጉሩንና ጺሙን እየነጨ ያለቅስ ጀመር።





አርድእቱም «አባ ለምን ታለቅሳለህ?» ሲሉ ጠየቁት። «ታላቁ የቤተ ክርስ ቲያን ዓምድ ወደቀ /ወጣቱን መነኩሴ ማለቱ ነው/» አላቸው። «ሒዱና የሆነውን ጠይቁት» ብሎ ላካቸው። አርድእቱም ያን መነኩሴ በበኣቱ ውስጥ ሰሌን ላይ ተቀምጦ ስለ ፈጸመው ኃጢአት ሲያለቅስ አገኙት። እርሱም «ለአባ እንጦንስ እግዚአብሔር ዐሥር የንስሐ ቀናት ይሰጠኝ ዘንድ ጸልይልኝ በሉት» አላቸው። ይሁን እንጂ በአምስተኛው ቀን ዐረፈ።

13. አንድ ጊዜ መነኩሳት ስለ አንድ መነኩሴ እያመሰገኑ ለአባ እንጦንስ ነገሩት። ያ መነኩሴ በመጣ ጊዜ ምስጋና የሚቀበለውን ያህል ሲሰድቡት ምን ያህል እንደሚታገሥ ለማረጋገጥ በክፉ ቃል ተናገረው። መነኩሴው ግን አብዝቶ ተቀየመ። በዚህ ጊዜ አባ እንጦንስ «አንተ ከውጭ በልዩ ልዩ ጌጥ የተዋበ ውስጡን ግን ሌቦች የዘረፉት መንደር ትመስላለህ» አለው።

14. አንድ ጊዜ አረጋውያን ወደ አባ እንጦንስ መጡ። ከመካከላቸውም አባ ዮሴፍ የሚባል አባት ነበረ። አባ እንጦንስ ይፈትናቸው ዘንድ ከመጽሐፍ አንድ ዐንቀጽ አውጥቶ «ምን ማለት ነው?» ብሎ ከታናሹ እስከ ታላቁ ጠየቃቸው። ሁሉም የየራሳቸውን ሐሳብ ተናገሩ። አባ እንጦንስ ግን «ሁላችሁም አላወቃችሁትም» አላቸው። ወደ አባ ዮሴፍ ዞር ብሎ «አንተስ ምን ትላለህ?» አለው። አባ ዮሴፍም «አላውቀውም» አለ። «በእውነት አባ ዮሴፍ መልሱን አገኘው» ሲል ተናገረ።

15. አንድ ጊዜ ወንድሞች ከገዳመ አስቄጥስ ተነሥተው አባ እንጦንስን ለማየት ወጡ። በጀልባ ሲጓዙም አንድ አረጋዊ አገኙ። ወንድሞች ግን ማን እንደሆነ አላወቁትም ነበር። በጀልባዋ ተቀምጠው ስለ አበው፣ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ስለሚሠሩት ሥራ ይነጋገሩ ነበር። ያ አረጋዊ ግን በአርምሞ ይጓዝ ነበር። ወደ ባሕሩ ዳርቻ ሲደርሱ ያም አረጋዊ አብሮ ወረደ። ወደ አባ እንጦንስ በኣት ሲጓዙም አብሮ ተጓዘ። ከበኣቱ ሲደርሱ አባ እንጦንስ «ይህን የመሰለ አባት አብሯችሁ መኖሩ ታድላችኋል» አላቸው። ያንንም አረጋዊ «ብዙ ጥሩ ጥሩ ወንድ ሞችን ይዘህልኝ መጣህ» አለው። አረጋዊው ግን «ጥሩዎች መሆናቸው የማይካድ ነው። ነገር ግን ለቤታቸው በር የለውም፤ ማንም ደስ ያለው ሰው ወደ ጋጣው ገብቶ አህያዋን መፍታት ይችላል» አለው። ያም ማለቱ እነዚህ ወንድሞች ወደ ልባቸው የመጣውን ሁሉ ይናገሩታል ማለቱ ነው።

16. አንድ ወንድም በዓለም ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድኾች ሰጠና ለግል መጠቀሚያው ብቻ ጥቂት አስቀርቶ ወደ አባ እንጦንስ መጣ።

ያደረገውንም ሁሉ ነገረው:: አባ እንጦንስም «መነኩሴ ለመሆን ከፈለግክ ሔደህ ያስቀረኸውን ሽጥና ከመንደሩ ሥጋ ገዝተህ ገላህን በርሱ ሸፍንና ና» አለው:: ያም ወንድም እንደታዘዘው ሥጋ ገዝቶ በገላው ላይ ለብሶት መጣ:: በመንገድም ውሾች ከብበው ነከሱት፤ አሞ ራዎችም አሠቃዩት:: ወደ አባ እንጦንስ ሲደርስ በታዘዘው መሠረት መሥራቱን ጠየቀው:: ያም ወንድም ውሾች የነከሱትን ቁስሉን ለአባ እንጦንስ አሳየው:: አባ እንጦንስም «ዓለምን ከናቁ በኋላ ለራሳቸው አንዳች የሚያስቀሩ መነኰሳት ጦርነት በሚከፍቱባቸው አጋንንት በዚህ መልክ ይሠቃያሉ» አለው::

17. በአባ ኤልያስ ገዳም የሚኖር መነኩሴ ድቀት አገኘውና መነኩሳቱ ከገዳም አባረሩት:: እርሱም ወደ አባ እንጦንስ ዘንድ ሔዶ ለጥቂት ጊዜ ከተቀመጠ በኋላ ወደ ገዳሙ መልሶ ላከው:: ነገር ግን ገዳማውያኑ መልሰው አባረሩት:: ያም ወንድም ወደ አባ እንጦንስ በድጋሚ መጣ:: አባ እንጦንስም «አንዲት ጀልባ በባሕሩ ውስጥ ተሰበረች፣ የጫነችውንም ዕቃ ሁሉ አጣች:: ከዚያም በብዙ መከራ ወደ ወደቡ ደረሰች:: ነገር ግን በብዙ ጭንቀት ወደቧን ያገኘችውን ጀልባ እናንተ መልሳችሁ ወደ ባሕሩ ልትመልሷት ትፈልጋላችሁ?» ሲል መልእክት ላከባቸው:: ያን ጊዜ ተጸጽተው ያን መነኩሴ ተቀበሉት::

18. ሦስት አበው በየዓመቱ ወደ አባ እንጦንስ ይመጡ ነበር:: ሁለቱ ስለ አጋጣሚቸው ፈተናና ስለ ነፍሳቸው ድኅነት ከአባ እንጦንስ ጋር ይወያዩ ነበር:: ሦስተኛው ግን ሁልጊዜ በዝምታ ያዳምጥ ነበር:: ከብዙ ጊዜ በኋላ አባ እንጦንስ «በየጊዜው ልትጐበኘኝ ትመጣለህ፤ ነገር ግን ምንም ነገር ጠይቀኸኝ አታውቅም» አለው:: ያም አባት «አባ ሆይ÷ ለእኔ አንተን ማየት ብቻ ይበቃኛል» አለው::

19. አንድ አረጋዊ አባት ቅዱሳን አባቶችን ያሳየው ዘንድ እግዚአብሔርን ለመነው:: እግዚአብሔርም ከአባ እንጦንስ በቀር ሁሉንም አሳየው:: ይመራው የነበረውን መልአክ «አባ እንጦንስ የት አለ?» ሲል ጠየቀው:: ያም መልአክ «እግዚአብሔር ባለበት ሥፍራ በዚያ አባ እንጦንስ አለ» አለው::

20. አንድ ጊዜ አባ እንጦንስ ከቁስጥንጥንያው ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ወደ ቁስጥንጥንያ እንዲመጣ መልእክት ደረሰው:: ልሒድ ወይስ ልቅር በሚለው ሐሳብ ውስጥ እያለ ረድኡን «ምን ትመክረኛለህ?» ሲል ጠየቀው:: ያም ረድእ «ከሔድክ እንጦንስ ትባላለህ፤ እዚህ ከቆየህ ግን አባ እንጦንስ ትባላለህ» አለው:: አባ እንጦንስም ምክሩን ተቀብሎ ቀረ::





21. አባ እንጦንስ እንዲህ ይል ነበር፤ «ዘወትር በዐይንህ ፊት ፈሪሐ እግዚአብሔር ይኑር፤ ሕይወትና ሞት የሚሰጠውን አዘክረው:: ዓለምንና በዓለም ያለውን ሁሉ ጥላው፤ ከሥጋ የሚመጣውን ደስታና ሰላም አትሻ፤ ለዚህኛው ኑሮ ሙትና ለእግዚአብሔር ሕያው ሁን፤ለእግዚአብሔር ቃል የገባኸውን አትርሳ፤ ያም በፍርድ ቀን ካንተ ይፈለግብሃል:: ረኀብን በጸጋ ተቀበለው፤ ተጠማ፤ ተራቆት፣ ንቁና በሐዘን የምትኖር ሁን:: በልቡናህ አልቀስና ጩኽ፤ ለእግዚአብሔር የምትመች መሆን አለመሆንህን ፈትን፤ሥጋህን ቀጥተህ ነፍስህን ታድናት ዘንድ::»

22. «የጋለ ብረትን ለመቀጥቀጥ የሚነሣ ሰው አስቀድሞ በብረቱ ምን ለመሥራት እንዳሰበ መወሰን አለበት፤ መጥረቢያ፣ ሰይፍ፣ ወይስ ማጭድ? እኛም በምን ዓይነት የሕይወት መስመር ፍሬ ለማፍራት እንዳሰብን አስቀድመን ልቡናችንን ማዘጋጀት አለብን::»

23. «ታዛዥነትና ተዐቅቦ በአንድነት ሲገኙ ሰውን በአራዊት ላይ ሥልጣን ይሰጡታል::»

24.አባ እንጦንስ አባ ጳውሊን ሊጠይቀው በሔደ ጊዜ አባ ጳውሊን «እስኪ ይህ ሥርዓት ምንኩስና ከእኔ በኋላ ይቀራል ወይስ ይቀጥላል የሚለውን ከእግዚአብሔር ጠይቅልኝ?» አለው:: አባ ጳውሊም በጸሎት እግዚአብሔርን ጠየቀለት:: ከጸሎቱ በኋላ የአባ ጳውሊ ገጽ በደስታ ተመላ:: አባ እንጦንስም «ምን አየህ?» ብሎ ጠየቀው:: አባ ጳውሊም «ነጫጭ ርግቦች አንተ እየመራኻቸው በጠፈር ላይ ሲሔዱ አየሁ» አለው:: አባ እንጦንስም «ምንድን ናቸው? ሲል ጠየቀው:: «በቆብ የምትወልዳቸው ንጹሐን ጻድቃን መነኮሳት ናቸው» አለው:: አባ እንጦንስም «እስኪ ደግመህ አመልክትልኝ» ብሎ ለመነው:: በድጋሚ ሲጸልይ የአባ ጳውሊ ፊቱ በሐዘን ተመላ:: «ምነው?» ሲል አባ እን ጦንስ አባ ጳውሊን ጠየቀው:: «በክንፋቸው ላይ ጥቁር መልክ የተቀላቀ ለባቸውን ርግቦች አየሁ» አለው:: «እነዚህ ደግሞ ምንድን ናቸው?» ሲል አባ እንጦንስ ጠየቀ:: «ጽድቅና ኃጢአት እየቀላቀሉ የሚሠሩ መነኮሳት ናቸው» አለው:: «እስኪ ለሦስተኛ ጊዜ አመልክትልኝ» አለና ለመነው:: አባ ጳውሊም ጸለየለት:: በዚህ ጊዜ አባ ጳውሊ ድምፁን ከፍ አድርጐ ጮኾ አለቀሰ:: አባ እንጦንስም «ምነው ምን ሆንክ?» አለው:: «እንደ ቁራ ጠቁረው አየኋቸው» ሲል መለሰለት:: «ምንድን ናቸው?» ቢለው «ሹመት ፈላጊዎች፣ ገንዘብ ወዳጆች፣ በጠዋቱ ከመኳንንቱ ጋር ለማዕድ የሚቀመጡ፣ በፍጻሜ ዘመን የሚነሡ ኃጥአን መነኮሳት ናቸው»አለው:: አባ እንጦንስም፤«ንስሐ ሳይገቡ በሞት እንዳይወስዳቸው እስኪ እግዚአብሔርን ለምንልኝ»አለው:: ይዚህ መልስ ግን ከአባ ጳውሊ አልመጣለትም::



አባ እንጦንስና አባ ጳውሊ ፤





# አባ ሙሴ ጸሊም[10]

1. አባ ሙሴ ጸሊም በበኣቱ እያለ የፈቲው ፆር ያሠቃየው ነበር:: ፈተናውን ተቋቁሞ በበኣቱ መቀመጥ ስላልቻለ ወደ ገዳሙ አበ ምኔት ወደ አባ ኤስድሮስ ዘንድ ሔደና «በበኣቴ መቀመጥ አልቻልኩም» አለው:: አባ ኤስድሮስም ወደ በኣቱ ተመልሶ በዚያው እንዲጸና መከረው:: ሙሴ ግን «ፈጽሞ አልችልም» አለ:: በዚህ ጊዜ አባ ኤስድሮስ ሙሴን ይዞት ከገዳሙ ቅጥር ውጭ አወጣው፤ ከዚያም ወደ ምዕራብ አዞረውና «ተመልከት» አለው:: በዚያ አቅጣጫ የአጋንንት መንጋ ለወረራ ሲዘጋጁና ሲንጫጩ አሳየው:: ቀጥሎ ደግሞ ወደ ምሥራቅ እንዲመለከት አደረገውና እልፍ አእላፍ መላእክት ብርሃን ተጐናጽፈው አሳየው:: ከዚያም «እነዚህ የብርሃን መላእክት ቅዱሳንን ለመርዳት ከእግዚአብሔር የሚላኩ ናቸው፤ እነዚህ ርኩሳን አጋንንት ደግሞ ቅዱሳንን ለመፈተን የሚዘምቱ ናቸው:: የብርሃን መላእክት ኃይል ከአጋንንት ኃይል ይበልጣልና ጸንተህ ተጋደል» ሲል መከረው፤ አባ ሙሴም ወደ በኣቱ ተመለሰ::

2. አባ ሙሴ በገዳመ አስቄጥስ እያለ ከገዳማውያን አንዱ ጥፋት ሠራና ማኅበሩ ለፍርድ ተሰበሰበ:: አባ ሙሴ ግን በጉባኤው ላይ አልነበረም:: ስለዚህ ካህኑ ተልኰ «ና÷ ሁላችንም አንተን እየጠበቅን ነው» አለው:: አባ ሙሴም በሚያፈስስ ከረጢት አሸዋ ሞልቶ ያንንም በጀርባው ተሸክሞ ከኋላው እያፈሰሰ ወደ ጉባኤው አመራ:: ጉባኤተኞቹ ተገርመው ለምን እንደዚህ እንዳደረገ ጠየቁት:: እርሱም «የእኔ ኃጢአቶች በኋላዬ እንደዚህ አሸዋ በዝተው ይፈሳሉ፤ ነገር ግን ላያቸው አልቻልኩም፤ ዛሬ ግን በሌላው ላይ ለመፍረድ መጥቻለሁ::» አላቸው::ይህን ሲሰሙ ዝም አሉ:: ያን ወንድምም በይቅርታ አለፉት::

3. በሌላ ጊዜ በገዳመ አስቄጥስ ያሉ መነኰሳት ተሰበሰቡና የአባ ሙሴን ትዕግሥት ለመፈተን ሲሉ «ይህ ጥቁር መነኩሴ ለምን እዚህ መጣ፣» ብለው ተናገሩት:: እርሱም ዝም አለ:: ጉባኤው ሲበተን «አባ ክፉ ስንናገርህ ምንም ሐዘን አልተሰማህም ነበርን?» ሲሉ ጠየቁት:: «ተሰምቶኛል፣ነገር ግን እንዳልናገረው አንደበቴን ተቆጣጠርኩት» አላቸው::

10 አባ ሙሴ ጸሊም በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሲሆን አስቀድሞ በውንብድና ኑሮ ሕይወቱን ይገፋ ነበር:: በንጥራ አካባቢ በነበሩ መነኮሳት ሕይወት ስለተማረከ ወደ ገዳሙ ገብቶ የምናኔን ሕይወት ጀመረ:: በኋላም በገዳመ አስቄጥስ የገዳሙ አበ ምኔት የነበረው የአባ ኤስድሮስ ደቀ መዝሙር ሆነ:: በአባ መቃርዮስ ምክር ወደ ጴጥራ ሔዶ በተባሕትዎ መኖር ቀጠለ:: ያረፈው በርበሮች አስቄጥስን በ375 ዓ.ም አካባቢ ሲያጠፉ በሰማዕትነት ነው::




ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ሙሴ ጸሊም





4. በአንድ ወቅት በገዳመ አስቄጥስ ጾም ታወጀ:: በዚያ ሳምንት አባ ሙሴን ለማየት ከግብፅ ወንድሞች መጡ:: አባ ሙሴም በእንግ ድነት ተቀበላቸውና ምግብ ያበስልላቸው ጀመር:: የእሳቱን ጢስ የተ መለከቱ ጐረቤቶቹ «አባ ሙሴ ትእዛዝ አፍርሶ ምግብ ያበስላል» ብለው ለገዳሙ ሓላፊዎች ተናገሩ:: ሓላፊዎቹም «አሁን ተውት ሲመጣ እኛው ራሳችን እናናግረዋለን» አሏቸው:: ሓላፊዎቹም አባ ሙሴን ጠርተው ለምን ምግብን እንዳበሰለ ተረዱ:: በቀዳሚት ሰንበት ማኅበሩ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ በዐደባባይ «አባ ሙሴ ሆይ÷የሰውን ትእዛዝ አልጠበቅኸም፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ /እንግዳ ሆኜ መጥቼ ተቀብላችሁኛል የሚለውን/ ግን ጠብቀሃል» ብለው አመሰ ገኑት::

5. አንድ ጊዜ የአካባቢው ገዥ ስለ አባ ሙሴ ዝና ሰምቶ ያየው ዘንድ ወደ ገዳመ አስቄጥስ መጣ:: ይህን የሰማው አባ ሙሴ ሸሽቶ ወደ ጫካ ገባ:: በመንገድም ላይ የገኘው መልእክተኞች አገኙትና «እባክህ አባ ሙሴ የት እንዳለ በአቱን አሳየን?» አሉት:: «ከርሱ ምን ትሻላችሁ፤እርሱ 'ኮ ቂላቂል ነው» አላቸው:: ይህን የሰማው የአካባቢው ገዥ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መጣና የሆነውን ሁሉ ለአገልጋዮች ነገራ ቸው:: «ብዙ ሰዎች ስለ አባ ሙሴ ሲያወሩ ሰምቼ ለማግኘት መጥቼ ነበር፤ በመንገድ ላይ ያገኘነው አንድ አረጋዊ ሰው ግን የአባ ሙሴ በኣት የት እንደሆነ ስንጠይቀው ከርሱ ምን ትሻላችሁ፤ እርሱ 'ኮ ቂላ ቂል ነው አለን» ብሎ ነገራቸው:: አገልጋዮቹም በጣም ተናደዱና «ምን ዓይነት አረጋዊ ሰው ነው ስለ ቅዱሱ ይህን የሚናገር» ብለው ጠየቁት:: «ትልቅ፣ ጠቆር ያለ፣ አሮጌ ልብስ የለበሰ ነው» አላቸው:: አገልጋዮቹም ተገርመው «ይህማ ራሱ አባ ሙሴ ነው፤ይህን ያለህ ሊያ ገኝህ ስላልፈለገ ነው» አሉት:: የአካባቢው ገዥም ከአባ ሙሴ ሁኔታ ከንቱ ውዳሴን ስለ መሸሽ ትልቅ ትምህርት ተምሮ ተመለሰ::

6. አንድ ጊዜ በገዳመ አስቄጥስ ወንድሞች አብረውት እያሉ አባ ሙሴ «ተመልከቱ በርበሮች ገዳማችንን ሊያጠፉ እየመጡ ነው:: ተነሡና ሽሹ» አላቸው:: እነርሱ ግን «አባ አንተስ አትሸሽምን?» ሲሉ ጠየቁት:: አባ ሙሴም «እኤማ ይህችን ቀን ለብዙ ዘመናት ስጠብቃት ኖሬያለሁ:: ጌታ በወንጌሉ «ሰይፍን የሚያነሡ በሰይፍ ይጠፋሉ» ያለው ቃል (ማቴ.25÷52) ይፈጸማል::» አላቸው:: እነርሱም «እኛም አንሸሽም፤ አብረን እንሞታለን እንጂ» አሉት:: አባ ሙሴም «ያ ለእኔ ረብ የለውም፤ ሁሉም ሰው ለየራሱ ይወስን» ብሎ መለሰላቸው:: በዚያ

ለነበሩት ሰባት ወንድሞች «በርበሮች ወደ ገዳሙ ደጅ እየደረሱ ነው» ብሎ ነገራቸው። ወዲያውም በርበሮቹ ደርሰው ገዳማውያኑን በሰይፍ መቷቸው። ከሰባቱ ደቀመዛሙርት አንዱ ሸሽና በተቀለለው ሰሌን ውስጥ ተደበቀ፤ወዲያውም ሰባት አክሊላት ሲወርዱላቸው ተመለከተ።

7. አባ ሙሴ በአት ሠርቶ ወደ ጴጥራ ሲሔድ በአካባቢው ውኃ ስላልነበረ ተጨንቆ ነበር። አንድ ድምፅ «ሒድ፥ ስለምንም ነገር አትጨነቅ» አለው። ስለዚህም በዚያ መኖር ጀመረ። አንድ ቀን በጴጥራ እያለ አበው ሊጐበኙት መጡ። የነበረችው ውኃ ጥቂት ነበረ ችና በርሷ ምግባቸውን አበሰለ። የሚያጠጣቸው ግን አላገኘም። ስለዚህ ወደ ውጭ እየወጣ ውኃ ይሰጠው ዘንድ እግዚአብሔርን ይለምን ነበር። በመጨረሻ ዝናብ ዘነበና የውኃ ማጠራቀሚያዎቹን ሁሉ ሞላ ቸው። እነዚያ አባቶችም «ተወጣና ትገባ የነበረው ለምን እንደሆነ እባክህ ንገረን» አሉት። «እናንተ በእንግድነት ስትመጡ ውኃ አልነ በረኝም፤ ስለዚህ ያንተን አገልጋዮች ወደ እኔ ልከሃቸዋል፣ ነገር ግን ውኃ የለኝም፤ ስለዚህ እባክህ ውኃ ስጠኝ እየልኩ እግዚአብሔርን ለመለመን ነበር» አላቸው።

*አባ ሙሴ ለአባ ጴሜን የላካቸው ሰባቱ ትእዛዛት*

1. መነኩሴ ለባልንጀራው መሞት አለበት፤ በምንም መንገድና በምንም ሁኔታ በወንድሙ ላይ መፍረድ የለበትም።

2. መነኩሴ ማንንም እንዳይጐዳ ሥጋን ከመተው በፊት ለማንኛውም ነገር መዋቲ መሆን አለበት።

3. መነኩሴ በልቡ በደለኛ መሆኑን ካላሰበ፤ እግዚአብሔር አይሰ ማውም። አንድ ወንድም «ይህ ምን ማለት ነው?» ብሎ ጠይቆት ነበር። «አንድ ሰው ስለ ራሱ ጥፋት በማሰብ ልቡ ከተጠመደ የባልን ጀራውን በደል የሚያይበት ዐይን አይኖረውም» አለው።

4. የሰው ምግባር ከጸሎቱ ጋር ካልሠመረ በከንቱ ይደክማል፤ አንድ ወንድምም «በምግባርና በጸሎት መካከል ያለው ሥምረት ምን ድን ነው?» ብሎ ጠይቆት ነበር። «እኛ እንዳይሆኑብን የምንጸልይ ባቸውን ነገሮች መፈጸም የለብንም፤ ሰው የልብ መሻት ካለው ጌታ ያንን ተቀብሎ የጸሎቱን ግዳጅ ይፈጽምለታል» አለው። ያም ወንድም «አንድ መነኩሴ የሚቀበላቸውን መከራዎች እንዲያልፍ ርዳታ የሚያ ገኘው እንዴት ነው?» አለው። አባ ሙሴም በቅዱሱ መጽሐፍ





«እግዚአብሔር መጠጊያችንና ኃይላችን፣ ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው» ተብሎ ተጽፏል አለው /መዝ.45÷1/።

5. አባ ሙሴ «ሰው በራሱ ላይ የሚወስነው ጾምና የሰውነት ቁጥጥር ዋጋው ምንድን ነው?» አለ። መልሰም «እነርሱማ ነፍስን ትሑት ያደር ጓታል። በመዝሙር «ድካሜን እና መከራዬን እይ፤ ኃጢአቴንም ሁሉ ይቅር በለኝ» ተብሎ እንደ ተጻፈ (መዝ.24÷18)። ስለዚህም ነፍስ እነዚ ህን መከራዎች ከተቀበለች እግዚአብሔር ይቅር ይላታል።

6. «ሰው ወደ ልቡ የሚመጣውን ፍትወትና ክፉ ሐሳብ ለመቋቋም ምን ማድረግ አለበት?» ብሎ አባ ሙሴ ጠየቀ፤ ሲመልስም «ማልቀስና የእግዚአብሔርን ረዳትነት መለመን አለበት፤ ከዚያም በተረዳ ልቡና ሆኖ ከጸለየ ፈተናው ይታገስለታል። በመጽሐፍ «እግዚአብሔር ረዳቴ ነው አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል?»(መዝ.117÷6)ተብሎ እንደ ተጻፈ።

7. አንድ ወንድም አባ ሙሴን «አንድን አገልጋይ ባጠፋው ጥፋት የተነሣ ጌታው መታው። አገልጋዩ ምን ማለት አለበት?» ብሎ ጠየ ቀው። አባ ሙሴም «አገልጋዩ ብፁዕ ከሆነ፣ አጥፍቻለሁና ይቅር በለኝ ማለት አለበት።» አለው። «ሌላ አይጠበቅበትምን?» ሲል ያ ወንድም ጠየቀው። «አይጠበቅበትም፣ ለጊዜው ለጥፋቱ ሓላፊነቱን ወስዶ አጥፍ ቻለሁ ካለ ጌታው ይቅር ይለዋል። የዚህ ሁሉ ዓላማው በባልንጀራ ላይ ላለመፍረድ ነው። በእውነቱ ጌታችን የግብፅን በኩራት ሁሉ ሲመታ ሰው ያልሞተበት አንድም ቤት አልነበረም» አለና መለሰለት። ያም ወንድም «ምን ማለት ነው?» አለው። «ሁላችንም የየራሳችንን ጥፋቶች ካየን የባልንጀራችንን ለማየት ዕድል አንሰጥም። በራሱ ቤት ሰው የሞተበት በጐረቤቱ ልቅሶ ለማልቀስ አይሔድም።

ለባልንጀራ መሞት ማለት ለራስ ጥፋት ትኩረት በመስጠት፤ የሌ ላውን ጥፋት ከቁም ነገር አለመቁጠር ነው። ማንንም አትጉዳ፣ በማንም ላይ ክፉ አታስብ፣ ክፉ የሚሠራውን ሰው አትናቀው፤ በባልንጀራው ላይ ክፉ በሚሠራ ሰው ላይ አትተማመን፤ በባልንጀራው ላይ ክፉ ከሚሠራ ሰው ጋር አትደሰት፤ ለባልንጀራ መዋቲ መሆን ማለት ይህ ነው። በማ ንም ላይ አትማረር፤ ነገር ግን «ሁሉንም እግዚአብሔር ያውቃል።» በል። ከሚያማ ሰው ጋር አትተባበር፣ በሐሜቱም አትደሰት፤ ወንድሙን የሚያ ማውን ሰውም አትጸየፈው። አትፍረድ÷ ማለት ትርጉሙ ይህ ነው። በማ ንም ላይ የጥላቻ ሐሳብ አይኑርህ፤ ጥላቻ ልብህን እንዲያሸንፈውም አትፍ ቀድለት። ባልንጀራውን የሚጠላውን አት ጥላው፤ ሰላም ማግኘት ማለት ይህ ነው። የሚከተለውን እያሰብክ ልብህን አበርታው «ፈተና በቶሎ ያል ፋል፣ሰላም ግን ለዘለዓለም ይጸናል፤በእግዚአብሔር ወልድ ጸጋ። አሜን።»

## አባ መጣዕ

1. ሰው ወደ እግዚአብሔር በቀረበ መጠን የገዛ ኃጢአቱ ይታየዋል:: ነቢዩ ኢሳይያስም እግዚአብሔርን ባየው ጊዜ «ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ» ብሏል /ኢሳ.6÷5/::

2. ልጅ እያለሁ አንድ ቀን መልካም ነገር አደርግ ይሆናል ብዬ ለራሴ እነግረው ነበር:: እነሆ ሸመገልኩ፣ እስካሁን ግን መልካም የሚባል ነገር አላደረግኩም::

3. ሰይጣን በየትኛው ፈተና ነፍስን እንደሚያሸንፋት አያውቅም:: እርሱ ምን እንደሚበቅል ሳያውቅ የሚዘራ ሞኝ ገበሬ ነው:: ስለዚህም በፍትወት ይፈትናታል፣ በሐሜት ይፈትናታል፣ በሌሎችም ፈተናዎች እያቀያየረ ይፈትናታል፣ ነፍስ ልትወድቅበት የምትችለውን የፈተና ዓይነት እስኪያገኘው ድረስ ሁሉንም ይሞክራል::

4. አባ ያዕቆብ ወደ አባ መጣዕ በአት ሔዶ ሲመለስ «ወደ ሴላስ ገዳም መሔዴ ነው» አለው:: አባ መጣዕም «እባክህ አባ ዮሐንስን ሰላም በልልኝ» አለው:: አባ ያዕቆብ ወደ አባ ዮሐንስ በመጣ ጊዜ የአባ መጣዕን ሰላምታ አቀረበለት:: አባ ዮሐንስም «ተንኰል የሌለበት የእስራኤል ሰው ማለት አባ መጣዕ ነው» አለው:: ከዓመት በኋላ ወደ አባ መጣዕ ተመልሶ አባ ዮሐንስ ያለውን ነገረው:: እርሱም «እኔ ያ አረጋዊ አባት ላለው ነገር የምመጥን አይደለሁም:: ነገር ግን ይህን ዕወቅ:: አንድ አባት ወንድሙን ከራሱ አብልጦ ሲያመሰግን ስትሰማ እርሱ ራሱ ከትልቅ መዓርግ መድረሱን ተረዳ:: ፍጹምነት ማለት ባልንጀራን ከራስ በላይ ማክበር ነውና» አለው::

5. አንድ ወንድም አባ መጣዕን «እባክህ የምክር ቃል ለግሠኝ?» ብሎ ጠየቀው:: «እግዚአብሔር የሚጸጸት ልቡና እና ትሑት ሰብእና እንዲሰጥህ ጸልይ፣ በደልህን አትዘንጋ፣ በሌሎች ላይ መፍረድ ትተህ ራስህን የሁሉም የበታች አድርገህ ቁጠር፣ ከልጅ ጋርና ከመናፍቅ ጋር ጓደኛ አትሁን፤ እንደመጣልህ መናገርን ካንተ አርቅ፣ አንደበትህንና ሆድህን ተቆጣጠረው፣ በጣም ጥቂት ወይን ብቻ ጠጣ፣ አንድ ሰው ስለ አንድ ጉዳይ ሲያወራ አትከራከረው፣ ትክክል ከሆነ «እውነት ነው» በለው:: ትክክል ካልሆነ «የምትናገረውን ታውቀዋለህ» በለው:: ትሕትና ማለት ያ ነው::





## አባ ማርቆስ /የአባ ስልዋኖስ ደቀ መዝሙር/

1. በገዳመ አስቄጥስ የነበረው አባ ስልዋኖስ አባ ማርቆስ የተባለ የጽሕፈት ችሎታ ያለው ረድእ ነበረው:: አባ ማርቆስ ፍጹም ታዛዥ ሰው ስለነበር ከሌሎች ዐሥራ አንድ አርድእት የበለጠ አባ ስልዋኖስን ይወደው ነበር:: ዐሥራ አንዱ አርድእት በዚህ ነገር ያዝኑ ነበር:: በገዳሙ የነበሩ አበው ሁኔታውን ለአባ ስልዋኖስ ነገሩት:: እርሱም «ኑ እንሒድ» አለና የዐሥራ አንዱን አርድእት የበኣታቸውን በር እያንኳኳ «ወንድሜ እገሌ ቶሎ ና እፈልግሃለሁ» ይል ነበር፤ አንዳቸውም ግን ፈጥነው አልወጡም:: ወደ አባ ማርቆስ በኣት መጥቶ «አባ ማርቆስ» ሲለው ገና ድምፁን እንደሰማ ፈጥኖ ወጣ::

አባ ስልዋኖስም በል ሒድ ብሎ ወደ ሌላ ሥራ ላከውና እነዚያን አበው «ዐሥራ አንዱ የት አሉ?» አላቸው:: ከዚያም ወደ አባ ማርቆስ በኣት ገባ:: አባ ማርቆስ አባ ስልዋኖስ ሲጠራው እየጻፈ ነበር:: ነገር ግን የመምህርን ድምጽ ሲሰማ «አሜን» የሚለውን ቃል እንኳን ሳይፈጽመው ሮጦ መውጣቱን አዩ:: እነዚያ አባቶችም «በእውነት የምትወደውን ወደድነው፣ ጌታም እንደ እኛ ይወደዋል» አሉት::

2. አባ ስልዋኖስ ወደ ሶርያ ሊሔድ በፈለገ ጊዜ ረድኡ አባ ማርቆስ «አባ አንተን ልተውህ አልወድድም፤ ይህንንም ቦታ ትቼ ልሔድ አልወድድም፣ እባክህ በዚህ ቦታ ሦስት ቀን ብቻ ቆይልኝ» ሲል ለመነው:: በሦስተኛው ቀን አባ ማርቆስ ዐረፈ::

## አባ ሚላስዮስ

አባ ሚላስዮስ በአንድ ቦታ ሲያልፍ ሰዎች አንድን መነኩሴ ሰው ገድለሃል ብለው የአካባቢው ሰዎች ይዘውት አገኘ:: አባ ሚላስዮስ ወደ ዚያ መነኩሴ ጠጋ ብሎ ከጠየቀው በኋላ በሐሰት እንደተያዘ ዐወቀ:: ሰዎቹንም «የተገደለው ሰው የት አለ» ብሎ ጠየቃቸው:: እነርሱም አሳዩት:: አባ ሚላስዮስም «ጸልዩ» ብሏቸው ወደ ሬሳው ተጠግቶ እጁን ወደ ሰማይ ዘርግቶ ጸለየ:: ያን ጊዜ የሞተው ሰው ተነሣ:: ሁሉም እያዩት «የገደለህ ማን እንደሆነ ንገረን?» አለው:: የሞተውም ሰው «ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔጄ ለካህኑ ገንዘብ ሰጠሁት፣ በዚህ ጊዜ ገንዘቡን ተቀበለኝና ገደለኝ:: ከዚያም ወደ አባ በኣት ወረወረኝ፣ እባካችሁ ገንዘቡን ወስዳችሁ ለልጆቼ ስጡልኝ» አላቸው አባ ሚላስዮስም «በል ሒድ እግዚአብሔር እስኪያስነሣህ ተኛ»አለው:: ያም ሬሳ ተመልሶ አንቀላፋ::

# አባ ማርቆስ ግብፃዊ

1. አባ ማርቆስ ግብፃዊ ለሠላሳ ዓመታት ከበኣቱ ሳይወጣ የሚኖር መነኩሴ ነበር። በአካባቢው የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ካህን በየጊዜው ወደ እርሱ እየሔደ ሥጋ ወደሙን ያቀርበው ነበር። ዲያብሎስ የዚህን አባት ጽናት አይቶ ቀናበት። ስለዚህም አባ ማርቆስ ካህኑን እንዲጸየፈው በማድረግ ሊፈትነው አሰበ። ሰይጣንም ርኩስ መንፈስ ያደረበትን ሰው ወደ አባ ማርቆስ ላከው። ያም ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ጸልይልኝ የሚል መስሎ ቀረበና «የካህኑ ኃጢአት ሰነፈጠኝ፣ ከዛሬ ጀምሮ ወደ አንተ አታቅረበው» ብሎ ጮኸ። አባ ማርቆስም «ሁሉም ሰው ከበደል ለመራቅ ይሮጣል፣ አንተ ግን ይዘኸው መጣህ፣ እንዳይፈረድብህ አትፍረድ ተብሏል (ማቴ.7÷1)።» ኃጢአተኛ ቢሆንም እግዚአብሔር ይፈውሰዋል፣ ትፈወሱ ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ ተብሏልና (ያዕ.5÷16) አለው። ይህንን ብሎ ሲጸልይ በሰውየው ላይ ያደረው ሰይጣን ትቶት ኰበለለ። ሰውየውንም በሰላም አሰናበተው።

ካህኑም እንዳስለመደው ሲመጣ አባ ማርቆስ በደስታ ተቀበለው። ጌታም የአባ ማርቆስን የልቡን ንጽሕና ተመልክቶ የሚከተለውን ተአምር አሳየው። ካህኑ ሊያቀርበው ጠረጴዛውን ባዘጋጀ ጊዜ «ከሰማይ መልአከ እግዚአብሔር ወርዶ እጁን በካህኑ ራስ ላይ አኖረው። ካህኑም የእሳት ዓምድ መሰለ። ይህንን ሳይ እደነቅ ጀመር። በዚህ ጊዜ «ምድራዊ ንጉሥ ባለሚሎቹ የቆሸሸ ልብስ ለብሰው በፊቱ እንዲቆሙ አይሻም፣ በክብር ተጐናጽፈው እንጂ፣ ሰማያዊው ንጉሥማ የተቀደሱ ምስጢራትን ለማገልገል በሰማያዊው ክብር ፊት የሚቆሙትን ካህናት እንዴት የበለጠ አይቀድሳቸውም» የሚል ድምጽ ሰማ። አባ ማርቆስ በካህኑ ላይ ባለመፍረዱ ለዚህ ክብር በቃ።

# አባ ኔለስ

1. በአንተ ላይ ክፉ በሠራብህ ወንድም ላይ ለበቀል የሰነዘርከው ነገር ሁሉ በጸሎት ጊዜ በልቡናህ እየመጣ ይፈትንሃል።

2. ጸሎት የደግነት ፍሬ፣ የቁጣም አለመኖር ነው።

3. ጸሎት የትካዜና የውሳጣዊ ሐዘን ማስታገሻ ነው።

4. ሒድ ያለህን ሁሉ ሽጥና ለድሆች መጽውት፣ ከዚያም





መስቀሉን ተሸከም፣ ራስህን ካድ፣ በዚህ መንገድ ያለ ሁከት ልትጸልይ ትችላለህ።

5. ነገሮች ሁሉ አንተ እንደምትፈልጋቸው እንዲሆኑ አትመኝ፣ እግዚአብሔርን እንደሚያስደስቱት እንጂ። እንደዚህ ከሆነ የማትታወክና በጸሎትህም ጊዜ አዘውትረህ የምታመሰግን ትሆናለህ።

6. ራሱን ከሁሉም ተለይቶ የተጣለ እንደሆነ አድርጐ የሚያስብ መነኩሴ ብፁዕ ነው።

7. ውሳጣዊ ሰላምን የሚሻ መነኩሴ ለጠላቱ ጦር የማይበገር ሆኖ ይኖራል፣ ከሕዝብ ጋር እየተቀላቀለ የሚኖር ከሆነ ግን ባለማቋረጥ የሰይጣንን ቡጢዎች ይቀምሳል።

# አባ ኔጥራስ

የአባ ስልዋኖስ ረድእ የነበረው አባ ኔጥራስ በደብረ ሲና በበኣቱ እያለ ለሰውነቱ የሚያስፈልጉትን ነገሮች በተመለከተ ራሱን በጥንቃቄ ይይዘው ነበር። በኋላ ጳጳስ ሲሆን ግን ለሥጋው በሚያስፈልጉት ነገሮች ግድ የለሽ ሆነ። ረድኡ አንድ ጊዜ «አባ በገዳም እያለን ይህን የመሰለውን ተባሕትዎና ትሕርምት አታደርገውም ነበር» ሲል ጠየቀው። አባ ኔጥራስም በገዳም እያለሁ ውሳጣዊ ሰላምና ድኅነት ነበረኝ፣ ስለዚህ በአንድ በኩል እንዳልታመም በሌላ በኩልም ከሚገባኝ በላይ እንዳልጠግብ ስል ብቻ ሰውነቴን እጠብቀው ነበር። አሁን ግን በዓለም ውስጥ በምቾት ወንበር ላይ ነኝ። ብታመም እንኳን ተከታትሎ የሚያሳክመኝ አለ። ስለሆነም ይህን ሁሉ የተቀጠቀጠ ትሕርምት የምፈጽመው በውስጤ ያለውን መነኩሴ እንዳላበላሸው ብዬ ነው» አለው።

# አባ ኔቅጣስ

አባ ኔቅጣስ ስለ ሁለት ወንድሞች የሚከተለውን ተናግሯል። አንድ ጊዜ ሁለት መነኰሳት በአንድነት ለመኖር ወሰኑ። አንደኛው በልቡ «ወንድሜ የሚፈልገውን ሁሉ አደርግለታለሁ» ሲል ቃል ገባ። ሌላውም «የወንድሜን ፈቃድ እፈጽማለሁ» ሲል በልቡ ወሰነ። በዚህ ውሳኔያቸው ለብዙ ዘመናት በስጋሥነት ኖሩ። በዚህ ፍቅራቸው የቀና ሰይጣን ሊለያያቸው ተነሣ። በበኣታቸው በር ላይ ቆመና ለአንደኛው ርግብ ለሌላኛው ቁራ መስሎ ታየው። በዚህ ጊዜ አንደኛው መነኩሴ «ርግቧን አየሃት?» ሲለው ሌላኛው ደግሞ «ርግብ አይደለችም ቁራ



የባቱ ደ/ተ/ቅ/ሚካኤል
እና ቅ/ጊዮርጊስ
ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት ቤ/መጻሕፍት

ነው» ሲል መለሰ። «ርግብ ናት» «ቁራ ነው» ክርክር ጀመሩ። ክርክሩ ወደ ጭቅጭቅ፣ ጭቅጭቁም ወደ ድብድብ አመራና ደም በደም እስኪ ሆኑ ድረስ ተደባደቡ። በመጨረሻም ተለያዩ። ከሦስት ቀናት በኋላ ወደ ልባቸው ተመልሰው ሁለቱም ተፀፀቱ። ይቅርታም ተጠያየቁ። ሁለቱም በተለያየ መልክ አንድ ዓይነት ነገር ማየታቸውንና ልዩነታቸው የመጣው ከነገሩ ሳይሆን ከዲያብሎስ መሆኑን ተረዱ። እስከ ዕለተ ሞታቸውም አብረው ያለ ፀብ ኖሩ።

# አባ ዞዮስ

አንድ ወንድም አባ ዞዮስን «ሦስት ቁራጭ ዳቦዎች በቀን ብመገብ ብዙ ነውን» ብሎ ጠየቀው። አባ ዞዮስም «ወደ ገዳም የመጣኸው በአውድማ እህል ልትወቃ ነውን» አለው። ያም ወንድም አስከትሎ «ሦስት ብርጭቆ ወይን ብጠጣስ ብዙ ነውን?» አለው። አባ ዞዮስም «ሰይጣን ባይኖር ኖሮ ብዙ አይሆንም ነበር፤ ነገር ግን ሰይጣን አለና ብዙ ነው፤ ወይን በፈቃደ እግዚአብሔር ለሚኖሩ መነኮሳት ዋና የፆር መነሻ ነው» አለው።

# አባ ዛንትያስ

አባ ዛንትያስ «ውሻ ከእኔ ይሻላል፤ እርሱ ለሌሎች ፍቅር አለው፤ በማንም ላይም አይፈርድም» ይል ነበር።

# አባ አሊምፐስ

በሴልስ ገዳም የነበረው አባ አሊምፐስ የፍትወት ፆር ይፈትነው ነበር። ሰይጣን በሐሳቡ እየመጣ «ሒድ ውጣና ሚስት አግባ» ይለውም ነበር። እርሱም ከበአቱ ወጥቶ ወደ ጭቃው ሔደና ከጭቃው የሴት ምስል ሠርቶ «አሊምፐስ ሆይ ሚስትህ ይቻት፤ አሁኑ እርሷን ለማስተዳደር ጠንክረህ መሥራት አለብህ» እያለ በጉልበት ሥራ ተጠመደ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም እንደገና ሒዶ ትንሽ ምስል ሠራ። ከዚያም «ሚስትህ ልጅ ወልዳለችና ለምግቧና ለልብሷ ከበፊቱ በባሰ ሁኔታ መሥራት አለብህ» እያለ ይደክም ጀመር። በመጨረሻም ሥራው ሲበዛበት ለልቡናው «ይህን መከራ ከዚህ በላይ መሸከም አልችልም» አለ። ልቡናውም «እንግዲያው ሚስት መፈለግህን ተው» አለው። ወዲያው እግዚአብሔር ፆሩን አራቀለት።





# አባ አርሲሲየስ

ሰው ልቡን ካልጠበቀ የሰማውን ሁሉ መርሳትና መዘንጋት ይጀምራል፤ ስለሆነም ጠላት በርሱ ውስጥ ቦታ ያገኛል፣ ገልብጦም ይጥለዋል። ልክ ዘይት ተሞልቶ እንደሚያበራ መብራት ማለት ነው። ዘይቱን መጨመርን በዘነጋህ ቁጥር መብራቱ እየቀነሰ ይመጣና ጨለማ ቦታውን ይረከበዋል። ከዚህ የባሰው የሚፈጠረው ደግሞ አይጥ ወደ መብራቱ ተጠግታ ክሩን መብላት ከጀመረች ነው። ዘይቱ አልቆ መብራቱ ባልጠፋ ይህንን ማድረግ አትችልም። ነገር ግን መቅረዙ ያለ ብርሃን ብቻ ሳይሆን ያለ ሙቀት መቅረቱን ስታይ ክሩን ለመጐተትና መብራቱን ለመጣልም ጥረት ታደርጋለች። ከሸክላ የተሠራ መብራት ከሆነ ይሰበራል፤ ከነሐስ የተሠራ ከሆነ ግን የቤቱ ጌታ መልሶ ዘይት ይሞላዋል። በተመሳሳይ ሁኔታም ልባችንን ካልጠበቅን መንፈስ ቅዱስ ቀስ በቀስ ሙቀቱ ጭራሽ እስኪለየን ድረስ ከሕይወታችን ውስጥ ይጠፋል። ጠላትም የነፍስን ግለት ያቀዘቅዘዋል፤ ክፋትም ሰውነትን ያበላሸዋል። ነገር ግን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ጠንካራ ግንኙነት ኖሮት በዝንጋኤ ውስጥ የሚሰቃይ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በቸርነቱ እርሱን መፍራትን እና የፍርዱን ሰዓት ማስታወስን በልቡናው ያስቀምጥበታል፤ ልብ ንቁ እንዲሆን ያዘጋጀዋል፤ እስኪጐበኘው ድረስም ራሱን በእስተ ማማኝ ሁኔታ ለወደፊቱ እንዲጠብቅ ያደርገዋል።

# አባ ጴሜን[11]

1. አባ ጴሜንና አርድእቱ ወደ ገዳመ አስቄጥስ ከመምጣታቸው በፊት በመላው ግብፅ ዝናና ተሰሚነት የነበረው አንድ አረጋዊ ነበር። አባ ጴሜንና አርድእቱ ወደ ገዳመ አስቄጥስ ከመጡ በኋላ ግን ሕዝቡ አረጋዊውን እየተወ ወደ አባ ጴሜን መሔድ ጀመረ። በዚህ ሁኔታ ያ አረጋዊ ያዝን ነበር። ሁኔታውን የተመለከተው አባ ጴሜን «ይህንን አረጋዊ አባት ምን እናድርግለት፤ ሕዝቡ እርሱን ትቶ ከንቱ ወደ ሆነው ወደ እኛ በመምጣቱ አዝኗል፤ ታድያ እርሱን ለማስደሰት ምን እናድርግ?» አለ። «ቡሉ ምግብ አዘጋጁ፣ ወይንም በአቁማዳ ጫኑ፣ ወደ እርሱ ሔደንም አብረነው እንብላ» አለ። ተነሥተውም ተጓዙ። ሲደርሱም በሩን አንኳኩ። የአረጋዊው ረድእም ከፈተ። አባ ጴሜንም «ከእርሱ እጅ በረከት ለማግኘት መምጣቱን ለአረጋዊው ንገርልን» አለው። ያም ረድእ ወደ አረጋዊው ገብቶ ነገረው። እርሱ ግን «ሒዱ

11 ከተሰባሰቡት የአበው ንግግሮች መካከል አንድ ሰባተኛው ከአባ ጴሜን ጋር የተያያዘ ነው።

ጊዜ የለኝም በላቸው» አለው:: ረድኡም የተባለውን ለአባ ጴሜን ነገረው:: አባ ጴሜን ግን «እርሱን አግኝተን ካልተባረክን በቀር አንመለስም» ብሎ መለሰለት:: ምንም እንኳን ወበቁ ቢያስቸግርም ለረዥም ሰዓታት ጸንተው ባሉበት ቆዩ:: ያም አረጋዊ አባት ትዕግሥታቸውንና ትኅትናቸውን ተመልክቶ ተጸጸተ:: በሩንም ከፈተላቸው:: ወደ ውስጥም ገብተው አብረውት ተመገቡ:: በዚያ ጊዜ «በእውነቱ ስላንተ የሰማሁት ነገር እውነት ነበር፤ ሥራህ ሁሉ ከእኔ በመቶ እጥፍ የሚበልጥ ነው» ብሎ አረጋዊው አባ ጴሜንን አመሰገነው:: ከዚያ ሰዓት ጀምሮም ወዳጆቸው ሆኑ::

2. በአንድ ገዳም ውስጥ አንድ ወንድም ተሳሳተ:: በዚያ ገዳም ውስጥ ለብዙ ዓመት ዘግቶ የሚኖር አንድ ባሕታዊ ነበር:: የገዳሙ አበምኔት ወደዚህ ባሕታዊ ዘንድ ሔዶ ስለዚያ ወንድም ነገር አጫወተው:: ባሕታዊውም «አስወጥተህ ስደደው» ሲል ፈረደበት:: አበ ምኔቱም እንደተባለው አደረገ:: ያም የተባረረ ወንድም ከገዳሙ ወጥቶ በአንድ ዋሻ ውስጥ ገብቶ ያለቅስ ጀመር:: አባ ጴሜንን ለማየት የሚሔዱ ወንድሞች በመንገድ ሳሉ ድምፁን ሰምተው ወደ ዋሻው ገቡና አጽናኑት:: ከዚያም ወደ አባ ጴሜን ዘንድ ሔዱና የሆነውን ሁሉ ለአባ ጴሜን አወሩለት:: አባ ጴሜንም ተመልሰው እንዲሔዱ አደፋፈራቸውና «አባ ጴሜን ሊያይህ ይፈልጋል በሉት» ብሎ ላካቸው:: ሔደውም አመጡት::

አባ ጴሜን ያ ወንድም ልቡ በሐዘን መጐዳቱን ተመልክቶ ከመቀመጫው ተነሥቶ አቀፈው፣ ራራለት፤ ወደ ገበታም ጋበዘው:: ከወንድሞች አንዱን ወደ ባሕታዊው እንዲህ ሲል ላከው «ስለ አንተ ዝና እየሰማሁ ለብዙ ዘመናት ላይህ እናፍቅ ነበር፤ ነገር ግን ደካሞች በመሆናችን ልንገናኝ አልቻልንም:: እግዚአብሔር ቢፈቅድ አንተም ጊዜ ካለህ እባክህ እኔ ያለሁበት ዘንድ ናና እንገናኝ::» ባሕታዊውም «እግዚአብሔር ካላመለከተው በቀር አይልክብኝም ነበር» ብሎ ወደ አባ ጴሜን ተጓዘ::

እዚያ እንደ ደረሰም እርስ በርስ እጅ ተነሣሡና ዐረፍ አሉ:: አባ ጴሜንም «ሁለት ሰዎች በአንድ ቦታ ይኖሩ ነበር:: ሁለቱም የሚወዷቸው የየራሳቸው ወዳጆች ሞቱባቸው:: በዚህ ጊዜ አንደኛው የራሱን ሬሳ ትቶ ወደዚያኛው ሬሳ በመሔድ ያለቅስ ጀመር» አለው:: ባሕታዊውም ይህንን ሲሰማ ነገሩ ገባውና ተፀፀተ፤ የፈጸመውን ስሕተትም ተረዳ:: አባ ጴሜንንም «ጴሜን ሆይ አንተ ወደ መንግሥተ





ሰማያት ሔደሃል፤ እኔ ግን ወደ ምድር ወርጃለሁ» አለው::

3. አንድ ጊዜ የአካባቢው ገዥ ከአካባቢው ሰዎች አንዱን ያዘው:: ሰዎች ሁሉ እየመጡ አባ ጴሜንን ሔዶ እንዲያስፈታላቸው ይለምኑት ነበር:: በመጨረሻ «ሦስት ቀን ስጡኝና እሔዳለሁ» አላቸው:: በዚያ ጊዜ አባ ጴሜን ወደ ልዑል እግዚአብሔር «ጌታ ሆይ ይህን ጸጋ እባክህ አትስጠኝ፣ ያለበለዚያ ነገ ሰው ሁሉ እየመጣ ሰላም አይሰጠኝም» ሲል ለመነ:: ከዚያም አባ ጴሜን ወደ አገረ ገዥው ሔዶ ለመነው:: ገዥው ግን «አባ ለቀማኛ ታማልዳለህን?» ብሎ ከለከለው:: ይህም አባ ጴሜንን አስደሰተው::

4. የሚያስተምር ነገር ግን የሚያስተምረውን የማይፈጽም ሰው ማለት ለብዙዎች ለጥማቸው ማርኪያ፣ ለንጽሕናቸውም ምንጭ እንደ ሚሆን ነገር ግን ራሱን እንደሚያጠራ ምንጭ ማለት ነው::

5. አንደበቱ ዝምተኛ የሆነ፣ ነገር ግን በልቡናው ወንድሞቹን የሚያወግዝ ሰው እርሱ ባለማቋረጥ የሚያጉረመርም ሰው ነው:: በሌላም በኩል ከጠዋት እስከ ማታ ሲናገር የሚውል፣ ነገር ግን በአርምሞ የሚኖር ሰው አለ:: ምክንያቱም ይህ ሰው የማይረባ ነገር አይናገርምና::

6. አንድ ወንድም ወደ አባ ጴሜን መጥቶ «ብዙ ሐሳቦች ወደ ልቡናዬ እየመጡ እያስቸገሩኝ ነው» ብሎ ጠየቀው:: አባ ጴሜንም ወደ ውጭ አወጣውና «ተንፍስና አየር ወደ ውጭ አስወጣ» አለው:: በኃይል ተነፈሰ:: «ነገር ግን አየር መልሰህ አታስገባ» አለው:: «አልችልም» አለ:: «አየህ» አለው አባ ጴሜን፣ «ያር ወደ ልቡናህ እንዳይመጣ ማድረግ አትችልም:: መከላከል ግን ትችላለህ::» አለው::

7. በመዝሙር «ቀይ ድብ ወደ ውኃ ምንጭ እንደምትናፍቅ አቤቱ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች»(መዝ.41÷1) ይላል:: በበረሃ የምትኖረው ቀይ ድብ በበረሃ የሚገኙት ተሳቢዎችን ከለቃቀመች በኋላ መርዛቸው ስለሚያቃጥላት ወደ ውኃ ምንጭ ለመንዝ ትፋጠናለች:: የመርዙን ቃጠሎ ለማስታገስ ትችል ዘንድ:: ለመነኮሳትም እንዲሁ ነው:: በበረሓ ተቀምጠው በአጋንንት መርዝ ሲነድዱ ይከርማሉ፤ በዕለተ ቀዳሚትና በዕለተ ሰንበትም ወደ ምንጭ ቤተ ክርስቲያን መጥተው ከሥጋውና ከደሙ ለመቀበል ይፈጥናሉ:: የክፉውን ምሬት ያጠፉ ዘንድ::

8. «ማንም ለሌላው በክፉ ፋንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ

(1ኛተሰ.5÷15) ማለት ምን ማለት ነው?» ሲሉ አባ ጴሜንን ጠየቁት። አባ ጴሜንም «ኃጢአት የሚሠራው በአራት ደረጃ ነው። መጀመርያ በልብ፣ ከዚያ በገጽታ፣ ከዚያ በቃላት፣ በአራተኛ ደረጃ በተግባር ነው። ክፉን በክፉ ያለመመለስ የተባለው አራተኛው ደረጃ ነው። ልብህን ንጹሕ ካደረግከው ገጽታህ ውሳጣዊውን ክፉ ስሜት አይገልጠውም፤ ወደ ገጽታህ ከወጣብህ ደግሞ በንግግር ላለማውጣት ታገለው፤ ከዐቅምህ በላይ ሆኖ ለመናገር ከጀመርክም ክፉን በክፉ ተግባር ከመመለስህ በፊት ንግግርህን ቆረጠው» አለው።

9. ንቅሐ ልቡና፣ ራስን ማወቅና ራስን መግዛት የነፍስ መሪዎቿ ናቸው።

10. ጤስ ንቦችን ከቀፎ እንደሚያባርራቸው፣ ከተግባራቸውም ውስጥ ጣፋጭነትን እንደሚወስድባቸው ሁሉ ሥጋዊ ቅንጦትም ከነፍስ ውስጥ ፈሪሐ እግዚአብሔርን ያስወጣዋል። ተግባርዋንም ሁሉ ያባክንባታል።

11. ስሜታዊ ከሆኑ ነገሮች መሸሽ አለባችሁ። ስሜታዊ ከሆኑ ነገሮች ጋር የሚታገል ሰው በሐይቅ ጠርዝ ላይ የቆመን ሰው ይመስላል፤ ጠላት በቀላሉ በገፋው ጊዜ ወደ ሐይቁ ይገባልና። ነገር ግን ከስሜታዊነት ርቆ የሚኖር ከሆነ ከጥልቁ ሐይቅ ርቆ የሚኖርን ሰው ይመስላል። ጠላት ወርውሮ ወደ ሐይቁ ሥር ሊከትተው ቢገፋው እንኳን በእያንዳንዱ ርምጃው እግዚአብሔር ርዳታውን ይልክለታል፤ ለጠላቱም በቀላሉ የማይወረወር ይሆንበታል።

12. የፈቃድ ድህነት፣ ተጋድሎና ድሎት የለሽ ሕይወት የምናኔ መሣርያዎች ናቸው። በመጽሐፍ «ኢዮብ፣ ኖኅ እና ዳንኤል ካሉ በዚያ አለሁ» ተብሎ ተነግሮአል /ሕዝ.14÷14/። ኖኅ በፈቃድ ድህነትን መቀበሉን፣ ኢዮብ ተጋድሎን፣ ዳንኤልም ድሎት የለሽ ሆኖ መኖርን ያመለክታሉ። ስለሆነም በሰው ውስጥ እነዚህ ሦስቱ ከተገኙ ጌታ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ ይኖራል።

13. «ወንድሜ ሲያጠፋ ብመለከተው ልሸፍንለት ይገባልን» ሲል አንድ ወንድም አባ ጴሜንን ጠየቀው «የወንድሞቻችንን ጥፋት በሠወርን ጊዜ እግዚአብሔርም የኛን ይሠውርልናል፤ የወንድሞቻችንን ጥፋት በገለጥን ጊዜ ደግሞ የኛን ይገልጥብናል» ሲል መለሰለት።

14. አንድ ጊዜ አባ ፔየስ ለአንድ ሰው የነገረውን አባ ጴሜን እንዲህ ገለጠው። «ልቡናየ ደንዳናና ፈሪሐ እግዚአብሔር የሌለው ሆነ፣ ምን ላድርግ?» ሲል አንድ ወንድም አባ ፔየስን ጠየቀው፤ አባ ፔየስም «ሒድና ፈሪሐ እግዚአብሔር ካደረበት ሰው ጋር አብረህ ኑር፤ እርሱ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ያስተምርሃልና» ብሎ መለሰለት።

15. «መነኩሴ ሁለት ነገሮችን ድል ካደረገ ከዚህ ዓለም ተጽዕኖ ነፃ ይሆናል» አለ አባ ጴሜን። «ምንና ምን ናቸው?» ሲል አንድ ወንድም ጠየቀው። «ሥጋዊ ቅንጦት እና ከንቱ ውዳሴ ናቸው» ብሎ መለሰ።

16. አብርሃም የተባለው የአባ አጋቶን ረድእ «አጋንንት እንዴት ነው የሚዋጉኝ?» ሲል ጠየቀው። አባ ጴሜንም «አጋንንት አንተን ይዋጉሃልን?» ሲል ጠየቀውና «እኛ የሥጋ ፈቃዳችንን /የራሳችንን ፈቃድ/ እስከ ፈጸምን ድረስ አጋንንት እኛን አይወጉንም፤ የራሳችን ፍላጎቶች አጋንንት ሆነው ይዋጉናል እንጂ፤ እንፈጽማቸው ዘንድ የሚወጉን እነርሱ ናቸው። በርግጥ አጋንንት ማንን እንደሚዋጉ ለማየት ከፈለግክ፣ የሚዋጉት አባ ሙሴ ጸሊምንና እርሱን የመሰሉትን ቅዱሳን ነው» አለው።

17. አንድ ወንድም መጣና «ኃጢአተኛ መሆኑን የሰማሁበት ወንድም ካለ ወደ በአቴ ይመጣ ዘንድ አልወድም፤ በመልካም ምግባሩ የታወቀ ከሆነ ግን ከርሱ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ ነኝ» አለው። አባ ጴሜንም «ለመልካሙ ወንድም ያደረግክለትን ሁለት እጥፍ ለበደለኛው ወንድምህ አድርግለት፤ እርሱ ሕመምተኛ ነውና። በአንድ ገዳም ውስጥ ጢሞቴዎስ የተባለ ባሕታዊ ነበር። በፈቲው ፆር የሚፈተን አንድ ወንድም አለ፣ ምን ላድርገው? ብሎ የገዳሙ አበ ምኔት አባ ጢሞቴዎስን አማከረው። አባ ጢሞቴዎስም አስወጥተህ አባርረው ሲል አበ ምኔቱን መከረው። ልክ ያ ወንድም እንደተባረረ የዚያ ወንድም ፆር ወደ አባ ጢሞቴዎስ ተጋባ። ጢሞቴዎስም መቋቋም አቃተው። «በድያለሁና ይቅር በለኝ» እያለ ሲጸልይ ጢሞቴዎስ ሆይ ይህን ፆር ያመጣሁብህ ብቸኛ ምክንያት በፈተናው ሰዓት ወንድምህን ስለ ናቅከው ነው» የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማ።» ብሎ ነገረው።

18. የተወሰኑ መናፍቃን ወደ አባ ጴሜን መጥተው ከቆዩ በኋላ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ከካህናት አንብሮተ እድ ይቀበላል ሲሉ የሐሰት ወሬ አወሩለት። እስከዚያች ሰዓት ጸጥ ብሎ የነበረው አባ ጴሜን አርድእቱን ጠርቶ «ገበታ አዘጋጁ፣ የሚበሉትን ሰጧቸውና በሰላም አሰናብቷቸው» ሲል አዘዘ።

19. አንድ ወንድም እግዚአብሔርን ስደበው የሚል መንፈስ ይፈት ነው ነበር።ይህንን ፆር ሊቋቋም ስላልቻለ ወደ አባቶች ለምክር ሔደ ። ነገር ግን ጉዳዩን መግለጽ አሳፍሮት ሳይነግራቸው ተመ ለሰ። በኋላም ወደ አባ ጴሜን መጣ። ይሁን እንጂ አውጥቶ መናገር ስላሳፈረው አሁንም ሳይገልጥለት ተመለሰ። ብዙ ጊዜ ወደ አባ ጴሜን እየመጣ ሳይናገር ይመለስ ነበር። አንድ ቀን አባ ጴሜን መጨነቁንና መረበሹን ተመልክቶ «ወንድሜ ሆይ ለብዙ ጊዜያት አንድ ነገር ልትነግረኝ ትመጣለህ፤ ነገር ግን ፈርተህ ትመለሳህ። ንገረኝ?» ሲል ጠየቀው። ያም ወንድም «አጋንንት እግዚአብሔርን ስደበው እያሉ ይፈትኑኛል። ይህ ጉዳይ ስላሳፈረኝ ነው» ብሎ መለሰለት። አባ ጴሜንም «ልጄ ሆይ አትዘን፤ ይህ ክፉ ሐሳብ ሲመጣብህ ይህ ጉዳይ የኔ ጉዳይ አይደለም፤ ሰይጣን ይህ ክፉ ሐሳብ በአንተ ላይ ይቅር፤ ነፍሴ አትፈልገውምና በለው። ምክንያቱም ነፍስ የተጸየፈችው ነገር አብሯት አይዘልቅምና ይጠፋልሃል» አለው። ያም ወንድም በሰላም ሔደ።

20. አባ አሞናስ የተባለው አባት የተናገረውን ጠቅሶ አባ ጴሜን እንዲህ አለ። «ሰው በበኣት ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለበት ሳያውቅ ለመቶ ዓመታት በበኣት ይኖር ይሆናል»

21. ገዳማዊ ኑሮ ሦስት ነገሮች ይፈልጋል÷የመጀመሪያው ትኅትና፤ ሁለተኛው ታዛዥነት፤ ሦስተኛው እና እነዚህ ሁለቱን ህያው የሚያደርጋቸውና የሚያጸናቸው ገዳማዊ ሥራን መሥራት ነው።

22. በክርስትናው ብርቱ የሆነ አንድ ምእመን ወደ አባ ጴሜን ዘንድ መጣ። በዚያ ሰዓት ከአባ ጴሜን ምክር ለመቀበል አርድእት ተሰብስበው ነበር። አባ ጴሜንም ይህንን ምእመን «እባክህ ምከራቸው» አለው። ያም ምእመን አልችልም ብሎ እምቢ አለ። ነገር ግን አባ ጴሜን ባስገደደው ጊዜ «እኔ ዓለማዊ ነኝ፤ አትክልት እየሸጥኩ እተዳደራለሁ። በብዛት ገዝቼ በየመጠኑ እቸረችራለሁ። በርካሽ ገዝቼ በተሻለ ዋጋ እሸጣለሁ። ከዚህ በላይ ለመናገር የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት የለኝም። ስለዚህም አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ።

አንድ ሰው ለወዳጆቹ ወደ ንጉሥ ዘንድ ልሔድ ተጠርቻለሁ አላቸው። የመጀመሪያው ባልንጀራው አብሬህ የመንገዱን እኩሌታ እሔዳለሁ አለው። ሁለተኛው እስከ ንጉሡ ቤተ መንግሥት ድረስ አብሬህ እሔዳለሁ አለው። ሦስተኛውም እስከ ንጉሡ ቤተ መንግሥት አብሬህ እገባለሁ፤ አብሬህ እቆያለሁ፤ ንጉሡን ታገኘው ዘንድም





እረዳሃለሁ፤ ተከስስህ ከሆነም ጥብቅና እቆምልሃለሁ አለው ብሎ ነገራቸው። አርድእቱም «ትርጉሙ ምንድን ነው?» ብለው ጠየቁት። እርሱም የመጀመሪያው ባልንጀራ «ምናኔ» ነው። እርሱም የድኅነትን መንገድ የሚመራ ነው፤ ሁለተኛው «ድንግልና» ነው። እርሱ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያገባን ነው፤ ሦስተኛውና በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የሚሰጠንና ያለ ፍርሐት እንድንቆም የሚያደርገን ምጽዋት ነው ብሎ ተረጐመላቸው።

23. አንድ ወንድም አባ ጴሜንን «ምከረኝ» ብሎ ጠየቀው። «ድስት በእሳት ላይ እያለ ምንም ዓይነት ተባይ ሊቀርበውና ሊያበላሸው አይችልም። ከእሳት ወጥቶ ሲቀዘቅዝ ግን ነፍሳት ሁሉ ለመግባትና ለማበላሸት ይቻላቸዋል። መነኩሴም ከመንፈሳዊ ተግባር ካልራቀ ጠላት የድቀት ምክንያት አያገኝበትም» አለው።

24. አንድ ወንድም «የሚፈታተኑኝን ቁጣንና ፍትወትን እንዴት ልቋቋመው?» ሲል አባ ጴሜንን ጠየቀው። አባ ጴሜንም «ዳዊት አንበ ሳውን አመታው ድቡንም አገደለው ነበር» ብሏል (1ሳሙ.17÷35) ያም ማለት ቁጣን አስወግደው ፍትወትንም አስባብረው ነበር ማለቱ ነው። ስለዚህም እነዚህ ሁለቱ የሚጠፉት በኃይለኛ ተጋድሎ ነው አለው።

25. «ለነገ አትጨነቁ (ማቴ.6÷34) የተባለው ለማን ነው?» ብለው ጠየቁት። አባ ጴሜንም «በፍትወት ፆር ለሚፈተን፤ ነገር ግን ገና ጥንካሬ ለሌለው ሰው ነው። እርሱ ነገ ደግሞ ምን የባሰ ፈተና ይመጣ ይሆን? እያለ መጨነቅ የለበትም። በዚህ ይልቅ «የምፈተነው ዛሬ ብቻ ነው» እያለ በተስፋ ይጽናና።

26. ለሌላው መመሪያ የሚሰጥ ሰው እርሱ ከፈተናዎች የተገላገለ መሆን አለበት። ያለበለዚያ የራሱ ቤት የፈረሰበት ሰው የሌላውን ሊገነባ ቢጓዝ ምን ዋጋ አለው።

27. ከመጠን ያለፈ ነገር ሁሉ የሚመጣው ከአጋንንት ነው።

28.ቤት የሚገነባ ሰው ለግንባታ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ዕቃዎች ከየቦታው ያሰባስባል፤ እኛም መንፈሳዊ ቤት ለመሥራት ከሁሉም በጐ ምግባራት ጥቂት ጥቂት እንሰብስብ።

29. አባ ዮሴፍ ከአባ ይስሐቅ የሰማውን እንዲህ ተናገረ። አንድ ጊዜ ከአባ ጴሜን ጋር ተቀምጨ እያለሁ ገጹ በተመስጦ በርቶ አየሁት። ከተመስጠው ሲመለስ በፊቱ ተደፍቼ «አባ እባክህ የት እንደ ነበርክ ንገረኝ?» ብዬ ነዘነዝኩት። እርሱም «ልቡናየ ከድንግል ማርያም ጋር ነበር። ልክ

በእግረ መስቀሉ ሥር ሆና ስታለቅስ ትታየኝ ነበር። ልክ እንደርሷ ሆኜ ሳለቅስ ብኖር ደስታየ ነው» አለኝ።

30.«መናገር ይሻላል ወይስ አርምሞ» ብለው አባ ጼሜንን ጠየቁት። «ስለ እግዚአብሔር ሲል የሚናገርም መልካም አደረገ፤ ስለ እግዚአብሔር ሲል ዝም የሚልም መልካም አደረገ» ብሎ መለሰ።

31. እነዚህ ሦስቱ ከሁሉም በላይ የሚጠቀሙ ናቸው «ፈሪሐ እግዚአብሔር ጸሎት እና ለባልንጀራ መልካም ነገር መሥራት»

32. አንድ ጊዜ ብዙ አበው የእግዚአብሔር ወዳጅ ወደ ሆነ አንድ ሰው ቤት ሔዱ። ከመካከላቸውም አባ ጼሜን ነበር። በዚያ ሰው ቤት ማዕድ ሲቀርብ ሥጋ ቀረበላቸው፤ ሁሉም ሲበሉ አባ ጼሜን ግን አልተመገበም ነበር። እነዚያ አባቶች ያደረገውን ባወቁ ጊዜ ተገርመው «አባ ጼሜን ሆይ እንዲህ ማድረግህ ደግ ነውን?» ሲሉ ጠየቁት። እርሱም «አባቶቼ ሆይ ይቅር በሉኝ፤ እናንተ ብትመገቡም ማንም አይሰና ከልባ ችሁም እኔ ግን ብመገብ ብዙ አርድእት አሉኝና ይሰናከላሉ፤ አባ ጼሜን ሥጋ ከበላ እኛስ ለምን አንበላም ይላሉ» አላቸው። እነዚያ አባቶችም በማስተዋል ተደነቁበት።

33. ንጉሥ መርቅያን ያጋዘው አባ ዮሐንስ እንዲህ አለ «አንድ ጊዜ አባ ጼሜንን ለማየት ወደ ሶርያ ሔደን ነበር። በዚያም ስለ ልቡና ንጽሕና ልንጠይቀው ፈለግን። ነገር ግን አባ ጼሜን የግሪክ ቋንቋ አይችልም ነበር። አስተርጓሚም አላገኘንም። አባ ጼሜን በዚህ ነገር ማዘናችንን ሲረዳ የግሪክ ቋንቋ መናገር ጀመረ። «የውኃ ጠባይ ለስላሳ ነው፤ የድንጋይ ጠባይ ጠጣር ነው። ነገር ግን ውኃ በጠርሙስ ተደርጎ ከድንጋዩ በላይ ከተያዘና ውኃ የሚያንጠባጥብ ከሆነ፣ ቀስ በቀስ ድንጋዩ መሰባበሩ አይቀርም። ቃለ እግዚአብሔርም ለስላሳ ነው፤ ልቡናችን ደግሞ ጠጣር ነው። ነገር ግን ሰው ቃለ እግዚአብሔርን አዘውትሮ የሚሰማ ከሆነ ልቡናው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለፈሪሐ እግዚአብሔር ቦታ መስጠቱ አይቀሬ ነው» አለን።

34. አንድ ጊዜ አባ ይስሐቅ ወደ አባ ጼሜን ሲመጣ እግሩን እየታጠበ አገኘው። አባ ይስሐቅም «ሌሊት ሥጋቸውን ክፉኛ የሚጐዱትና አካላቸውን በክፉ ሁኔታ የሚይዙት ለምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው። «እኛ አካላችንን እንድንገድለው አልተማርንም፤ ፍትወታችንን እንጂ» ሲል መለሰለት።

35. ያለ እነርሱ ልኖር የማልችል ሦስት ነገሮች አሉ፦ ምግብ፣ ልብስና እንቅልፍ። ነገር ግን በመጠን እንዲሆን መገደብ እችላለሁ።





36. ዳዊት ለኢዮአብ «ከተማዋን በእጅህ እስክታስገባ ድረስ ጦርነቱን ቀጥል» ብሎ ልኮበት ነበር። ከተማ የተባለው የነፍስ ጠላት ነው።

37.ምን እንደተፈጸመ አለማወቅ ወደ ተሻለ ነገር ከመንዝ ያስቀርናል።

38. ጠላት በበዛበት ቦታ የምኖር ከሆነ ብርቱ ወታደር እሆናለሁ።

# አባ ፓምቦ[12]

1. ሊቀ ጳጳስ አባ አትናቴዎስ አባ ፓምቦን ወደ እስክንድርያ ይመጣ ዘንድ ለመነው። አባ ፓምቦ ወደ እስክንድርያ በወረደ ጊዜ አንዲት ዳንሰኛ ተመለከተና ቆሞ አለቀሰ። በዚያ የነበሩት ሁሉ ለምን እንደሚያለቅስ ጠየቁት።«ያስለቀሱኝ ሁለት ነገሮች ናቸው። አንዱ የዚህች ሴት ነፍስ መጥፋት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ይህቺ ሴት ተዳሚዎቿን የምታስደስተውን ያህል እኔ ፈጣሪዬን አለማስደሰቴ ነው» አላቸው።

2. መነኩሴ መልበስ ያለበት ልብስ ከበአቱ አውጥቶ ሲወረውረው እስከ ሦስት ቀን ድረስ ማንም ወድዶት ሊሰርቀው የማይችለውን ልብስ ነው።

3. ልብ ካለህ ትድናለህ።

4. አባ ፓምቦ ቁጹረ ገጽ ሆኖ ይኖር ነበር። ፈገግ ብሎ እንኳን አያውቅም። አንድ ቀን አጋንንት ሊያስቁት ስለ ፈለጉ በእንጨት ፋኖስ ላይ የላባ ክንፎች ሰክተው እያወኩ «ሒድ ሒድ» እየተባባሉ ፋኖሱን ይዘውት በአየር ላይ ሔዱ። ይህን ሲያይ አባ ፓምቦ መሳቅ ጀመረ። ይህን ጊዜ አጋንንት ደስ ብሏቸው «ሃ ሃ ሃ ፓምቦን አሳቅነው» ብለው ጮኹ። «እኔ የሳቅኩት በተግባራችሁ አይደለም፤ ይህ ሁሉ አጋንንት ተሰብስቦ አንዲት ፋኖስ መሸከሙ ምን ያህል ደካሞች እንደሆናችሁ ስላረጋገጠልኝ ነው» አላቸው።

# ጲስጦስ

1. ሰባት ባሕታውያን ሆነን አባ ሲዞስን ለመጐብኘት ሔድን። እርሱ ይኖር የነበረው ቁልዝም በተባለ ቦታ ነው። ምክረን ብለን

12 በ303 ዓ.ም ተወለደ። አባ እሞንን በንጥራ ገዳም መጀመርያ ያገኘው እርሱ ነው። በ340 ዓ.ም ክህነትን ተቀበለ። አባ አትናቴዎስ ወደ እስክንድርያ ይመጣ ዘንድ ጋብዞት ነበር። አባ ጀሮም ከመቃርዮስ እና ከአባ ኤስድሮስ ጋር በአንድነት በግብፅ የገዳማዊ ሕይወት ታላላቅ አበው ብሎ ጠርቷቸዋል። ያረፈው በ373 ዓ.ም አካባቢ ነው

አስጨነቅነው፡፡ እርሱ ግን «ይቅር በሉኝ እኔ ማይም ሰው ነኝ፡፡ ነገር ግን ከአባ አር እና ከአባ አጥሬ ጋር ኖሬያለሁ፡፡ አባ አር ለዐሥራ ስምንት ዓመታት ታማሚ ነበር፡፡ በፊቱ ሰግጄ «እባክህ ምከረኝ?» አልኩት፡፡ አባ አውርም ምን ልነገርህ? ሒድና መልካም መስሎ የታየህን አድርግ፣ ራሱን ወደሚወቅስ እና በሁሉም ነገር ራሱን ወደሚቀጣ ሰው እግዚአብሔር ይመጣል፣ አለኝ»፡፡

አባ አውርና አባ አጥሬ ከአንድ አካባቢ የመጡ ሰዎች አልነበሩም፣ ነገር ግን እስከ ዕለተ ሞታቸው በመካከላቸው ፍጹም ፍቅር ነበር፡፡ የአባ አጥሬ ታዛዥነት ወደር የሌለው ነው፡፡ የአባ አውር ትሕትናም አምሳያ የለውም፡፡ ለብዙ ጊዜያት ሳልለያቸው አብሬ ኖሬያለሁ፡፡ አባ አጥሬ ያደረገውን አንድ ድንቅ ነገርም ተመልክቻለሁ፡፡

አንድ ሰው ዓሣ አመጣላቸው፣ አባ አጥሬም ዓሣውን ለማዘጋጀት በቢላዋ መክታተፍ ጀመረ፡፡ ቢላዋውን በዓሣው ላይ ጥሎ ከመሐል አያለ አባ አውር ጠራው፡፡ «የጀመርኩትን ልፈጽም» ሳይል ሮጦ አቤት አለው፡፡ በዚህም ታዛዥነቱን አደነቅኩ፡፡ «ይህን ታዛዥነት ከየት አገኘኸው?» ብዩ ጠየቅኩት፡፡ እርሱም «ይህ ሀብት የእኔ አይደለም የአባ አውር ነው» አለኝና፡፡ «ና የአባ አውርን ታዛዥነት ተመልከት» አለኝ፡፡ ከዓሣው መካከል የተወሰነውን ባልተገባ ሁኔታ አዘጋጅቶ ለአባ አውር አቀረበለትና «ጣፋጭ ነውን?» አለው፡፡ አባ አውርም «በጣም ልዩ ነው» አለው፡፡

ቀጥሎም በደንብ የተዘጋጀውን አቀረበለትና «አባ አበላሸሁት» አለው «በመጠኑ አበላሽተኸዋል» አለው፡፡ በዚህ ጊዜ አባ አጥሬ «አየህ ይህ አረጋዊ በእውነት ተአዛዚ መሆኑን» አለኝ፡፡ የመጣሁት ይህን የመሰለ ፍቅር እና ታዛዥነት ካለበት ቦታ ነው፣ አሁን የምነግራችሁም ያንን ነገር በተቻለኝ መጠን ለመፈጸም እየታገልኩ መሆኔን ነው አላቸው፡፡

## ጲዮር[13]

1. አባ ጲዮር የሚመገበው እየሔደ ነው፡፡ «ለምንድን ነው እየሔድክ የምትመገበው?» ብሎ አንድ ሰው ቢጠይቀው «መመገብን እንደ ሥራ ሳይሆን እንደ ተጨማሪ ነገር ማሰብ ስለምፈልግ ነው» አለ፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ «ነፍሴ በምግብ ሥጋዊ ደስታ እንዳይሰማት ብዬ ነው» ብሎ መለሰ፡፡

13 አባ ጲዮር በንጥራ የመጀመሪያውን ገዳማዊ ኑሮ ከወጠኑት አበው አንዱ ነው፡፡ አስቀድሞ ከአባ እንጦንስ ታላቁ ጋር ነበረ፡፡ ካህንና በገዳመ አስቄጥስ በተባሕትዎ ለብዙ ዘመን የኖረ አባት ነው፡፡





2. አንድ ጊዜ በገዳመ አስቄጥስ ጉባኤ ተደረገ፡፡ የጉባኤው ዓላማ ጥፋት በፈጸመ በአንድ ወንድም ላይ ለመወያየት ነው፡፡ ተሳታፊዎቹ ሁሉ ሲናገሩ አባ ጲዮር ጸጥ አለ፡፡ በመጨረሻም ወጥቶ ሔደና በጆንያ ሙሉ አሸዋ ሞልቶ በትከሻው፣ በትንሽ ከረጢት ደግሞ ጥቂት አሸዋ ጨምሮ በፊት ለፊቱ ተሸክሞ መጣ፡፡ አባቶችም «ይህ ምን ማለት ነው» ብለው ጠየቁት፡፡ እርሱም «ይህ ከኋላዬ የሞላው አሸዋ የኔ ኃጢአት ነው፡፡ ብዙ ቢሆንም ከኋላ ሸሽጌዋለሁ፣ ስለዚህ አልጨነቅም፣ ይህ ጥቂቱ አሸዋ ደግሞ የወንድሜ በደል ነው፣ ያም በፊቴ ለፊቴ የማየው በመሆኑ በርሱ ላይ በመፍረድ ጊዜዬን አጠፋለሁ፡፡ ይህ ግን ትክክል አይደለም፡፡ የኔን ኀጢአት ከፊት ለፊት ማድረግ ስለዚያም መጨነቅ ይገባል፣ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለኝም መለመን ይገባኛል» አላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የተሰበሰቡት አበው ተነሥተው «በእውነቱ የድኅነት መንገድ ይህ ነው» አሉ፡፡

## አባ ጳውሊ መፍቀሬ ትሕትና

የአባ እንጦንስ ደቀ መዝሙር የነበረው አባ ጳውሊ የሚከተለውን ታሪክ ተናገረ፡፡ አንድ ጊዜ አንድን ገዳም ለመጐብኘት ሔደ፡፡ ከጉባኤ በኋላ ወንድሞች ሁሉ ለጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን ገቡ፡፡ አባ ጳውሊ ከውጭ ሆኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡትን ይመለከት ነበር፡፡ ጌታ የእያንዳንዱን ሰው ልቡና የማወቅን ጸጋ ሰጥቶት ነበር፡፡ እኛ የሰው ፊት የምናየውን ያህል እርሱ የሰዎች ጽድቅና ኃጢአት ተገልጦ ይታየው ነበር፡፡ የሁሉም ፊታቸው አብርቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ጠባቂ መልአካቸው በእነርሱ ይደሰት ነበር፡፡ በዚህ መሐል «አንድ ወንድም ጨለማ ለብሶ ጨለማ ተጐናጽፎ አየሁ አጋንንት በዙርያው ከብበውታል፡፡ ሁሉም ይጫኑት ነበር፡፡ አፍንጫውን ሰንገው ወደ ራሳቸው ይጐትቱት ነበር፡፡ ጠባቂ መልአኩም በሐዘን ተውጠና ራሱን ዝቅ አድርጐ በሩቁ ይከተለው ነበር፡፡» በዚህ ጊዜ በዕንባ ተሞልቼ አለቀስኩ፣ ከቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት የተመለከቱ ወንድሞች ፊቱን ወደ ዕንባ የለወጠውንና በሐዘን ውስጥ የከተተውን ነገር እንዲነግራቸው ወተወቱት፡፡ ሁሉም በኔ ምክንያት ይሆንን? ብለው ፈርተዋልና፡፡ ሁሉም አብሯቸው ወደ ጸሎቱ ይገባ ዘንድ ለመኑት፡፡ አባ ጳውሊ ግን ከእነርሱ ርቆ ከውጭ ተቀመጠ፡፡ ስለዚያ ወንድምም ማልቀስ ቀጠለ፡፡

ጸሎቱ እንዳለቀ የገቡት ሁሉ ሲወጡ በምን ሁኔታ እንደተመለሱ አባ ጳውሊ ሁሉንም መመርመር ጀመረ፡፡ ያንን ጨለማ ለብሶ ቀድሞ ያየውን ወንድም ገጹ አብርቶ፣ ልብሱ ጸዐዳ መስሎ ሲወጣ

ተመለከተው:: አጋንንቱም በርቀት ሲከተሉት ጠባቂ መልአኩ ግን በደስታ ተሞልቶ አጀበታል:: አባ ጳውሊ በደስታ ዘለሎ ጮኸ:: እግዚ አብሔ ርንም «የእግዚአብሔር ፍቅርና ርሕራሔ» ብሎ አመስግነና ከፍ ወደ አለ ሥፍራ እየሮጠ ሔደ:: በታላቅ ድምፅ «ኑ እና የእግዚአብሐ ሔርን ድንቅ ሥራ እዩ፤ እንዴት ኃይለኛና አስደናቂ እንደሆነ:: ሰው ሁሉ ይድን ዘንድ እንደሚፈልግ ኑና እዩ፤ ኑ ወደ እውነተኛው ዕውቀት፤ ኑ ከእግሩ ሥር ወድቀን ኃጢአትን ማስወገድ የምትችል አንተ ብቻ ነህ እንበለው» እያለ ጮኾ ተናገረ::

በዚህ ጊዜ ሁሉም በጥድፊያ እየሮጡ የሚለውን ለመስማት ወደ እርሱ ቀረቡ:: ሁሉም በተሰበሰቡ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ያየ ውንና ከጸሎት በኋላ የተፈጸመውን ነገራቸው:: ያንን ወንድም ጠር ቶም እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ለውጥ በርሱ ላይ ያመጣበትን ምክንያት እንዲነግራቸው ጠየቀው::

ያም ወንድም የሆነውን ነገር በሁሉም ፊት መግለጥ ጀመረ:: «እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ:: ለብዙ ጊዜ በዝሙት ውስጥ እኖር ነበር:: ዛሬ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስገባ የነቢዩ የኢሳይያስ መጽሐፍ ሲነበብ ሰማሁ:: «ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ፣ የሥራችሁን ክፋት ከዐይኔ ፊት አስወግዱ፤ ክፉ ማድረግን ተው፤ መልካም መሥራትን ተማሩ፤ ፍርድን ፈልጉ የተገፋውን አድኑ:: ለድኻ አደጉ ፍረዱለት፤ ስለ መበለቲቱም ተሟገቱ:: ኑ እና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፣ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትጠቁር እንደ ዐመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች:: እሺ ብትሉ ብትታዘዙም የምድርን በረከት ትበላላችሁ» (ኢሳ.1÷16-19) ይላል:: «በዚህ ጊዜ እኔ ዘማዊው በዚህ ቃል የተነሣ ተፀፀትኩ፣ በልቤም አሰምቼ ጌታ ሆይ ወደ ምድር የመጣኸው ኃጥአንን ለማዳን ነው:: በነቢይህ ቃል ያወጅከውን በእኔ ፈጽመው:: እኔ በደለኛና ዋጋ አልባ ነኝና ብዬ ተናገርኩ:: ከአሁን ጀምሮ በልቤ ቀርጫለሁ፤ በንጹሕ ልቡና አገለግልሃለሁ፤ ጌታ ሆይ ከአ ሁን ሰዓት ጀምሮ ተቀበለኝ:: ንስሐ ገብቼ በእግርህ ሥር ወድቀ ያለሁና፤ ለወደፊቱ ከክፋት ሁሉ ለመራቅ እሻለሁና፤ ይህንን ብዬ ከቤተ ክርስቲያን ወጣሁ::» በዚህ ጊዜ ሁሉም አንድ ሆነው «አቤቱ ሥራህ እጅግ ብዙ ነው፤ ሁሉን በጥበብ አደረግክ (መዝ.103÷24) እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑት::»

ስለዚህም ከቅዱሳት መጻሕፍት እና ከመገለጦች የምንማር ክርስ ቲያኖች እንደመሆናችን በርሱ ለሚመኩና ኃጢአታቸውን በንስሐ





ለሚያጥቡ እግዚአብሔር ያለውን ደግነት ዕወቁ:: ስለዚህም ለመዳን ተስፋ አንቁረጥ:: በእውነት በነቢዩ በኢሳይያስ እንደታወጀው እግዚ አብሔር በኃጢአት ያደፉትን ያነጻቸዋል፤ እንደባዘቶና እንደ በረዶ ነጭ ያደር ጋቸዋል፤ የሰማያዊቱን ኢየሩሳሌም ጌጦችም ይሸልማቸዋል:: በነቢዩ በሕዝቅኤል «የሚቹን ሞት አልፈቅድምና ይላል እግዚአብሔር፣ ተመ ልሳችሁ በሕይወት ኑሩ» /ሕዝ.18÷32/»::

## አባ ሩፎስ

አባ ሩፎስ እንዲህ አለ:: አንድ አባት እንዲህ ነገረኝ «በሰማይ አራት ደረጃዎችን አየሁ:: በመጀመሪያው እርከን ፈጣሪውን ሳያማርር የሚያመ ሰግን በሽተኛ አየሁ፣ በሁለተኛው እንግዶችን በፍቅር የሚቀበል ሰውን ተመለከትኩ፣ በሦስተኛው ማንንም ሳያይ በረሓ የሚያቋርጥ ሰው አየሁ:: በአራተኛው ደግሞ ለአባቱ የሚታዘዝና ስለ ጌታ ብሎ የተባለውን ሁሉ የሚፈጽምን ሰው አየሁ:: በመታዘዝ የሚኖረው የወርቅ ሐብል አሥሮ፣ የወርቅ ጋሻ ታጥቆ ከሁሉም የበለጠ ክብር ተጐናጽፎ አየሁት:: ይመራኝ የነበረውን «ይህ አራተኛው ከሁሉ የበለጠ ክብር ለምን ተሰጠው?» ብዬ ጠየቅኩት:: እርሱም እንግዳ የሚቀበል ሰው በራሱ ፈቃድ የሚሠራ ነው፤ ተአዛዡ ግን የራሱን ፍላጐት ሁሉ ትቶ፣ በእግዚአብሔር እና በመን ፈሳዊ አባቱ ታምኖ ይኖራል» አለኝ:: «ይህን የመሰለ የላቀ ክብር ያገኘ ውም በዚህ የተነሣ ነው» ሲል መለ ሰልኝ:: ልጄ ሆይ ተመልከት፣ ለክር ስቶስ ሲባል የሚፈጸም ከሆነ መታዘዝ እንዴት ታላቅ ነገር መሰለህ? እና ንተ የዚህን በጐ ምግባር ገጽታዎች በመጠኑ ተገንዝባችኋል:: መታዘዝ ሆይ የታማኞች መዳኛ፣መታዘዝ ሆይ የበጐ ምግባሮች ሁሉ እናት፤ መታ ዘዝ ሆይ የመንግሥተ ሰማያት መገለጫ፤ መታዘዝ ሆይ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻና የሰው ልጅ ከምድር ወደዚያ እንዲያርግ የምታስ ችይው፤ መታዘዝ ሆይ የቅዱሳን ሁሉ ምግብ፤ ለሚጠቡሽ ወተታቸው፣ ቅዱሳን ባንቺ ፍጹማን ሆኑ፤ መታዘዝ ሆይ የመላእክት ወዳጅ::

## አባ ሲዞስ[14]

1. አባ ሲዞስ በአባ እንጦንስ ገዳም በተራራ ላይ ይኖር ነበር:: ረድኡ ከሔደ ብዙ ጊዜው ስለሆነ ለዐሥር ወራት ያህል ማንንም ሰው አላየም ነበር:: በተራራው ላይ ወዲያ ወዲህ ሲል አንድ ግብፃዊ አዳኝ ተመለከተ:: አባ ሲዞስም «ከየት መጣህ? እዚህስ ምን ያህል ጊዜ

14 አባ ሲዞስ ምናኔን የተማረው በአባ አውር እግር ሥር በገዳመ አስቄጥስ ነው:: አባ እንጦንስ ታላቁ ካረፈ በኋላ ገዳመ አስቄጥስን ትቶ ሔደ:: ከዚያም በአባ እንጦንስ ተራራ ላይ ለሰባ ሁለት ዓመታት በበኣት ኖሯል::

ኖርክ?» ሲል ጠየቀው:: አዳኙም «እኔ በዚህ ቦታ ዐሥራ አንድ ወር ሆኖኛል፤ ነገር ግን ካንተ በቀር ማንንም አላየሁም» አለው:: በዚህ ጊዜ ይህን ሲሰማ ወደ በአቱ ገብቶ ደረቱን እየደቃ «ሲዞስ ሆይ ተመልከት አንተ ልዩ የሆነ ነገር የሠራህ መስሎሃል፤ ነገር ግን ገና ከዚህ አዳኝ ጋር እንኳን መስተካከል አልቻልክም» አለ::

2. አንድ ወንድም አባ ሲዞስን «አባ በቀድሞ ዘመን ሰይጣን አሁን እኛን በሚፈትንበት ሁኔታ ሰዎችን ይፈትናቸው ነበርን?» ሲል ጠየቀው:: እርሱም «ዛሬ ብሶበታል፤ ምክንያቱም ዘመኑ እያለቀ በመሆኑ በጣም ተበሳጭቷልና አለው::»

3.አባ ሲዞስ በሞት አፋፍ እያለ አበው በዙርያው ተሰባስበው ነበር:: በዚያ ሰዓት ገጹ እንደ ፀሐይ አበራ:: ወዲያውም «ተመልከቱ አባ እንጦንስ መጣ»አላቸው:: ጥቂት ቆይቶ «ተመልከቱ የነቢያት ማኅበር መጡ» አለ:: ገጹ ብሩህ ሆነና «ማኅበረ ሐዋርያት መጡ» አለ::

የገጹ ብርሃን እየጨመረ መጣ:: ከዚያም ከአንድ ሰው ጋር ይነጋገር ጀመር:: አረጋውያን አበው «ከማን ጋር ነው የምትነጋገረው አባ?» ሲሉ ጠየቁት:: እርሱም «ተመልከቱ መላእክት ሊጠሩኝ መጡ፣ እኔም ለንስሐ ጊዜ እንዲሰጡኝ ለመንኳቸው» አላቸው:: እነዚያ አባቶችም «አባ ንስሐ መግባት አያስፈልግህም» አሉት:: እርሱ ግን «እንደ እውነቱ ከሆነ መንፈሳዊ ሕይወትን ገና አልጀመርኩትም» አለና መለሰ:: በዚህ ሁኔታ ከፍጹምነት መዓርግ መድረሱን ተረዱ:: ወዲያው ገጹ እንደ ፀሐይ አንፀባረቀና «ተመልከቱ ጌታችን ወደ እኔ መጣና ከበረሓው ውስጥ የተቀደሰውን ንዋይ አምጡልኝ አለ» ሲል ሰሙት:: ቤቱ በብርሃን ተሞላ፤ መልካም መዓዛም ዐወደው::

4. አንድ ጊዜ አባ ሲዞስ በአባ እንጦንስ ተራራ ላይ እያለ አርዮሳውያን መጡ:: እነርሱም የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን እየተቃወሙ ይናገሩ ጀመር:: አባ ሲዞስም ረድኡን ጠርቶ «አብርሃም እባክህ የአትናቴዎስን መጽሐፍ አምጣና አንብብልኝ» አለው:: አርዮሳውያኑም ኑፋቄያቸው እንደታወቀ ሲረዱ ጸጥ አሉ:: በሰላምም ሸኛቸው::

5. አንድ ወንድም አባ ሲዞስን «አባ ወድቄያለሁና ምን ላድርግ?» አለው «እንደገና ተነሣ» ሲል መለሰለት:: ያም ወንድም «መልሼ ብነሣም እንደገና ወደቅኩ» አለው «እንደገና ተነሣ» ብሎ ነገረው:: «ለምን ያህል ጊዜ» ሲል መልሶ ጠየቀው «ወይ በጽድቅ አልያም በኃጢአት እስክትሸነፍ ድረስ:: ማንም ሰው የሚፈረድበት በመጨረሻ





በተገኘበት ሁኔታ ላይ ነውና» አለው::

6. እግዚአብሔርን ፈልግ እንጂ መኖርያውን አትፈልግ::

7. የምንተ እፍረትና የፈሪሓ እግዚአብሔር መጥፋት ሰውን ወደ በደል ይመራሉ::

## አባ ስልዋኖስ[15]

1. አንድ ጊዜ አባ ስልዋኖስ ከወንድሞች ጋር ተቀምጦ እያለ ተመስጦ መጣበት:: ወዲያውም መሬት ላይ በግንባሩ ተደፋ:: ከረዥም ሰዓት በኋላ ተነሥቶ አለቀሰ:: ወንድሞችም «ምንድን ነው?» ሲሉ ጠየቁት:: እርሱ ግን በአርምሞ ሆኖ ያነባ ጀመር:: አብዝተው ሲለምኑት «የጌታን ፍርድ እመለከት ዘንድ ተነጥቄ ነበር:: ሔጄም ፍርዱን አየሁ:: ብዙ እኛን መሰሎች መነኩሳት ሲፈረድባቸው ብዙ ዓለማውያንም ወደ መንግሥተ ሰማያት ሲገቡ ተመለከትኩ» አለ:: አባ ስልዋኖስ በጥልቅ ሐዘን ተዋጠ:: ከዚያ በኋላ ከበአቱ መውጣት አይሻም ነበር:: በግድ የሚወጣበት ምክንያት ካጋጠመው ፊቱን በአጽፉ ሸፍኖ እንዲህ እያለ ይጓዝ ነበር «ይህንን ምድራዊ ብርሃን ለማየት ለምን እሻለሁ:: ምንም ጥቅም የለውም 'ኮ::»

2. በሌላ ጊዜ በበአቱ እያለ እጆቹን ዘርግቶ በተመስጦ ውስጥ ገባ:: ረድኡ ዘካርያስ ሲገባ በተመስጦ ላይ መሆኑን ሲረዳ በሩን ዘግቶለት ወጣ:: በስድስት ሰዓትና በዘጠኝ ሰዓት ዘካርያስ ሲመለስ በዚያው ሁኔታ ላይ ነበር:: በዐሥረኛው ሰዓት ተመልሶ መጥቶ አንኳኩቶ ሲገባ ቁጭ ብሎ አገኘው:: ዘካርያስም «አባ ዛሬ ምን ገጠመህ?» አለው:: አባ ስልዋኖስም «ልጄ ሆይ ዛሬ አሞኛል» አለው:: ዘካርያስም ወዲያው እግሩ ሥር ተደፍቶ «ያየሀውን ካልነገርከኝ አልተውህም» አለው:: አባ ስልዋኖስም «ወደ ሰማይ ተነጥቄ የእግዚአብሔርን ክብር እመለከት ነበር:: እስከ አሁንም እዚያው ነበርኩ:: አሁን ግን ተመለስኩ» አለው::

3. አባ ስልዋኖስ በደብረ ሲና እያለ ረድኡ ዘካርያስ ለመልእክት ወደ ውጭ ሲወጣ አባ ስልዋኖስን «ጉድጓዱን ከፍተህ አትክልቱን አጠጣው» ብሎት ሔደ:: አባ ስልዋኖስ ፊቱን በአጽፉ ሸፍኖ እግር እግሩን

15 በትውልድ ፍልስጥኤማዊ የሆነው አባ ስልዋኖስ ዐሥራ ሁለት አርድእት የነበሩበት ማኅበር አበ ምኔት ነበር:: ማኅበሩ በ380 ዓ.ም ወደ ደብረ ሲና ተጓዘ:: በመቀጠልም ወደ ጋዛ ሔዶ በሳቭራ ሠፈረ:: ያረፈው ከ414 ዓ.ም በፊት ነው::

ብቻ እያየ አትክልቱን ያጠጣ ጀመር። በዚህ ጊዜ አንድ ወንድም መጣ። የሚያደርገውን አይቶ ተገረመና «አባ አትክልቱን ስታጠጣ ፊትህን ለምን በአጽፍህ ትሸፍናለህ?» ሲል ጠየቀው። «ዐይኖቼ ዛፎቹን እንዳያዩ ብዬ ነው ልጄ፤ ምናልባት ሐሳቤ በእነርሱ ይሰረቅ እንደሆን ማን ያውቃል» አለው።

4. አንድ ወንድም አባ ስልዋኖስን ለማየት ወደ ደብረ ሲና ወጣ። በዚያ የሚገኙ ወንድሞች ተግተው ሲሠሩ አየና ለአባ ስልዋኖስ «ለሚ ጠፋ ምግብ አትድከሙ /ዮሐ.6፥27/ ማርያምስ የማይቀሟትን ዕድል መረጠች (ሉቃ.10፥42) ተብሏል አለው። አባ ስልዋኖስም ለረድኡ ለዘ ካርያስ «ዘካርያስ ይህንን ወንድም መጽሐፍ ስጠውና በበአት ውስጥ አስቀምጠው፤ ሌላ ነገር ግን አትስጠው» አለው። ያ ወንድም ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ምናልባት አንድ ሰው ለማዕድ ይጠራኝ ይሆናል ብሎ በር በሩን ያይ ጀመር።

ማንንም ሲያጣ ተነሥቶ ወደ አባ ስልዋኖስ ተጓዘና «ዛሬ ውንደ ሞች አይበሉም እንዴ?» ሲል ጠየቀው። አባ ስልዋኖስ ተመግበው መጨረሳቸውን ነገረው። «ታዲያ ለምን እኔን አልጠራችሁኝም?» አለው። አባ ስልዋኖስም «ምክንያቱም አንተ መንፈሳዊ ሰው ስለሆንክ ይህን መሰሉን ምግባር አትፈልገውም ብለን ነው። እኛ ሥጋውያን ስለሆንን እንመገባለን፤ የምንሠራውም በዚህ ምክንያት ነው። አንተ ግን የማይቀሙህን ዕድል መርጠሃል፤ ቀኑን ሙሉም መጽሐፍ ብቻ ታነባለህ፤ አላፊ ጠፊ ምግብም አያስፈልግህም» ሲል መለሰለት። ይህን ሲሰማ ያ ወንድም በግንባሩ ተደፍቶ «ይቅር በለኝ» ብሎ ለመነ። አባ ስልዋኖስም «ለማርያም ማርታ ታስፈልጋታለች። ማርያም የተመሰ ገነችው በማርታ ምክንያት ነውና ለማርታ ምሥጋና ይገባት» አለው።

5. ዝናው ከሥራው በላይ የገነነበት ሰው ያልታደለ ነው።

## አባ ስምዖን

አንድ ጊዜ የአካባቢው ገዥ አባ ስምዖንን ለማየት መጣ። የቤተ ክርስቲያኑ ካህናት ቀድመው ሔዱና «ገዥው ካንተ ቡራኬ ለማግኘት መጥቷልና ተዘጋጅተህ ጠብቀው» አሉት። አባ ስምዖንም «እሺ እዘጋ ጃለሁ» ብሎ ከሸኛቸው በኋላ የተቀደደ ልብስ ለብሶ፤ በዳቦ ላይ አይብ ጨምሮ ከበአቱ ውጭ እየበላ ቁጭ አለ። ገዥው በመጣ ጊዜም ናቀውና «ያን ያህል ዝናውን የሰማሁለት ባሕታዊ ይህ ነውን?» ብሎት





ትቶት ሔደ።

## አባ ሳርማታስ

1. ኃጢአቱን ተረድቶ ንስሐ የሚገባ ኃጢአተኛ፣ ምንም በደል ከሌለበት ነገር ግን ራሱን እንደ ጻድቅ ከሚቆጥር ሰው የበለጠ ይሻለኛል።

2. አባ ሳርማታስ በአባ ጴሜን ምክር ለብቻው ዘግቶ ዐርባ ቀን ቆየ። ዐርባ ቀኑ ሲፈጸም ምንም ልዩ ነገር እንዳላደረገ ተሰማው። አባ ጴሜን ሊጐበኘው ሔደና «በዚህ ዓይነት ተጋድሎ ስትሰነብት ምን ነገር ተገለጠልህ?» ሲል ጠየቀው። አባ ሳርማታስም «ምንም አዲስ ነገር የለም» አለው። አባ ጴሜን ግን «ካልነገርከኝ አልለቅህም» ብሎ ያዘው። በዚህ ጊዜ አባ ሳርማታስ «አንድ ቀላል ነገር ተገል ጦልኛል። ዕንቅልፌን «ና» ስለው ይመጣል፤ «ሒድ» ስለው ይሔዳል» አለው።

## አባ ሰራፕዮን

1. አባ ሰራፕዮን በአንድ የግብፃውያን መንደር መካከል ሲያልፍ አንዲት ጋለሞታ አየ። እርሱም «በዚህ ምሽት ጠብቂኝ፣ ሌሊቱን ካንቺ ጋር አሳልፋለሁ» ብሏት ሔደ። ጋለሞታዋም ራሷንም አልጋ ዋንም አዘጋጀች። ሲመሽ አባ ሰራፕዮን መጣና «አልጋውን አዘጋጀሽ ውን?» ሲል ጠየቃት። «አዎ አባ» ስትል መለሰች። በሩን ግጥም አድ ርጐ ከዘጋው በኋላ «ጥቂት ጠብቂኝ፣ በሕጋችን መሠረት ቀድመን መ ጸለይ አለብንና፤ መጀመሪያ ያንን ልፈጽም» አላት። ከዚያም ዳዊት መድገም ጀመረ። ከእያንዳንዱ መዝሙር በኋላ ለዚያች ሴት ይጸል ይላት ነበር። ይህን ከመሰለው ሕይወት አውጥቶ እግዚአብሔር ነፍ ሷን ያድን ዘንድ አጥብቆ ለመነው። እግዚአብሔርም ሰማው። ያቺ ሴት እየተንቀጠቀጠች ከአባ ሰራፕዮን አጠገብ ቆመችና መጸለይ ጀመ ረች። መዝሙረ ዳዊትን ሲጨርስ ያቺ ሴት መሬት ላይ በግን ባርዋ ተደፋች። ከዚህ በኋላ ደግሞ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን መልእ ክታት ማንበብ ቀጠለ።

ጸሎቱን ሲፈጽም ያቺ ሴት ልቡናዋ በጸጸት ተመልቶ ይህ ታላቅ ሰው ወደርሷ የመጣው ነፍሷን ለማዳን እንጂ ኃጢአት ለመሥራት አለ መሆኑን ተረዳች። ከዚያም እግሩ ሥር ተደፍታ «አባ እባክህን እግዚ አብሔርን ላስደስትበት ወደምችለው ቦታ ውሰደኝ» አለችው። እርሱም

ከጾም ጋር የተባበረ ጸሎትም ከፉ ሐሳቦችን ነቅሎ ይጥላል።

3. በገዳም ውስጥ ካለህ ወደ ሌላ ቦታ አትጓዝ። ያ እጅግ በጣም ይጐዳሃልና። የታቀፈችውን ዕንቁላሏን ትታ የምትጓዝ ርግብ እንዳይፈ ለፈል እንደምታደርገው ሁሉ፣ በአቱን ጥሎ የሚዞር መነኩሴም ዙረት ባበዛ ቁጥር በእምነቱ ቀዝቅዞ ይሞታል።

4. የሰይጣን ብልሃቱ ብዙ ነው። ነፍስን በድህነት ማሸነፍ ካቃተው ብልጽግናን ያመጣባታል፤ በስድብ ማሸነፍ ካቃተው ክብርና ውዳሴ ያስ ከትልባታል። በጤንነት ድል ማድረግ ካቃተው፣ ሕመምን ያመጣል፤ በምቾት ማባበል ሲሳነው ከፍላጐት ውጭ በሆነ ስቃይ ይሞክራል። ከዚህም ጋር እጅግ መራር የሆነ ደዌ ያመጣል። ገና ያልጸኑትን ፈሪ ዎች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ያቀዘቅዝባቸው ዘንድ። ሰው ነትን በክፉ ንዳድ ይመታና ያከሳቸዋል፤ ሊቋቋሙት የማይችሉ ውኃ ጥምም ያመጣባቸዋል።

ኃጢአተኛ እንደመሆንህ ይህን ሁሉ ስታልፍ የፈጣሪህን ፍርድ፣ የማይጠፋውን እሳት፣ የሚመጣውን ዘለዓለማዊ መከራ አስብ። ነገር ግን ተስፋ አትቁረጥ። እግዚአብሔር ይጐበኝሃልና ደስ ይበልህ። «መገ ሥጽስ እግዚአብሔር ገሠጸኝ፣ለሞት ግን አልሰጠኝም»(መዝ.117÷18) የሚለውንም ቃል አስበው። አንተ እንደ ብረት ነህ። እሳቱ ዝገትህን ያጠዳልሃል። ጻድቅ ሆነህ በደዌ ብትመታ ከኃይል ወደ ኃይል ያሸጋ ግረሃል። ወርቅ ነህን? እሳት ያነጻሃል። የሥጋ መውጊያ ተሰጥ ቶሃ ልን? (2ኛቆሮ.12÷9) በዚህ መልክ የተፈተነ ማን እንደሆነ አስብና ተደሰት። ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር አንድ ዓይነት መከራ መቀበል ላንተ ክብር ነውና። በንዳድ ትሰቃያለህን? «በብርድ ተመትተሃልን?» በእሳ ትና በውኃ መካከል አለፍን ወደ ዕረፍትም አወጣኸን (መዝ.65÷12) ያለውን ቃል አስበው። አንዱን ስትሻገር ሌላውን ጠብቅ፤ በበጐ ኀሊና ውስጥ ሁንና የከንፈርን መሥዋዕት ሠዋ፤ «እኔ ችግረኛ ቁስለኛ ነኝ /መዝ.68÷29/ በል፤ ይህንን የመሰለውን ድካም ከተቀበልክ ወደ ፍጹም ነት ትደርሳለህ።» እግዚአብሔር በጠራሁት ጊዜ ሰማኝ (መዝ.4÷3) ብሏልና አንደበትህን ክፈት፣ በእነዚህ የነፍስ ውጣ ውረዶች ውስጥ በማለፍ በጠላታችን ዓይን ሥር እያለፍን መሆኑን ትረዳ ዘንድ።

4. እንደ ቀራጩ ሁን፤ ከፈሪሳዊው ጋር አብረህ እንዳትኰነን፣ የሙሴን ትሕትና ምረጥ፣ ጠጣሩና ዐለቱ ልብህ ወደ ውኃ ምንጭ ሲለወጥ ታገኘዋለህና።





5. አለመቆጣት መልካም ነው። ካጋጠመ ግን ሐዋርያው ይህን ለመሰለው ያር ሙሉ ቀን አልሰጠህም። ፀሐይ አይግባ ብሏልና (ኤፌ.4÷25)። ዘመንህ ሁሉ እስኪያልቅ ትጠብቃለህን? ያሳዘነህን ሰው ለምን ትጠላዋለህ? ክፉውን ያደረገብህ እርሱ አይደለም፤ ያ ክፉ ዲያብሎስ ነው እንጂ። በሽታን እንጂ በሽተኛን ሰው አትጥላ።

6. ጠላት ዲያብሎስ እንድንፈጽመው የሚፈልገው ዓይነት ገዳ ማዊ ሕይወት አለ። ታድያ ሰማያዊውንና መንፈሳዊውን የገዳም ሕይ ወት ከሰይጣናዊው እንዴት እንለየዋለን? ያለጥርጥር ወጥ በሆነው ምጣ ኔው ነው። ሁል ጊዜ አንድ ዓይነት የሆነ የጾም ሕግ ይኑርህ። አራት ወይም አምስት ቀን ከጾምክ በኋላ ልክ በሌለው ምግብ አትግደፍ። በእ ውነቱ አለማመጣጠን ምን ጊዜም የጥፋት ምንጭ ነው። ወጣትና ጤናማ ከሆንክ በድካም ለምትሸነፍበት ለእርጅናህ ዘመን ጭምር ጹም። በቻልከው መጠን ሀብት አከማች /መንፈሳዊ ሀብት/፤ በማት ችልበት ጊዜ ትመነዝረው ዘንድ።

7. በፍርክታዎች ውስጥ ተቀምጠው ጠባያቸው ግን በከተማ እንዳ ሉት ሰዎች የሆነ ብዙ መናንያን አሉ። እነዚህ ጊዜያቸውን እያባከኑ ነው። በብዙ ሰዎች መካከል ተቀምጦ ኀሊናን ባሕታዊ ማድረግ፤ እንዲ ሁም በብሕትውና ተቀምጦም በሐሳብ በከተማ ውስጥ መኖር ይቻላል።

8. ከጠላታችን ለመጠበቅ በሁሉም መንገድ መታጠቅ አለብን። ከውጭም ያጠቁናል ከውስጥም ይቆሰቁሱናል። በዚህ ጊዜ ነፍስ በባሕር ማዕበል እንደተመታች መርከብ ትሆናለች። ከውጭ ማዕበል ያናጋታል ከውስጥ ደግሞ በተሰበረው ክፍል ውኃ ይገባባታል። በውስጥ በሚ ፈጠር ፍትወት የምንፈተነውን ያህል በአፍአ በሚሠራ ኃጢአት እን ፈተናለን። ስለሆነም ከአፍአም ከውስጥም ራሳችንን መጠበቅ አለብን።

## አባ ጥጦስ

1. አንድ ወንድም አባ ጥጦስን «እንዴት ልቤን መጠበቅ እችላ ለሁ?» ሲል ጠየቀው። አባ ጥጦስም «አፋችንና ሆዳችን ክፍት ከሆነ እንዴት ልባችንን መጠበቅ ይቻለናል?» ሲል መለሰለት።

2. «ወደ ትሑት ሰብእና የሚመራው መንገድ የቱ ነው?» ሲል አንድ ወንድም ጠየቀው። እርሱም ሲመልስ «የትሑት ሰብእና መገኛ መንገድ ራስን መግዛት፣ ጸሎትና ራስን የሁሉም ፍጥረታት የበታች አድርጎ ማሰብ ነው» አለው።

ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት ቤ/መጻሕፍት

# አባ ጢሞቴዎስ

ካህኑ አባ ጢሞቴዎስ ለአባ ጴሜን የሚከተለውን ነገረው። «ግብፅ ውስጥ በዝሙት ሥራ የምትተዳደር አንዲት ሴት አለች፤ ያገኘችውን ገንዘብ ግን በምጽዋት ትሰጠዋለች» አባ ጴሜንም «እርስዋ በዝሙት ሥራ አትቀጥልም የእምነት ፍሬ በውስጥዋ እያደገ፤ ነውና» አለው። የካህኑ የአባ ጢሞቴዎስ እናት ልታየው በመጣች ጊዜ «ያቺ ሴት አሁንም በዝሙት ውስጥ ናትን?» ብሎ ጠየቃት። እናቱም «እንዲያውም ወዳጆቿ በዝተዋል ነገር ግን የምትሰጠው ምጽዋትም በዚያው ልክ ጨምሯል» አለችው። አባ ጢሞቴዎስም ይህንኑ ለአባ ጴሜን ነገረው። አባ ጴሜንም «እርስዋ በዝሙት ሥራ አትቀጥልም» ብሎ መለሰለት።

በሌላ ጊዜ የአባ ጢሞቴዎስ እናት ስትመጣ «ታውቃለህ ያቺ ኃጢአተኛ ሴትኮ አንተ ትጸልይላት ዘንድ አብራኝ ልትመጣ ፈለገች» ብላ ነገረችው። ይህን ሲሰማ አባ ጢሞቴዎስ ለአባ ጴሜን ነገረው። «ሒድና አግኛት» አለው አባ ጴሜን። ያቺ ሴት አባ ጢሞቴዎስን አግኝታ የእግዚአብሔርን ቃል ሲነግሯት ልቧ በፀፀት ተሞላ፤ በዕንባም ታጠበች። «ከዛሬ ጀምሮ እግዚአብሔርን አጥብቄ እይዛለሁ፤ የዝሙት ሥራንም አልሠራም፤» ስትል ቃል ገባች። ወደ ገዳም ገብታም እግዚአብሔርን ደስ አሰኝታ ዐረፈች።

# አባ አውር[17]

1. የመነኩሴ አክሊሉ ትሕትናው ነው።

2. ከመጠኑ በላይ የሚመሰገንና የሚከበር ሰው ብዙ ኩነኔ ያገኛል። በሰው ዘንድ ከቁም ነገር ሳይቆጠር መልካም ሠርቶ ያለፈ ሰው ግን በሰማይ ታላቅ ክብር ይጠብቀዋል።

17 ከአባ ሲዞስ እና ከአባ ቴዎዶር ጋር በንትራ ገዳም መጀመርያ አካባቢ ከሠፈሩ አበው አንዱ። ያረፈው በ390 ዓ.ም ነው።